# ሁለተኛ ዙር የጥያቄዎች መልስ



**አዘጋጅ፡- በትረ ማርያም አበባው ካሣ**

**(የመጻሕፍተ ብሉያት፣ የመጻሕፍተ ሊቃውንትና የመጻሕፈተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)**

**ግንቦት ፩፣ ፳፻፲፫ ዓ.ም**

# መግለጫ

**መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ራእየ ዮሐንስ ለተጠየቁ ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጠው ከዚህ ቀጥሎ በፎቶ የምታዩት ይህ ኦርቶዶክሳዊ ተዋሥኦ መጽሐፍ ነው፡፡**




**መጻሕፍተ ሊቃውንት ላይ ማለትም ፍትሐ ነገሥት፣ ሃይማኖተ አበው፣ መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ድርሳነ ቄርሎስ ወጰላድዮስ፣ ውዳሴ ማርያም፣ ድርሳነ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ተግሣጸ ዮሐንስ አፈወርቅ ላይና የሐዋርያት ሲኖዶስ ላይ እንዲሁም መጻሕፍተ መነኮሳት ላይ ለተጠየቁ ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጥ መጽሐፍ ደግሞ ኦርቶዶክሳዊ ተዋሥኦ ቅጽ 2 ነው፡፡**




**እነዚህ ሁለቱ መጻሕፍት የሚገኙት አዲስ አበባ፣ አራት ኪሎ ቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ሕንፃ ሥር ኦሜጋ መጻሕፍት መደብር፣ ስልክ ቁጥር 0941555550 ደውላችሁ ማግኘት ትችላላችሁ፡፡**

# የጥያቄዎች መልስ

## ፩. የአንድ ሰው አካል ክፍል (ከሕያውም ሆነ ከሞተ ሰው ላይ የሚወሰድ) ወደ ሌላ ሰው አካል መተካት ይፈቀዳል? ሰው የገዛ አካሉን ክፍል የራሱ ላልሆነ ሰው መስጠት ተፈቅዶለታል? ደም መለገስ፣ ዓይንን፣ ኵላሊትን መስጠት?

መልስ፦ በዚህ ዙሪያ የተወሰነ ውሳኔ እስከዛሬ አላየሁም:: በመምህራን ዘንድ ግን ሁለት ዓይነት እሳቤዎች አሉ:: አንደኛው አንድ ሰው አካሉን ያገኘው ከእግዚአብሔር ስለሆነ ለሌላ ሊሰጠው አይገባም የሚሉ ናቸው:: ሁለተኛው እኛ ሳንጎዳ በእኛ አካል ሌላውን ማዳን ከቻልን ከዚህ የበለጠ ፍቅር ለማንም የለም ብለው የዮሐንስ ወንጌልን የሚጠቅሱ ናቸው:: "ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም" እንዲል (ዮሐ.15፥13):: ሁለቱም ኵላሊቶቹ የታመሙበት ሰው ቢኖር አንዱን ኵላሊት ሰጥተውት ጤናማ የሚሆን ከሆነና በፈቃዳቸው ቢሰጡት እንዲያውም ከጽድቅ ይቆጠራል የሚሉ ምሁራን አሉ:: ደም ያነሰውን ሰው ደም ሰጥተነው የሚድን ከሆነ መስጠት መልካም ነው ይላሉ:: ደም የሚሰጠው ሰው ግን ቆርቦ ከሆነ ከ24፡00 ሰዓት በኋላ መስጠት ይገባዋል ይላሉ:: ምክንያቱም ዕለቱን መታገም፣ መተኮስ አይገባም ተብሏልና ይላሉ:: በተቃራኒው ያሉ ሰዎች ደግሞ ምንም እንኳ ደሙን ብንሰጠው ደሙን በግሉኮስ መልኩ ስለሚሰጠው የሰውን ደም እንደመጠጣት ይቆጠራል አይገባም የሚሉ አሉ:: [የእኔ ፍርድ፦ እኔም ሁለተኛውን ሐሳብ ከሚደግፉት ወገን ነኝ:: እኛን የማይጎዳ ከሆነና ሌላው የሚጠቀምበት ከሆነ ብንሰጠው መልካም ነው ባይ ነኝ:: ሕክምናው ቀድሞ ከነበረበት ደረጃ ከፍ ሲል ልዩ ልዩ የሕክምና ጥበቦችም አብረው መጥተዋል:: ስለዚህ እንደዚህ ያሉ አዳዲስ ጉዳዮች ሲመጡ ቅዱስ ሲኖዶስ እየተከታተለ ቀኖና ቢቀንን መልካም ነው እላለሁ]::

## ፪. ባልና ሚስት ለየብቻቸው መቁረብ ይችላሉ?

መልስ፦ ባልና ሚስት በተጋቡ ጊዜ በአንድ ላይ ይቆርባሉ:: ከጋብቻ በኋላ ደግሞ ተፈጥሯዊ ሁኔታቸውን ባገናዘበ መንገድ፣ ንስሓ እየገቡ ሲመቻቸው በአንድ ቀን፣ ካልተመቻቸም በየራሳቸው መቍረብ ይችላሉ:: ዞሮ ዞሮ ከጋብቻ በኋላ ሴቷም በሴቶች ገጽ ሆና ትቆርባለች፣ ወንዱም በወንዶች ገጽ ሆኖ ይቆርባል:: የፈቃድ መለያየት እንዳይኖር ሊቆርቡ ሲሉ መነጋገር ይገባል::

## ፫. ማንኛውም ክርስቲያን ከፖለቲካ ነጻ መሆን የሚችለዉ እንዴት ነው?

መልስ፦ ክርስቲያን ከፖለቲካ ነጻ ይሁን አልተባለም:: ክርስቲያን ፖለቲከኛ፣ ወታደር፣ ሰላይ፣ ንጉሥ፣ የሀገር መሪ መሆን ይችላል:: ፍሬ ነገሩ እነዚህን ነገሮች ሲሆን ክርስትናውን መተው የለበትም:: እግዚአብሔር ለሚያምኑበትም ለማያምኑበትም የሰው ልጆች ሁሉ እኩል ፀሐይን እንደሚያመጣ፣ ክረምትና በጋን፣ መዓልትና ሌሊትን

እንደሚያፈራርቅ ሁሉ ክርስቲያንም ከላይ ያልናቸውን ማለትም ፖለቲከኛ፣ ወታደር፣ ሰላይ፣ ንጉሥና የመሳሰሉትን ሲሆን የሰው ልጆችን ሁሉ በእኩልነት በፍቅር ማገልገል ይገባዋል።

፬. አሁን ባለንበት ሁኔታ ፋኖ እና መከላከያ እየተዋጉ ነው። ቢሞቱ ይጸድቃሉ? አንድ ወታደር ጥይት እንዳይመታው ቢያሠራ ችግር አለው?

መልስ፦ አንድ ወታደር ጥይት እንዳይመታው ቢያሠራ ችግር አለው ወይ የሚለው ግልጽ አልሆነልኝም። ምናልባት ጠንቋዮች ጥይት የማያስመታ ድግምት ደግመን በአንገታችሁ ቋጥራችሁ ያዙት ጥይት አይመታችሁም እንደሚሉት ዓይነት ከሆነ ውሸት ስለሆነ መታለል አይገባም። እንዲህ ያለ አጭበርባሪ ካለ የማያስመታውን ያዘውና በአንተ እንሞክረው በሉት። የአጭበርባሪነት ጭንብሉ ወዲያው ሲወልቅ ታዩታላችሁ። ሰው ግዙፍ እስከሆነ ድረስ መመታት፣ መቍሰል፣ መሞት የሚችል ነው። መሪጌታ ነን ምናምን እያሉ በቤተክርስቲያን ስም የሚያጭበረብሩ ሰዎችም ውሸታቸውን ነው። በሁለት አካላት መካከል [ለምሳሌ በፋኖና በመከላከያ] በሚደረግ ውጊያ ቢሞት የሚጸድቀው የትኛው ነው ላላችሁኝ መልሱ እውነትን ይዞ የገጠመውና ለእውነት ሲል የሞተው ነው የሚል ነው።

፭. ልጁ ዲያቆን ነውና በአጋጣሚም ሆን ተብሎም ብቻ በተለያየ ምክንያት ከሴቶች ጋር ግኑኙነት አለው። የእኔ ማር የእኔ ውድ የሚሉ የዝሙት ቃላትን በመጠቀም፣ በመሳሳም፣ በመተቃቀፍ በሦስቱም ዘር ይፈሰዋል። ከሩካቤ ብቻ ንጹሕ ነው። ጥያቄዬ ልጁ ሊያገባ ነው እና እንዴት ይሁን? በተክሊል ያግባ ወይስ በመዓስባን?

መልስ፦ ድንግልና የሚተረጎም ሴትና ወንድ በመኝታ በሚፈጽሙት ግንኙነት መሠረት ነው። ይህም ማለት የሁለቱም መራቢያ አካል ግንኙነት ካደረገ ድንግልና ፈርሷል ይባላል። ከላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች ምንም እንኳ ታላላቅ ኃጢአቶች ቢሆኑም ድንግልናን ያስፈርሳሉ የሚል ግን እስካሁን አላገኘሁም። በተክሊል ሊያገባ ይችላል። ነገር ግን ከጋብቻ በፊት የድሪያ (የመዳራት) ቃላትን መጠቀምና ሌላውን ስሜት ውስጥ መክተት፣ ፍትወታዊ መሳሳምን ማድረግና፣ በጠቅላላው ፍትወታዊ ንክኪን (መተቃቀፍን) ማድረግ አይገባም። ይህ ግልጽ አመንዝራነት ነው። ቅዱስ ሲኖዶስ ከላይ የተጠቀሱትንም እንደሁኔታው አይቶ ከተክሊል እንደሚከለክሉ ቢገልጽ ምናልባት ጥንቃቄ ይበዛ ይሆናል። ስለዚህ ይህ ጉዳይ የብዙዎች ችግር እየሆነ ስለመጣ ጠንካራ ቀኖና ቢሠራ እላለሁ።

፮. ጤና ዘርፍ ላይ ያለሁ ሰው ነኝ። እና እንደ ሳይንሱ ከሆነ የሴትም የወንድም ድንግልና ልክ HIV positive/negative እንደሚባለው ድንግልና የሚባል ተጨባጭ ማረጋገጫ ያለው ነገር አይደለም። የፈጸመው ሰው በኅሊናው ስለሚያውቀው ነው እንጂ ድንግልናውን ሊመሰክር የሚችለው ድንግልና መፍረስ አለመፍረሱን የሚያረጋግጥ ምንም ዓይነት ከዚያው ሰው ውጪ

ማረጋገጫ የለውም። ይልቁንም ድንግልና social concept ተደርጎ ነው የሚወሰደው በሳይንስ። ስለዚህ የሥጋ ድንግልና ምን እንደሆነ በምን ተግባራት እንደሚጠፋ በግልጽ ቢያስረዱን።

መልስ፦ የድንግልናን ትርጉም በትክክል መረዳት አስፈላጊ ነው። በመሠረቱ ድንግልና የሚለው ጥሬ ምዕላድ ተደንገለ=ተጠበቀ ከሚለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ነው። ከግንኙነት መጠበቅን ያመለክታል። አንዳንዱ ከአፈ ማሕፀን መድማት ጋር ያያይዘዋል። ቁምነገሩ ግን ይህ አይደለም። ብዙ ጊዜ በባህላዊ መንገድ የአፈ ማሕፀን መድማት የድንግልና ምልክት ሆኖ ቢታይም ነገር ግን አንዳንድ ሴቶች በሥራ ብዛት ከወንድ ጋር ሳይገናኙ እንዲሁ ካገቡ በኋላም ላይደሙ ይችላሉ። ወይም ደግሞ ግንኙነት ሲያደርጉ የኖሩ ሴቶችም ባገቡ ጊዜ ሊደሙ የሚችሉበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል። ድንግልናዋን ያጣች ሴት በSurgery መልሳ ልትደማ የምትችልበት ሁኔታም እንዳለ አንዳንድ ሐኪሞች ነግረውኛል። ድንግልና የሚባለው ግን ከመድማት ጋር የሚገናኝ አይደለም። አንዲት ሴትና አንድ ወንድ ከተገናኙ ቢደማም ባይደማም ሁለቱም ድንግልናቸውን አጥተዋል። የድንግልና መለኪያ ግንኙነት ማድረግ አለማድረግ ነው እንጂ የአካል መድማትና አለመድማት ጉዳይ አይደለም።

## ፯. ነፍስ ለምን በሴት አንቀጽ ትጠራለች?

መልስ፦ በግእዝና በአማርኛ ጾታ የሌላቸውን አካላት የምንጠራበት ሌላ ሦስተኛ መጠሪያ የለም። ስለዚህ ጾታ የሌላቸውን ነገሮች አንዳንድ ጊዜ በሴት አንቀጽ አንዳንድ ጊዜ በወንድ አንቀጽ ሲነገሩ እናስተውላለን። ይህም ሌላ መጥሪያ መንገድ ስለሌለን ነው። ለምሳሌ ፀሐይን በሴት አንቀጽ ፀሐይ ወጣች ብለን የምንናገርበት ጊዜ አለ። በክርስቶስ ጊዜ የነበረውን ለመግለጽ ደግሞ ፀሐይ ጸልመ (ፀሐይ ጨለመ) ብለን በወንድ አንቀጽ እንናገራለን። ነፍስንም ብዙ ጊዜ የተለመደው በሴት አንቀጽ ተነግራ መጻፍ ነው። በወንድ አንቀጽ ቢጻፍም የሚያመጣው ለውጥ የለም። ፍሬ ነገሩ ነፍስ ሴትም፣ ወንድም አይደለችም። እንደ መላእክት ናት። መላእክት ደግሞ ሴትም አይደሉም ወንድም አይደሉም። በጠቅላላው የጾታ ምልክት የላቸውም።

## ፰. ንስሓ አባት በቅርብ ማግኘት ያልቻለ ሰው በስልክ ንስሓ መግባት ይችላል?

መልስ፦ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “ለማንም እንዳትናገር ተጠንቀቅ። ነገር ግን ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ" ባለው መሠረት በትውፊታችንም ንስሓ የሚገባ ሰው በአካል ሄዶ ንስሓ ይገባል (ማቴ.8፥4)። ነገር ግን ሰው ከኃጢአቱ መሞት ስለሌለበት ንስሓ አባቱን በቅርብ ለማግኘት የማይቻል ከሆነ በስልክ የሚያገኝበትን አግባብ ቅዱስ ሲኖዶስ ቀኖና ቢሠራልን መልካም ነው።

## ፱. ጡት የተወ ሕፃናት ነገር ግን ከ7 ዓመት በታች የሆኑ ከምግብ ምን ያክል ጊዜ ተከልክለው ነው መቁረብ ያለባቸው?

መልስ፦ ሕግ የሚፈጸመው ወይም የሚተገበረው ከሰባት ዓመት በላይ ባሉ ሰዎች ነው:: "ነግሀ የተባለ ከተወለዱ ጀምሮ እስከ ሰባት ዓመት ያለው ዘመን ነው:: እስከዚያ ሥርዓት አይሠራባቸውም:: መምህረ ንስሓ የሚይዙ ጾም የሚጀምሩ ከዚያ በኋላ ነውና" እንዲል (ማቴ.20፥2 አንድምታ ትርጓሜ):: ስለዚህ ከሰባት ዓመት በታች ያሉት እንደሌላው 18፡00 ሰዓት መጾም አይጠበቅባቸውም:: እንዳያስመልሳቸው የሚመች ጊዜ ቅዳሜና እሑድ እንዲቆርቡ ነው:: ማታ በልተው አድረው ጠዋት መቁረብ ይገባቸዋል [የወንበር መምህራን አስተያየት]::

## ፲. ሴት ከወለደች በኋላ ከስንተኛው ቀን ጀምሮ ነው ግንኙነት/ተራክቦ የሚፈቀደው?

መልስ፦ ልጇን ክርስትና ካስነሣች በኋላ ነው ግንኙነት የሚፈቀደው:: ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ላይ እንደተገለጸው ሩካቤ ከሚከለከልባቸው ነገሮች አንዱ ሕርስ (አራስነት) ነው:: "ወተከልኦሰ እምነ ሩካቤ በመዋዕለ ትክቶሃ ወሕርሳ ዝኒ፤ ሴት ልጅ በወር አበባዋ ወቅትና በአራስነቷ ጊዜ ከግንኙነት መራቅ የሚገባት በዚህ ምክንያት ነው:: በእንተ ዘይረክቦ ለአባለ ዘርዕ እሙስና:: ከበሽታ ወገኖች አባለ ዘርዕን ስለሚያጋጥመው ነው:: ወዘይዳደቆሙ ለውሉድ እለተፀንሱ፤ በዚያ ወራት የተፀነሱትን ደዌ ሥጋ ሊያገኛቸው ስለሚችል ነው" ተብሎ ተገልጿል::

## ፲፩. የሰንበትን ቀን የሚያከብር ሰው መንገድ አይሄድም:: ነገር ግን ለምሳሌ የታሰረ ለማየት፣ የሞተ ለማስቀበር፣ ሩቅ መንገድ ቢሄድ ይፈቀዳል?

መልስ፦ ሰንበት የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ በመሆኗ በመንግሥተ ሰማያት ደግሞ ዘለዓለማዊ ዕረፍት እንጂ ድካም አለመኖሩን በተግባራዊ መንገድ ለመግለጽ በሰንበት ሩቅ መንገድ አንሄድም:: የታሰረ ለማየት፣ የሞተ ለማስቀበር፣ የታመመ ለመጠየቅ ብንሄድ ግን በደል የለውም::

## ፲፪. በጸሎተ ኀሙስ በገጠር ይታረሳል፣ ይቆፈራል፣ በጣም ነጭ ሥራ ናት ይባላል:: በምን የተነሳ ነው ከሌሎች ቀን ተለይታ ለሥራ የተመረጠችው?

መልስ፦ የጸሎተ ኀሙስ መታረስ የለበትም:: ምክንያቱም ከሆሣዕና ጀምሮ እስከ ትንሣኤ ያለው ሙሉው ሕማማቱ ከዘጠኙ ዐበይት በዓላት አንዱ ስለሆነ ሥጋዊ ሥራ ሊሠራበት አይገባም:: ዘጠኙ ዐበይት በዓላት የሚባሉት አንዱ ሕማማት (ስቅለት በዚህ ይካተታል)፤ ከትንሣኤ እስከ ዳግማይ ትንሣኤ (ትንሣኤ በዚህ ይካተታል)፤ ትስብእት፣ ልደት፣ ጥምቀት፣ ዕርገት፣ ጰራቅሊጦስ፣ ሆሣዕና እና ደብረ ታቦር ናቸው::

## ፲፫. ሰው ሲሞት እስከ ስንት ጊዜ ነው ማልቀስ የሚፈቀደው?

መልስ፦ በእርግጥ ሰው ሲሞት ማልቀስ እንደማይገባና እንዲያውም በዝማሬ መሸኘት እንደሚገባ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በተግሣጹና በድርሳኑ ገልጿል (ተግሣጽ 4፤ ድርሳን

26):: የሰውን ትንሣኤውን ተስፋ በማድረግ በደስታ መሸኘት ይገባል እንጂ:: አንዳንድ አባቶች ደግሞ ነፍሱ ከሥጋው ስትለይ፣ አስከሬን ከቤት ሲወጣ እና ወደ መቃብር ሲወርድ ጌታ ይምረው ዘንድ ማልቀስ ይገባል ብለዋል:: ይህኛውን ልቅሶ በደንብ ካስተዋልነው ሟቹን ይምረው ዘንድ የሚደረግ ልቅሶ ስለሆነ ቁጥሩ ከጸሎት ነው:: ጌታችን በአልዓዛር ሞት እንዳዘነ ተጽፏል (ዮሐ.11፥33):: ይህ ኀዘንም ከሚያዝኑት ጋር ማዘን እንደሚገባ ለመግለጽ ለአርአያነት ነው:: "ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ፥ ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ" ይላልና (ሮሜ 12፥15)::

፲፬. አህያ፣ ፈረስ ወይም ሌላ እንስሳት ያዋለደ ሰው ከቤተክርስቲያን መግባት ከጠበል መግባት ይከለከላል?

መልስ፦ በዚህ ዙሪያ የተጻፈ አላገኘሁም:: ሰውን ያዋለደን የከለከለ ፍትሐ ነገሥት በእንስሳቱ ዙሪያ ምንም አላለም:: ስለዚህ ግላዊ አስተያየቴን ከምሰጥ ከማዋለድ ጋር ለተያያዙ ጉዳዮች አዲስ ሥርዓት ሲኖዶሱ ቢሠራልን (ሠርቶ ከነበረም ቢያሳውቀን)::

፲፭. ዜና አይሁድ በሐዲስ ኪዳን ነው የተጻፈው:: ግን ለምንድን ነው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ የተካተተ?

መልስ፦ ምንም እንኳ የተጻፈው በሐዲስ ኪዳን ቢሆንም ታሪኩ ግን ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ የነበረውን ሁኔታ የሚገልጽ በመሆኑ የቀኖና ሊቃውንት በብሉይ ኪዳን የመጻሕፍት ዝርዝር አካተውታል::

፲፮. የቅዳሴ ጠበልን ወደ ቤት ይዞ መሄድ ተገቢ ነውን?

መልስ፦ አይደለም:: ሲጀምር ለቆራብያን የሚሰጠው የቅዳሴ ጠበል ቆራብያን ብቻ በቆረቡ ጊዜ የሚሰጥ እንጂ ላልቆረበ ሰው እንኳን አይሰጥም:: ፍትሐ ነገሥቱ ማየ መቁረር ይለዋል:: መቁረር ማለቱ ከእሳተ መለኮት ከሥጋው ከደሙ አንጻር ነው (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 13):: ከማየ መቁረር ውጭ ያለ ጠበል ከሆነ ግን ከቤትም መውሰድ ይቻላል::

፲፯. ቤተክርስቲያን የምትሠራው የጌታችን ደም በነጠበበት ቦታ እንደሆነ እናምናለን:: ግን የት እንደነጠበ ለማን እየተገለጠ ነው?

መልስ፦ እግዚአብሔር ባወቀ በሰዎች ፈቃድ አድሮ ያሠራል:: ስለዚህ እኛ ደስ ካለን ቦታ እንሠራለን:: የነጠበበት ቦታ እንደሆነ ማስረጃው ተሠርቶ ታቦቱ ገብቶ ከተቀደሰበት ነው:: ያልነጠበበት ከሆነ ከዚያ ቦታ እነዚህን ነገሮች ማድረግ አይቻልም::

፲፰. የሚወራበት ሰውዬ በሌለበት የሚወራ መጥፎ ነገር ሁሉ ሐሜት ነው ማለት ይቻላል? (ለምሳሌ በሥልጣን ከእኔ በላይ የሆነው የቢሮ ኃላፊዬ ጉቦ ሲቀበል ባየውና ከጓደኛዬ ጋር

ስለእርሱ ባወራ) ትክክል ስለሆነን የሰዎች መልካም ያልሆነ ድርጊትን ማንሳት በሙሉ ሐሜት ነው ይባላል? ሐሜት ምን እንደሆነ ቢያስረዱኝ?

መልስ፦ ሐሜት ማለት አንድ ሰው በሌሎች ዘንድ ያለውን ተቀባይነት ለማሳጣት ተብሎ ስለሌላው ሰው ክፉ ነገሮች ማውራት ማለት ነው:: ወይም ደግሞ ስለሌሎች ሰዎች ክፉ ነገር ሲወራ ውስጣዊ ደስታን ማድረግ ነው:: ስለዚህ አንድ ሰው ጉቦ በልቶ ከሆነ መጀመሪያ ይህንን ክፉ ሥራዉን እንዲያቆም ለብቻው መምከር ነው:: ካልተቀበለ ሁለት ሦስት ሆኖ መንገር ነው:: እኒህንም ካልተቀበለ በአደባባይ መንገር ነው:: እነዚህ ሂደቶች የራሳችንን ሥራ አደጋ ላይ የሚጥልብን ሆኖ ከተገኘ ደግሞ ማስረጃዎችን አጠናክሮ ለበላይ አካል ማሳወቅና አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወሰድበት ማድረግ ነው:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ "ምንት ብከ በቍዔት ለእመ ትቤ እገሌ እኩይ ውእቱ፤ እገሌ ክፉ ነው ብትል ምን ጥቅም ታገኛለህ? ማለት ጥቅም አታገኝም" ብሏል (ተግሣጽ 1):: ስለዚህ ትተናት በምንሄዳት ዓለም ስለሌሎች ሰዎች ክፋት ማውራት አይጠቅመንም እንተወው::

፲፱. አንዳንድ የመንፈሳዊ ዜማ መሣሪያዎች መምህራን ክራርን 'የተወገዘ' ስለሆነ አናስተምርም ይላሉ:: በ1981 (ይመስለኛል) በተወሰነ የሲኖዶስ ውሳኔ ላይ ክራርን ለመገልገያነት አልጠቀሰውም:: አንዳንድ ደብራትም ዝማሬዎች በክራር እንዳይታጀቡ የሚያደርጉበት ሁኔታ አለ:: ስለ መወገዝ አለመወገዙ ወይም ስለተገቢነቱ ቢያስረዱኝ::

መልስ፦ በመሠረቱ እንዲህ ዓይነት ጉዳዮች በሲኖዶሱ ቸልተኝነት የሚፈጠሩ፣ የምእመናንን አንድነት የሚሸረሽሩና እርስ በእርስ የሚያነቃቅፉ ናቸው:: ክራር የመዝሙር መሣሪያነት እንዲያገለግል የተወሰነበት ጊዜ የለም (ከነበረም ለምእመናን በግልጽ አልተነገረም ወይም አልሰማሁም)፣ ይህ ብቻ አይደለም ክራር ለመዝሙር መሣሪያነት እንዳያገለግል የታገደበት ጊዜም የለም:: በመሆኑም ባልተወሰነ ጉዳይ ላይ ስንነታረክ እንውላለን:: ተወስኖ ከነበረ ጳጳሳት ባሉበት በክራር ሲዘመር ዝም መባል አይገባውም ነበር:: (ስለዚህ በጠቅላላው ብዙ ጉዳዮች ላይ አንድ እንዳንሆን በቅዱስ ሲኖዶሱ ቸልተኝነት ባለመወሰኑ የልዩነት ግድግዳ ሆኖ በመታየቱ ያሳዝናል):: በመሆኑም ሲኖዶሱ ግልጥ አድርጎ ወይ አይቻልም ወይም ይቻላል ቢል መልካም ነው::

፳. የሰንበት ትምህርት ቤት ጓደኞቼ ሲቆርቡ ራቅ ያለ ደብር በመሄድ ሲሆን ምክንያታቸውም መታየት አንፈልግም የሚል ነው:: እኔ ደግሞ የምታስተምሯቸው ሕፃናትና የእናንተም ጓደኞች እናንተ ስትቆርቡ ካላዩ ከማን ሊማሩ ነው ከታይታ ወይም ከከንቱ ውዳሴ ምን ያገናኘዋል? እላቸዋለው:: እርስዎ ምን ይላሉ?

መልስ፦ ቤተክርስቲያን አንዲት ናት:: የትም ቦታ ሄደን ብንቆርብ ምንም ችግር የለውም:: ስንቆርብ አይተውን ሰዎች ቢያመሰግኑን ምስጋናውን ይገባናል ብለን በልባችን እስካልተቀበልነው ድረስ ከንቱ ውዳሴ አይሆንብንም:: ከንቱ ውዳሴ የሚባለው ሰዎች ሲያመሰግኑን በልባችንም ምስጋናው ይገባናል ብለን ካሰብን ነው:: በመጽሐፈ መነኮሳት

"መጽውቶ የሚመሰገን ሰውን ውዳሴ ከንቱ አይጎዳውም:: ውዳሴ ከንቱ ደስ ቢያሰኘው ግን ያለምንዳ (ደመዎዝ) የሚሠራ ገበሬን ይመስላል" ተብሎ እንደተገለጸ (አረ.መን.1)::

፳፩. ከአሕዛብ ጋር ማዕድ በመሳተፌ የንስሓ አባቴ የቄደር ጥምቀት በሚል አጥምቀውኛል:: ይህ ትክክል ነው?

መልስ፦ ትክክል አይደለም:: ቄደር ከሚያስፈልግባቸው ምክንያቶች መካከል በፍትሐ ነገሥት የተገለጸው "እመቦ ብእሲ ምእመን ዘይተሉ ብእሲተ እንተ ኢተአምን አው ብእሲት ማእምንት ዘትተሉ ብእሴ ዘኢየአምን በምክንያተ ዝሙት፤ በዝሙት ምክንያት ካላመነች ሴት የደረሰ ሰው ቢኖር ወይም ካላመነ ወንድ የደረሰች ሴት ብትኖር እና ሃይማኖቱን ቀይሮ የነበረ ሰው ወደ ሃይማኖት ሲመለሱና ንስሓ ሲገቡ ቄደር ይጠመቃሉ" ተብሏል (አንቀጽ 48):: ከዚህ ውጭ ከላይ በጥያቄው የተጠቀሰው ጉዳይና የመሳሰሉት የቄደር ጥምቀት አያስፈልጋቸውም::

፳፪. አሁን የልጆች አስተዳደግ አስፈሪ እየሆነ መጣ ለማሳደግ፣ ለትምህርት፣ ለተለያዩ ወጭዎች እየከበዱ መጡ:: ወልደን ሲቸገሩ አቅማችን እየደከመ አልፎ ኑሮ አልሞላ ሲል እንዲህ ሲሆኑ ከማየት ራስን ወደ ማጥፋት እየተሔደ ነው:: የወሊድ መቆጣጠሪያ እንዳይጠቀሙ ኃጢአት ነው:: ምን ቢደረግ ይመረጣል? ከዚህ ጋር ደግሞ ክኒን ከመጠቀም Biological method እርግዝና በማይፈጠር ጊዜ ቢሆን ኃጢአት ይሆናል ወይ?

መልስ፦ በመሠረቱ የሰውን ልጅ የሚመግብ ዋና መጋቢ እግዚአብሔር ነው:: ስለዚህ በእግዚአብሔር መጋቢነት ላይ ጥርጣሬን በማምጣት ወልጄ ማሳደግ ከሚያቅተኝ ባልወልደው ይሻላል ብሎ የወሊድ መቆጣጠሪያ መጠቀም አይገባም:: በእርግጥ ለችግራችን ብዙ መንሥኤዎችን መጥቀስ እንችል ይሆናል ፖለቲካው ሰዋዊ (ሰው ተኮር) አለመሆኑ እንዲህ ዓይነት ስሜት ውስጥ ከትቶናል:: የሆነ ሆኖ ጋብቻ ከተመሠረተባቸው ምክንያቶች አንዱ መውለድ ነው:: ስለዚህ ላለመውለድ በስሌት ተፈጥሯዊ መንገድን (Biological Method) መጠቀም ራሱም በደል ነው:: ይህ ግንኙነቱን እወዳለሁ፣ ልጅ አልወድም ማለት ነውና:: መጻሕፍት ግንኙነትን ከሚከለክልባቸው ምክንያቶች ውጭ ማለትም (ቅዳሜ፣ እሑድ፣ ዓርብ፣ ረቡዕ፣ ሰሙነ ሕማማት፣ እርግዝና፣ አራስነት፣ የወር አበባ) ውጭ አንዱ ቢፈልግ ሌላው መከልከል የለበትምና::

፳፫. አንዲት ሴት ከቆረበች በኋላ ድንገት (ያለጊዜው) በተቀበለችበት ቀን የወር አበባ ከፈሰሳት ምን ማድረግ አለባት?

መልስ፦ አንዳንድ ጊዜ በተለያዩ ምክንያቶች ከቆረቡ በኋላ ማስመለስ፣ የወር አበባ በድንገት መምጣት፣ መድማትና የመሳሰሉ ችግሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ:: በዚህ ጊዜ ጊዜ በንጹሕ ጨርቅ ተቀብለን ወይም አሻሽተን በማግሥቱ (ከ24፡00 ሰዓት በኋላ) ያንን

ያሻሸንበትን ትውኪያ ወይም ደም የነካውን ልብስ አጥበን ማቃጠል፡፡ ከዚያ ያጠብንበትን ውሃና የተቃጠለውን ጨርቅ አመድ ቀላቅለን ከፈሳሽ ወንዝ መጣል ነው፡፡ ይህም በመጽሐፈ መነኰሳት ተገልጿል (ፊልክስዩስ ተስእሎ 10)፡፡

**፳፬. ሐዲስ ኪዳን የሚጀምረው ከየት ነው?ሐዲስ ኪዳን የሚጀምረው ክርስቶስ ከተሰቀለ በኋላ ነው?**

መልስ፦ ሐዲስ ኪዳን የሚጀምረው ከክርስቶስ ፅንሰት ጀምሮ ነው፡፡ ክርስቶስ የተፀነሰው መጋቢት 29 ቀን ነው፡፡ ዕለተ ጠቢባን የተባሉትን ራሱን 29 እና 30ን አልፈን የምናገኘው ወር ሚያዝያ 1 ነው፡፡ ሚያዝያ 1 የሚውልበት ቀንና መስከረም 1 የሚውልበት ቀን ተመሳሳይ በመሆኑ በሀገራችን ከመስከረም ጀምሮ ሐዲስ ኪዳን ከገባ 2018 ዓመት ሆኗል እንላለን፡፡ ሐዲስ ኪዳን በአንድ ቀን የተሠራች ሳይሆን ከክርስቶስ ፅንሰት ጀምሮ እስከ ጰራቅሊጦስ ባለው የተሠራች ናት፡፡ ስለዚህ የሐዲስ ኪዳን መሥዋዕቱ በጸሎተ ኀሙስ፣ ትምህርቱ ክርስቶስ ማስተማር ከጀመረበት ጀምሮ፣ የሐዲስ ኪዳን ልጅነት ወይም ሐዲስ ተፈጥሮ ደግሞ በፅንሰቱ እርሱ በባሕርዩ ሆኖ ጀምሮልናል፡፡ ስለዚህ የጀመረ ከፅንሰቱ ነው፡፡

**፳፭. ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው ይላል፡፡ ወልድ በተለየ አካሉ ሰው ከሆነ በኋላ በዕለተ ዓርብ የቀረሰው ሥጋ እና ደም ነው፡፡ ኢአማንያን የሰው ሥጋና ደም ትበላላችሁ ትጠጣላችሁ ሲሉ ይሰማል፡፡ ይህ እንዴት ይታያል?**

መልስ፦ ኢአማንያን ያልተረዱት ነገር ቢኖር ዓለማትን የፈጠረ ጌታ፣ እነርሱን ራሳቸውንም የፈጠራቸው ጌታ ሰውን ሁሉ ለማዳን እግዚአብሔርነቱን ሳይለቅ ሰው መሆኑን ነው፡፡ የክርስቶስ ሥጋ አምላክ የሆነና አምላክነትን በተዋሕዶ ገንዘብ ያደረገ ሥጋ ነው፡፡ ይህ ሥጋ ደግሞ ሕይወትን የሚሰጥ ሥጋ እንጂ እንደሌሎች ፍጡራን ሥጋ አይደለም፡፡ የእኔን ሥጋ ብትበሉ ሕይወት ታገኛላችሁ ስላለን ሥጋውን እንበላለን ደሙን እንጠጣለን፡፡ "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው" እንዲል (ዮሐ.6፥54)፡፡ ስለዚህ እኛ ክርስቲያኖች በራሱ በፈጣሪያችን ትእዛዝ መሠረት የክርስቶስን ሥጋና ደም ብቻ እንበላለን እንጠጣለን እንጂ የሌላ ሰውን ሥጋና ደም አንበላም፡፡ የምንበላው አምላክም ሰውም የሆነውን የክርስቶስን ሥጋ ነው፡፡

**፳፮. በዋዜማ ዕለት ዋዜማው እንዳለቀ ምግብ ይበላል፡፡ ከዚያ ወዲያውኑ ማሕሌት ይጀመራል፡፡ ይሄ እንዴት ነው? አንድ በዕለቱ የማይቆርብ ሰው ከበላ በኋላ ሰዓታትን ማሕሌትን ለመቆም ኪዳን ለማስደረስ ከበላ ከስንት ሰዓት በኋላ ነው ይሄን የሚያደርግ?**

መልስ፦ የማይቆርብ ከሆነ ማሕሌትን፣ ሰዓታትን፣ ኪዳንን፣ ስብከትንና የመሳሰሉትን ነገሮች በቤተክርስቲያን ለማድረግ በልቶም መግባት ይችላል፡፡ የሚቆርብ ሰው ግን 18፡00 ሰዓት ጹሞ መግባትና መቊረብ ይገባዋል፡፡

፷፲. አንድ ሕመምተኛ ክኒን ውጦ ወዲያውኑ ቤተክርስቲያን ገብቶ ከምሥጢራት ሳይሳተፍ ማስቀደስ ይችላል?

መልስ፦ ማስቀደስ ብቻ ከሆነ አዎ ይችላል። የሚቆርብ ከሆነ ግን ክኒን መዋጥም ጾም ስለሚያስገድፍ 18:00 ሰዓት ሳይሞላው መቊረብ የለበትም።

፷፰. ድኅረ ቁርባን እጅን አለመታጠብ፣ አለመራቆት ለምን ያህል ሰዓታት?

መልስ፦ ከቆረብን በኋላ አለመታጠብ፣ አለመራቆትና በጠቅላላ የቆረበ ሰው ሊያደርጋቸው የሚገቡ ጥንቃቄዎች ለአንድ ቀን (ለ24:00 ሰዓታት) ያህል የሚተገበሩ ናቸው። ለፍጹማን ግን እስከ ዕለተ ሞታቸውም ይህ ይቀጥላል። አባ መቃራ እለእስክንድራዊ ስለክብረ ቁርባን ከተጠመቀ ጀምሮ ለስልሳ ዓመት ምራቁን አልተፋም እንደተባለ (ፊልክስዩስ ተስእሎ 10)።

፷፱. በቤተ ክርስቲያን የሥነ ፍጥረት ትምህርት ሕዋ (Univers) ወሰን አለው? ከዚያ በኋላ ምን ይባላል?

መልስ፦ አዎ ሳይንሱ ሕዋ (Universe) የሚለው ነገር ፍጥረት ነው። ፍጥረታት ደግሞ ምንም ያህል ግዙፋን ቢሆኑ ወሰን አለባቸው። ፍጥረታትን ወስኗቸው የሚኖር እግዚአብሔር ነው። ከሕዋ በኋላ ያለው ማን ነው ከተባለ በሕዋ ውስጥም ከዚያ በኋላም የሚኖር እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ግን ወሰን የሌለበት ነው (ሃይ.አበ.124፥20)።

፸. በኢትዮጵያ ምስጢራት የተጀመሩት በአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው ይላሉ የታሪክ ሊቃውንቱ። በሌላ በኩል ክርስትና ኢትዮጵያ የገባው በ34 ዓ.ም በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ነው ይባላል። አይጋጭም ወይ? ካለ ምስጢራት ማለትም ያለ ሥጋና ወደሙ 300 ዓመት ቆይተናል ማለት ነው?

መልስ፦ ይህ ታሪክ ነው። ታሪክ ደግሞ በተገኙ ማስረጃዎች መሠረትነት የሚነገር ነው። የሆነ ሆኖ በዚያ ሦስት መቶ ዓመታት ውስጥ ምሥጢራት ይፈጸሙ ወይም አይፈጸሙ እስካሁን የተገኘ ምንም ማስረጃ የለም። ስለዚህ ምንም በሌለበት ምንም ማለት አይቻልም። ገድለ አቡነ ሰላማ ላይ እንደተገለጸው ደግሞ አቡነ ሰላማ የኢትዮጵያን ሰዎች "እምነት ብክሙ ጥምቀትሰ ወነሚአ ቊርባን አልብክሙ፤ እምነት አላችሁ ጥምቀትና ቁርባን ግን የላችሁም" እንዳሏቸው ተገልጿል። በዘመኑ ይህ አልነበረም። ገድለ አቡነ ሰላማ የዘመኑን ተናግሯል እንጂ የባለፈውን የ300 ዓመት ሁኔታ አልገለጸም። ይህም አያስጨንቀንም። ትልቁ ቁም ነገር አሁን እኛ ጥምቀትም፣ ቊርባንም እንዳለን ማወቁ ነው።

፸፩. ሕልመ ሌሊት ኃጢአት ነው ወይስ አይደለም?

መልስ፦ ሕልመ ሌሊት በራሱ ኀጢአት አይደለም። ሆን ብለን ሕልመ ሌሊት እንዲፈስሰን የተለያዩ ድርጊቶችን ማድረግ ግን ኀጢአት ነው። ሕልመ ሌሊት በድካም ብዛት ሳይታወቅ ሆኖ የሚገኝበት ጊዜ አለ። በዚህ ጊዜ በደል አይሆንም (መጽሐፈ ሐዊ ባህል 12)። ቀን ሲያስቡ ውለው ማታ በሕልም ግንኙነት ያደረጉ እየመሰላቸው ዝንየት ቢያገኛቸው ግን በደል ኃጢአት ይሆናል።

፴፪. አዋላጅ አይደለሁም ማዋለጃ ክፍል ገብቻለሁ። ወዲያውኑ የተወለደውን ሕፃንም እናትየዋንም ነክቻለሁ። እና ከቤተክርስቲያን ታጥቤ መግባት እችላለሁ ወይስ እንዴት ነው? ከአዋላጅ ውጭ ያሉ ጤና ባለሙያዎች ከእናትየዋ እና ከሕፃኑ ጋር ቢነካኩና ፈሳሽ ቢነካቸዉ ከማዋለጃ ክፍሉ ቢወሉ ታጥበው መግባት ይችላሉ?

መልስ፦ ፍትሐ ነገሥት ለአዋላጆች ብቻ ሕግ ሲሠራ ስለሌሎች ያለው ነገር የለም። ሌሎች ሰዎች ሊጠይቁ ሄደው የወለደችዋን ሴትና ልጇን ቢነኩ ቤተክርስቲያን ከመግባት አይከለከሉም። የካህን ሚስት ብትወልድ ካህኑን ከአገልግሎት አይከልክሉት የሚለው ለዚህ ፍንጭ ይሆናል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 6)። ደም ስለነኩ ሰዎች ግን ከአዋላጆች ውጭ ስላለው የተጻፈ አላገኘሁም። መምህራን ግን ታጥቦ መግባት ይቻላል እያሉ ይናገራሉ። [ይህን መሰል ነገሮች እንደ አዲስ በቅዱስ ሲኖዶስ ቢተረጎሙና ተያያዥ ጉዳዮችም ቢገለጹ ብዬ recommend አድርጋለሁ]።

፴፫. በዕለተ ምጽአት ሰማይና ምድር ሲያልፉ የሚያልፉት እና የማያልፉ ሰማዮች አሉ?

መልስ፦ በዚህ ዙሪያ በሊቃውንት ዘንድ ሦስት እይታዎች አሉ። አንደኛ ሰማይና ምድር ያልፋሉ ያለው ይህ የሚታየው ሰማይና ያለንባት መሬት ያልፋሉ። ነገር ግን የመላእክት ከተሞች ኤረር፣ ራማ፣ ኢዮርና በጠቅላላው ሰባቱ ሰማያት አያልፉም የሚሉ ናቸው። 2ኛ ጴጥ.3፥12 ላይ "ሰማያት ይረስና ወይትመሰዋ፤ ሰማያት ተቃጥለው ይቀልጣሉ" ከሚለው ሰማያት ያላቸው የምናየው ሰማይ እና ቀጥሎ ያለውን ሐኖስን የሚያመለክት ነው እንጂ "ሰማያት" ብሎ ያበዛው ሌሎችን ሰማያት የሚያመለክት አይደለም ይላሉ። ሁለተኛ የመላእክት ሰማያትም ያልፋሉ የሚሉና መንግሥተ ሰማያት ብቻ ትቀራለች ሰውና መላእክት በአንድ ላይ ይኖሩባታል የሚሉ ናቸው። ሦስተኛው መንግሥተ ሰማያት የተባለ ራሱ ክርስቶስ ስለሆነ የሚቀር ምንም ነገር የለም የሚሉ ናቸው። እነዚህ ሁሉም እይታዎች ናቸው። እይታ እንደ እይታ ይከበራል። እውነታውን የምናውቀው ግን ያን ጊዜ የምጽአት ጊዜ ነው።

፴፬. በማዕድ ጊዜ ምዕመናን/ሕዝባውያን በእንተ ማርያም፣ በእንተ ኢየሱስ ብለው ቡራኬ መስጠት ይችላሉ ወይ? ለምንስ በእንተ ማርያም ቀደመ?

መልስ፦ በማዕድ ጊዜ ባል ለሚስት ቆርሶ መስጠት የተለመደ ባህል ነው። እንደ ባህል የሚታይ እንጂ ከሃይማኖት ጋር የሚያያዝ ነገር የለውም። ስለዚህ ቢያደርጉም በደል

አይሆንም ባያደርጉም ኃጢአት አይሆንም። ወደ ቤተክርስቲያን የመጣውን የበረከት ኅብስት ግን ኤጲስ ቆጶስ ቢኖር ኤጲስ ቆጶስ እንዲቆርስ፣ ኤጲስ ቆጶስ ባይኖር ቄስ እንዲቆርስ፣ ቄስ ባይኖር ዲያቆን እንዲቆርስ ሥርዓት ከተሠራ በኋላ ክህነት የሌለው ጨዋ ግን እንዳይቆርስ ሥርዓት ተሠርቷል። "ወለሕዝባዊሰ ኢይደልዎ ከመ ይግበር ወየሀብ አውሎግያ" እንዲል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 11)። በእንተ ማርያም፣ በእንተ ኢየሱስ ወይም በእንተ ኢየሱስ፣ በእንተ ማርያም ተብሎ ቢጀመር ምንም ችግር የለውም። መቀዳደሙ ክብርን ወይም መበላለጥን የሚያመለክት እስካልሆነ ድረስ ምንም ችግር የለውም። በእንተ ማርያም ማለት ስለማርያም ማለት ነው ይህም በወዳጆቹ ስም የሰጠ ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። ምንም እንኳ ይህ ለዝክር ቢነገርም 'የሰጠ' ማለቱ ከዝክር ባለፈም ያስተረጉማልና። "ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውሃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ፥ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም" እንዲል (ማቴ.10፥42)። በእንተ ኢየሱስ ማለታችንም ወንጌልን መሠረት በማድረግ ነው። "የክርስቶስ ስለ ሆናችሁ በስሜ ጽዋዕ ውሃ የሚያጠጣችሁ ሁሉ ዋጋው እንዳይጠፋበት እውነት እላችኋለሁ" እንዲል (ማር.9፥14)። ምሥጢሩ ግን ጌታ 5500 ሰዎችን ሲያጠግብ እርሱ ለሐዋርያት፣ ሐዋርያት ለሕዝቡ የመስጠታቸው ምሳሌ ነው። "ሕዝቡም በሣር ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ። አምስቱንም እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ይዞ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየና ባረከ። እንጀራውንም ቆርሶ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ። ደቀ መዛሙርቱም ለሕዝቡ" እንዲል (ማቴ.14፥19)።

**፴፫. "ቶ" መስቀል ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አስተምህሮ አንጻር እንዴት ይታያል?**

መልስ፦ "ቶ" የሚባል የመስቀል ዓይነት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የለም።

**፴፬. ሥርዓተ ቅዳሴ ከምግብ በፊት መሆን አለበት ብለው ያስተማሩ የጥንት የቤተክርስቲያን አባቶች አሉ ወይ?**

መልስ፦ አዎ አሉ። የሥርዓተ ቅዳሴ መከናዎን በዋናነት የክርስቶስን ሥጋና ደም ማዕከል አድርጎ የሚከናዎን ነው። ሥጋውን ደሙን የሚቀበል ሰው ደግሞ በንጹሕ ጾሞ ይቀበል ብለው ሠለስቱ ምእት በፍትሐ ነገሥት ገልጸዋል። "ወኢይንሣእ መኑሂ ቍርባነ ዘእንበለ ይጹም በንጹሕ" እንዲል (አንቀጽ 13)

**፴፭. በዕለተ እሑድ ከቅዳሴ በኋላ ለምዕመናን የሚሰጠው መክለፍት /ቂጣ/ ታሪካዊ አመጣጡ ምንድን ነው? ስንበላስ የምንሸፋፈንበት ምክንያት ምንድን ነው?**

መልስ፦ መነሻ ታሪኩ መቼ እንደጀመረ አላውቀውም። ነገር ግን ከጥንት ጀምሮ የነበረ እንደሆነ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 11 የበረከት ኅብስት ብሎ በመግለጹ ማወቅ

እንችላለን:: ስትበሉ ተሸፋፈኑ የሚል እንኳ አላገኘሁም:: እንደ ልማዱ ተሸፋፍኖ የሚበላ አለ፣ ተገልጦ የሚበላ አለ::

፴፰. በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት በዐቢይ ጾም ማንኛውም በዓላት እንዳይከበሩ እና ታቦት እንዳይወጣ ይከለከላል:: በዕለቱም ፈንታ በሌላ ተለዋጭ ቀኖች እንዲከበሩ ይነገራል:: ለምሳሌ መጋቢት አቦ ወደ ጥቅምት አቦ፣ መጋቢት መድኃኔዓለም ወደ ጥቅምት 27:: አሁን ላይ ባለው ተግባር ግን በሁለቱም ቀናት በዓላት ይደረጋሉ:: አንዱ ቀን መተው አልነበረበትም ወይ? እና አንዱ ቀን የአንዱ ልዋጭ ከሆነ በሁለቱም ቀናት የሚቆመው ማሕሌት ለምን አንድ ዓይነት አልሆነም?

መልስ፦ በመሠረቱ በዐቢይ ጾም ማንኛውም በዓላት እንዳይከበሩ የሚል ሥርዓት የለም:: ስለዚህ ጥያቄው ራሱ የተሳሳተ ነው:: ያልተባለውን እንደተባለ አስመስሎ ያንኑ መሠረት አድርጎ ይጠይቃልና:: መከበር እንደሚችል ማስረጃው ከጌታ ንኡሳት በዓላት አንዱ መጋቢት 10 መስቀል ነው ተብሎ በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 19 መገለጹ ነው:: መጋቢት 10 ደግሞ ሁልጊዜም በዐቢይ ጾም መካከል የሚገኝ በዓል ነው:: ፍትሐ ነገሥት የሚለው ከሰኞ እስከ ዓርብ የሚውል ከሆነ ሰው ከበዓሉ ተገኝቶ በረከትን እንዲያገኝ ወይ ወደፊት ባለው እሑድ ወይም ወደኋላ ባለው እሑድ አክብሩ ብሎ ነው:: የመጋቢት 27ቱ በዓል አይደለም ወደ ጥቅምት 27 የመጣው:: ጥቅምት 27 ራሱን የቻለ ታሪክ ያለው በመሆኑ ነው እንጂ:: ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎች ከተሳሳተው አባባል የመነጩ በመሆናቸው ልለፋቸው::

፴፱. ሰው በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል ነው የተፈጠረው ይባላል:: ነገር ግን አካለ ጎደሎ ቢወለድ በማን አምሳል ነው የምንለው? ይህ የሚከሠተው በምን ምክንያት ነው?

መልስ፦ ሰው እግዚአብሔርን ይመስላል የሚባለው አንደኛ በነፍሱ ነው:: ነፍስ ለባዊ፣ ነባቢ፣ ሕያው እንደሆነች እግዚአብሔርም ሕያው፣ ለባዊ፣ ነባቢ ነውና:: ስለዚህ ማንኛውም ሰው አካለ ጎደሎ ሆኖ ቢፈጠርም በነፍሱ አካለ ጎደሎ ስለማይሆን እግዚአብሔርን ይመስላል ተብሏል:: አካለ ጎደሎነት የሚከሠተው የእግዚአብሔር ተአምር ይገለጽ ዘንድ ነው:: "ደቀ መዛሙርቱም "መምህር ሆይ ይህ ሰው ዕውር ሆኖ እንዲወለድ ኃጢአት የሠራ ማን ነው? እርሱ ወይስ ወላጆቹ?" ብለው ጠየቁት:: ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰ የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ እንዲገለጥ ነው እንጂ እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢአት አልሠሩም" እንዲል (ዮሐ.9፥2-3)::

፵. አንዱ የተቸገርንበት ነገር ቢኖር ፈዋሽ ጸበል በፈለቀ ቁጥር የዘመኑ አጥማቂያን ናቸዉ አትሂዱ ሲባል ግራ መጋባት ነው:: እኛ ግን ብንሄድም አዳኝም ሆነ ፈዋሽም ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን አምነን ነው:: ስለዚህ ምንም ጠንቋይ ቢሆኑ እኛ ፈውስ እናግኝ እንጂ ምን ችግር አለው?

መልስ፦ ከእግዚአብሔር ሕግ ተቃራኒ የሆኑ ሰዎች ላይ ምንም ፈውስ ብናገኝ መሄድ እንደማይገባንና ከክፉዎች ከመፈወስ ታሞ መሞት እንደሚሻል መጻሕፍት ይናገራሉ (ሃይ.አበ.20፥15)። ሲጀምር ጌታ እንደተናገረው ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክትን ይሻል እንዳለው ሆኖብን እንጂ ቤተክርስቲያን አንዲት እስከሆነች ከቤተክርስቲያን ከሚሰጠን ጠበል የበለጠ ሌላ ጠበልኮ የለም። የቤተክርስቲያንን አንድነት እንዳንረዳ ሰይጣን ያመጣው ፈተና ነው። በነገራችን ላይ እርሱ ያለባት ቤተክርስቲያን መፍትሔ የሌላት ይመስል አዲስ ጠበል ፈለቀ በተባለ ቁጥር የሚንከራተተው ሰው የድንቁ*/ርናው ጥግ ያሳዝናል። እንዲህ ያለ በቅዱሳን ስም የሚመጣ አጭበርባሪነት ጥሩ ስላልሆነ የመስከረም 14 ስንክሳር ላይ አንዲት ሴት በቅዱስ ሚናስ ስም ጠበል አስቆፍራ ነበር። ነገር ግን ምንም እንኳ በታላቁ በቅዱስ ሚናስ ስም የወጣ ቢሆንም አባ አጋቶን ጠበሉ እንዲደፈን አድርጓል። መጽሐፈ ሐዊ ባህል 47 ላይም "ሠናይ ውእቱ ከመ ንሙት እምንፍቅድ ፈውሰ እምነ አጽራሪሁ ለእግዚአብሔር" ይላል። ይህም ማለት የእግዚአብሔር ጠላቶች ከሆኑ ከጠንቋዮች ፈውስን ከምንፈልግ መሞት ይሻለናል ማለት ነው።

፵፩. በኦርቶዶክስ እምነት ጥቁር ልብስ መልበስ አይፈቀድም ይባላል። ሰው የሚለብሰው በባህል ነው የሚሉም አሉ። ቤተክርስቲያን ምን ትላለች?

መልስ፦ በሃይማኖት በኀዘን ጊዜ ጥቁር ልበሱ አልተባለም። በባህል ግን በሀገራችን ያዘነ ሰው ኀዘኑን ለመግለጽ ጥቁር ይለብሳል። ይህ ደግሞ ለሌላው ማኅበረሰብ ኀዘን ላይ መሆኑን መግለጫ መንገድ ነው። ስለዚህ ይህ እንደ ባህል የሚታይ እንጂ ሃይማኖት አይደለም። ስለዚህ የለበሰውንም አንነቅፍም ያልለበሰውንም ለምን አልለበስክም ብለን አንነቅፍም። በቀቢጸ ተስፋ ሆኖ ትንሣኤ ሙታን የለም ብሎ ማልቀስን፣ ፊትን መንጨትን፣ ጸጕርን መላጨትንና የመሳሰለውን ግን ሃይማኖት ይከለክላል (ተግሣጸ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ 4)። ከሞት በኋላ ትንሣኤ መኖሩን አውቀው ሞት እንጂ ለጻድቃን ዕረፍት ነው ብለው ነጭ ለብሰው የሚውሉም ይኖራሉ። ነጭ መልበስ ትእምርተ ፍሥሓ (የደስታ ምልክት) ነውና። በባህል ልብሰ ኀዘን፣ ልብሰ መርዓ፣ ልብሰ መንግሥት የሚባሉ አሉ (መጽሐፈ ተግሣጽ 3፥ 13 ትርጓሜ)። ሕዝ.7፥18 ትርጓሜ ላይም ወይቀንቱ ሠቀ፤ ጨርቅ ይለብሳሉ ማቅ ያሸርጣሉ ብሎ ትእምርተ ኀዘን ትእምርተ ወይሌ ይላል። በእስራኤል በተጨማሪ ልብስን መቅደድ፣ አመድ መነስነስ የኀዘን ምልክት ነው። በሀገራችን ደግሞ ሰው ሲሞት ጥቁር መልበስ፣ የነጠላን ዘርፍ ዘቅዝቆ መልበስ ማንንም የማይጎዳ ባህል ነው። ይህ ሁሉ ሲሆን ተስፋ ትንሣኤን ግን ሁልጊዜም በልብ ማሰብ ይገባል።

፵፪. የአንድ ማኅበር አገልጋዮች እርስ በርስ መጋባት ይችላሉ?

መልስ፦ ጋብቻን የሚከለክሉ ዝምድናዎች የጋብቻ ዝምድና፣ የክርስትና አባት እናት ዝምድና፣ የሥጋ ዝምድና፣ የአሳዳጊ እናት አባት ዝምድና ናቸው:: ከእነዚህ ውጭ በአንድ ማኅበር የነበሩ አባላት ቢጋቡ ምንም ችግር የለውም::

፵፫. ኢየሱስ በሥጋ በነበረበት ወቅት በአካል አንድ ቦታ ሆኖ በሌላ ቦታ የተደረገውን መናገሩ እና ኤልሳዕ አንድ ቦታ ሆኖ በሌላ ቦታ የተደረገውን ከማወቁ (ሑሰት ከሚለው የቅድስና ደረጃ ) በምን ይለያያል?

መልስ፦ ፈጽሞ ይለያያል:: ኤልሳዕ ከአንድ ቦታ ሆኖ እርሱ ካልነበረበት ቦታ የነበረውን በእግዚአብሔር ገላጭነት በጸጋ አውቋል:: ክርስቶስ ከሁሉም ቦታ ያለውን ማወቅ የቻለው በሁሉ ቦታ ያለ በመሆኑና በባሕርዩም ሁሉን ማወቅ የሚችል ስለሆነ ነው::

፵፬. ከዓመተ ምሕረት በፊት 5500 ዓመት ተብሎ የሚቆጠረው ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ነው ወይስ አዳም ዕፀ በለስን በልቶ ከተረገመ ሰዓት ጀምሮ ነው?

መልስ፦ 5500 ዓመት የሚቆጠረው ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ነው:: ምንም እንኳ አዳም ለሰባት ዓመት በገነት ቢኖርም ከዚያ በኋላ ከገነት ወጥቷል:: ጌታም ከአምስት ቀን ተኩል በኋላ አድንሃለሁ ብሎታል:: ያች በገነት የኖረባት ሰባት ዓመትም አንድ ላይ ተቆጥራለች:: በዓመተ ፍዳ ተካትታ መቆጠሯ በበዛው መገለጺ ነው እንጂ በሰባቱ ዓመት ውስጥም አዳም በመከራ ውስጥ ነበረ ለማለት አይደለም::

፵፭. ዲያቆን ያልሆኑት ወንዶች በተክሊል ማግባት ይችላሉ?

መልስ፦ አዎ ይችላሉ:: የተክሊል መስፈርቱ ድንግል መሆን ነው እንጂ ዲያቆን መሆን ወይም አለመሆን አይደለምና::

፵፮. በኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን ፅንስ ማስወረድ ማቋረጥ እንደማይቻል፣ እንዲሁም የወሊድ መከላከያም እንደማይፈቀድ አውቃለሁ:: አንዱ የሰውን ልጅ መግደል ሲሆን አንዱ ደግሞ የሰው ልጅ እንዳይፈጠር እንዳያድግ መከላከል ነውና:: በዚህ ጉዳይ በተለይም በሕክምናው ዘርፍ ለምንሠራ ሰዎች ፈተና ሆኖብናል:: በኢትዮጵያ ሕግ ፅንስ ለማስወረድ የሚፈቀዱ ቅድመ መስፈርቶች አሉ:: (ምሳሌ፦ የተደፈረች ከሆነ፣ ከዘመድ ከሆነ...ወዘተ) እና የወሊድ መከላከያ ደግሞ የሚፈቀድ ነገር ነው:: እነዚህ ሁለቱም የአንድ ሕክምና ባለሙያ የሥራ ድርሻ እና ግዴታዎች ናቸው:: እነዚህን አልሠራም የሚል ባለሙያ ኃላፊነቱን አልተወጣም እንደማለት ነው:: ይህንን ጉዳይ እንዴት ከቤተክርስቲያኗ አስተምህሮ ጋር ማስታረቅ ይቻላል?

መልስ፦ በእውነቱ እንደዚህ ጥያቄ ያስጨነቀኝ የለም:: እንደዚህ ያለ System የፈጠራቸው ኃጢአቶች በዝተዋል:: ባለፈው አንዱ ከገቢዎችና ጉሙሩክ ጋር ተያያዥ የሆነ የሥራው ባሕርይ እስከመምሰል የደረሰ ጉዳይ ጠይቆኝ አልፌው ነበር:: በትክክለኛው መንገድ ብትሔዱ ሥራችሁን አደጋ ላይ የሚጥል አካሄድ ማለት ነው::

በእርግጥ ይህንን የፈጠረው የተበላሸ የአሠራር ሥርዓት (System) ነው። በጋራ ሆነን እንዳንታገል በዚህ ሲስተም በሥጋ ተጠቃሚ የሚሆኑ አካላት ተደራጅተው ሀገርንም ትውልድንም እየገደሉ ይኖራሉ። የሕክምናው ጉዳይ ላይ ፅንሱ እናቱን ይገድላል ተብሎ ቢታሰብ ማስወረድ ይቻላል ወይም ከላይ በተጠቀሱ ኬዞች የሕክምናው ሥነምግባር (Work ethics) ሊፈቅድ ይችል ይሆናል። በሃይማኖት ግን ፅንስን ማስወረድ በየትኛውም መንገድ አይፈቀድም። እንዲህ ዓይነት ነገሮች በቀኖና የሚፈቀዱበት ሁኔታ ካለ ቅዱስ ሲኖዶስ ጋር መክሮ ቀኖና ቢዘጋጅ መልካም ይሆናል። አንደኛ ተጠያቂዎች ፅንሱ እንዲወርድ የጠየቁ አካላት ናቸው። ዶክተሩ በተሻለ ሙያዊ ድጋፍ የሚከናወንበትን መንገድ ነው የፈጸመው። ሆኖም ግን የተሠራ ቀኖና ስላላየሁ ዶክተሩም ልክ ነው አልልም። ከዘመድ የተፀነሰ እንኳ መውለድ እንጂ ማስወረድ አልተፈቀደም። የሎጥ ልጆች ከአባታቸው ፀነሱ ተብሎ ፅንሳቸው አልወረደም። ኀጢአትነቱ ተነግሮ ያልፋል እንጂ በመግደል ሁለተኛ ኀጢአት አይሠራም።

፵፮. ደቂቀ እስጢፋኖስን አንዳንድ ሰዎች መናፍ*ቃን ናቸው ይላሉ። ይሄ ነገር እንዴት ነው?

መልስ፦ ደቂቀ እስጢፋኖስን በተመለከተ ሁለት እይታዎች አሉ። አንደኛ ከቤተክርስቲያን አስተምህሮ ተቃራኒ ናቸው ለቅዱሳን፣ ለመስቀል ስግደት አይገባም የሚሉ ናቸው። አባ ጽጌ ድንግልም በማሕሌተ ጽጌ "ዘሰ ይብል አፈቅረኪ ወኢያፈቅር ተአምረኪ ክርስቲያናዊ፣ ኢክርስቱን ውእቱ አይሁዳዊ፣ ወሠርፀ እስጢፋ ሐሳዊ" ብለውታል። አንደኛዎቹ ደግሞ ያልሰገዱ ለንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ ነው እንጂ ለቅዱሳን አንሰግድም አላሉም የሚሉ ናቸው። የሆነ ሆኖ ከላይ እንደተባለው ለቅዱሳን የጸጋ ክብር የጸጋ ስግደት አያስፈልግም ብለው ከነበረ መና*ፍቅ ያሰኛቸዋል። ካላሉ ደግሞ ራሱ እግዚአብሔር ያውቃል። [በዚህ ዙሪያ በአማን ነጸረ ያዘጋጁትን ወልታ ጽድቅ መጽሐፍ ይመልከቱ]።

፵፯. በእደ ገብሩ ካህን ማለት ያለበት ሊቀ ዲያቆኑ ግን አንዳንድ ደብር ላይ የደብሩ አስተዳዳሪ አብሮ ካለ በእደ ገብሩ መምህር ይላሉ። እንዴት ያዩታል ይህን?

መልስ፦ በእርግጥ ይህ እንደ ትልቅ ጉዳይ የሚቀርብ አይደለም። መጽሐፈ ቅዳሴው በእደ ገብሩ ካህን ይላል። ካህን የሚለው ስም ለቀሳውስትም፣ ለቆሞሳትም፣ ለጳጳሳትም መጠሪያ ያገለግላል። ስለዚህ በእደ ገብሩ ካህን ስንል ቀዳሹ ጳጳስ ከሆነ ጳጳሱን የሚያመለክት ሲሆን ቄስ ከሆነ ቄሱን የሚያመለክት ነው። ስለዚህ በተጻፈው ቢባል መልካም ነው። ለይቶ በእደ ገብሩ ጳጳስ ቢልም የሚቀይረው ምሥጢር ስለማይኖር ምንም ችግር የለውም። ነገር ግን ጳጳሱ ለከንቱ ውዳሴ ፈልጎት በእደ ገብሩ ካህን ሳይሆን በእደ ገብረ ጳጳስ በሉኝ ካለ መነሻ ሐሳቡ (His motive) ከንቱ ውዳሴ በመሆኑ ነውር ይሆናል። እንዲህ ያለውን ሊቃውንት ይቃወሙታል መቃወማቸውም ተገቢ

ነው። ዙሮ ዙሮ ቄስም ይቀድስ፣ ጳጳስም ይቀድስ በቅዳሴው የምናገኘው በረከትና ጸጋ ግን አንድ ነው እንጂ ልዩነት የለውም።

፵፱. አንድ ዲ/ን ሚስት ሊያገባ ታጭቶለት ሳለ በአቋራጭ ሰርጉ ቢቀር በኋላ ሌላ ሚስት በተክሊል ማግባት ይችላል?

መልስ፦ እጮኝነት በብዙ ምክንያት ሊፈርስ ይችላል። ለዚያም ነው በእጮኝነት ጊዜ መሳሳምም፣ ግንኙነትም ፈጽሞ የማይፈቀደው። በእጮኝነት ጊዜ ምንም ዓይነት ጾታዊ ግንኙነት ሳያደርጉ በልዩ ልዩ ምክንያት እጮኝነቱ ቢፈርስ ዲያቆን ሌላ አጭቶ ሊያገባ ይችላል።

፶. አንድ ሰው ከባልንጀራው ጋር ቢጣላ እና ይቅርታ ቢጠይቀው ያ ሰው ግን ይቅርታ አላደርግም ቢለው ይቅርታ ጠያቂው መቁረብ ይችላል?

መልስ፦ አዎ ከንስሓ አባቱ ጋር ተመካክሮ መቊረብ ይችላል። ክፉ ሰዎች ይቅርታ ተብለውም ይቅርታ ላያደርጉ ይችላሉ። በእነርሱ ክፋት ምክንያት ከክቡር ሥጋው ከክቡር ደሙ መራቅ አይገባም።

፶፩. አለመማር ኃጢአት ነው?

መልስ፦ አለመማር በራሱ ኃጢአት አይደለም። የእግዚአብሔርን ሕግ አለመፈጸም ግን ኃጢአት ነው። የእግዚአብሔርን ሕግ አለመፈጸምን በአለመማር ምክንያት ማሳበብ ግን አያድንም። አለማወቅ ከተጠያቂነት አያድንምና።

፶፪. መለኮትና ትስብእት ያደረጉት ተዋሕዶ ሥጋና ነፍስ ካላቸው ተዋሕዶ በምን ይለያል? ረቂቁ መለኮት ግዙፉን ሥጋ ከተዋሐደ በኋላ መለኮት ትስብእትነቱ ሳይጠፋ በተዘጋ ቤት ገብቷል። እኛ ደግሞ ረቂቅ ነፍሳችን ከግዙፉ ሥጋ ጋር ብትዋሐድም በነፍሳችን ርቀት በተዘጋ ቤት መግባት አንችልም። ለምን?

መልስ፦ የሥጋና የነፍስ ተዋሕዶ በሞት መለየት ያለበት እንደገና በምጽአት የሚዋሐድ ነው። የቃልና የሥጋ ተዋሕዶ ግን ከተዋሐዶ በኋላ መቼም መች መለየት [ፍልጠት] የሌለበት ነው። ሌላውና ዋናው ቁምነገር የሥጋና የነፍስ ተዋሕዶ ለቃልና ለሥጋ ተዋሕዶ መነገሩ በምሳሌ ዘየሐጽጽነት (ጎደሎ ምሳሌ) እንጂ ፍጹም ምሳሌ አይደለም። ስለዚህ ሥጋ በቃል ገንዘብ በተዘጋ ቤት ሲገባ የእኛ ሥጋ በነፍስ ገንዘብ በተዘጋ ቤት አይገባም።

፶፫. የሐዋርያት ጥምቀትን አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ዓርብ ነው የተጠመቁ የኀሙሱ ሕጽበተ እግር የትሕትና ነው ይላል። ባስልዮስ ደግሞ ኅርኅርዮስን ማእዜ ተጠምቁ አርድእት ብሎ ቢጠይቀው አመ ሐጸቦሙ እግዚእነ ተጠምቁ ይላል። እንዴት ይታረቃል?

መልስ፦ ሁለቱም ትክክል ነው። ሐዋርያት የተጠመቁ በዕለተ ኀሙስ ነው። የክርስቶስን ሥጋዉን ደሙን የተቀበሉትም በዕለተ ኀሙሰ ነው። ነገር ግን በዕለተ ኀሙስ የተጠመቁበት ውሃ በዕለተ ዓርብ ከጌታ ጎን የፈሰሰው ማየ ገቦ ነው። የተቀበሉት ደምም በዕለተ ዓርብ የፈሰሰውን ነው። የነገውን ዛሬ ሰጣቸው። በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ይቻላልና። በትርጓሜ "ካሣ ሳይፈጸም ልጅነት የለም" የሚለው የሐዋርያት ልጅነት በዕለተ ዓርብ በተፈጸመ ካሣ መደረጉን ነው (ሉቃ.12፥50 ትርጓሜ)። በዕለተ ዓርብ በተፈጸመ ካሣ መሠረት ቀድሞ ባለው በዕለተ ኀሙስ አጠመቃቸው ልጅነትንም ሰጣቸው። የዓርቡን ኀሙስ መስጠት የሚችል አምላክ ነውና።

፶፬. አንድ ሰው በተደጋጋሚ ንስሓ ቢገባ እና ጸሩ ባይለቀው ቀድሞ ከነበረው መምህረ ንስሓ ለመናገር ቢፈራ ከሌላ ካህን መግባት ይችላል?

መልስ፦ ሰው ከንስሓ አባቱ ውጭ ለሌላ ሰው ኃጢአቱን መናዘዝ የለበትም። የፈለገ ቢደጋግሙ ከዚያው ከንስሓ አባት መግባት እንጂ ከሌላ መግባት አይገባም። ኃጢአቱን ደጋግመን ስንሠራው ያላፈርን ደጋግሞ መናገሩ አስጨነቀን ተብሎ ሌላ ሰው ላይ ንስሓ መግባት አይገባም። ማፈርና መፍራት ያለብን ደጋግሞ ኃጢአት መሥራትን ነው እንጂ ደጋግሞ ንስሓ መግባትን አይደለም።

፶፭. አንድ ሰው ንስሓ ገብቶ ተሠርዮለት መልሶ ያንኑ ኃጢአት ቢሠራውና ንስሓ አባቱን ማናገር ቢከብደው በራሱ ንስሓ መግባት ይችላል?

መልስ፦ በራስ ንስሓ መግባት የሚባል ነገር የለም። የፈለገ ቢፈራና ቢያፍር መልሶ ለንስሓ አባቱ መናዘዝ አለበት። ኃጢአቱን ስንሠራው ነው ሊከብደን የሚገባ እንጂ መናዘዙ ሊከብደን አይገባም።

፶፮. አንዲት እኅት በሕፃንነቷ (በአንዳድ አካባቢዎች በልጅነት መዳር ባህል እንደሆነ ሁሉ) ቤተሰብ ያለእርሷ ፈቃድ ቢድሯትና ሁለቱም ሙሽሮች ገና ልጅ ከመሆናቸው የተነሳ ምንም ሳይገናኙ ቢቀሩና ቢለያዩና ግንኙነት ስላላደረጉ ብቻ ስታድግ በተክሊል ማግባት ትችላለች?

መልስ፦ የተጋቡት በተክሊል ከነበረ ምንም እንኳ ግንኙነት ባያደርጉም ከጋብቻ ስለሚቆጠር ሁለተኛ ለማግባት ተክሊል አይፈቀድም። በመዓስባን ሥርዓት ይጋባሉ እንጂ። የተጋቡት ያለሥርዓት ተክሊል ከነበረ ይህ መጀመሪያውንም ከጋብቻ ስለማይቆጠር ምንም ግንኙነት እስካላደረጉ ድረስ በኋላ በተክሊል ሊጋቡ ይችላሉ።

፶፯. በትዳር ውስጥ ያሉ ጥንዶች ቢኖሩና አንደኛው አካል በሥጋ ወደሙ መኖር የሚፈልግ ቢሆን ሌላኛው አካል ደግሞ ምንም ዓይነት የመቁረብ ፍላጎት ባይኖረው፥ ይልቁንም ሃይማኖት የለም ብሎ የሚያስብ ቢሆን፣ ምክረ ካህናትንም ለመስማት ምንም ፍላጎት ባይኖረው ለረጅም

ዓመታት ለምሳሌ ለ20 እና ለ30 ዓመታት ያክልም በዚህ ሐሳብ የጸና አካል ቢኖር፥ በቁርባን መኖር የሚፈልገው አካል ማድረግ ያለበት ምንድን ነው?

መልስ፦ ጋብቻ ከሚፈርስባቸው ምክንያቶች አንዱ ይህ ነው። ከሁለት አንዱ ሃይማኖቱን ቢለውጥ መፋታት ይቻላል። ሃይማኖት የለም የሚል ሰው ከሓዲ ነውና። ስለዚህ ነገሩን ከአባቶች ጋር መክሮ መፍትሔ መስጠት ይገባል።

፶፰. ብዙ ጊዜ በጠበል ቦታ ላይ ሴቶች ጠበል መክፈትም ሆነ መዝጋት አይችሉም ይባላል። ሴት ልጅ በራሷ ላይ እንኳ በምትበላው ምግብ ማማተብ አትችልም ይባላል። ይህ የቤተ ክርስቲያ ሥርዓት ነው?

መልስ፦ አይደለም። እንዲህ እንዲህ ያሉ ነገሮች ልማዶች እንጂ ሥርዓቶች አይደሉም። ሴት ልጅ የራሷን ጠበል ከፍታ መጠጣት ትችላለች። በምትበላው ምግብ ላይም ማማተብ ትችላለች። አማትቦ መብላት ለክርስቲያን ሁሉ የተፈቀደ ነው እንጂ ለወንድ ብቻ የተፈቀደ አይደለም።

፶፱. ምስጢር ያላየ ዲያቆን ዕጣነ ሞገር መቀኘት ይችላል ወይስ አይችልም?

መልስ፦ ቅኔ እግዚአብሔርን ማመስገኛ ነው። ይህንን ደግሞ በቤተክርስቲያን ለማቅረብ ክህነት ያላቸው ሰዎችም ያቀርባሉ። ክህነት የሌላቸው ሰዎችም ያቀርባሉ። ስለዚህ አይከለከልም። በትውፊት ስንመለከተውም ክህነታቸው የፈረሰ ቄሶች፣ መርጌቶች፣ ክህነት ሳልተሰጣቸው ዓይነ ሥውር ሊቃውንትና ለመሳሰለው ሲሰጥ ይስተዋላልና። አንዳንዶች ግን ቅኔ አድራጊ ስድስተኛ ቀዳሽ ማለት ስለሆነ ክህነት ላለው ብቻ ይሰጥ ይላሉ። ግን ስድስተኛ ቀዳሽ የሚለው ግላዊ አስተያየት እንጂ መጽሐፈ ቅዳሴ ላይ የለም።

፷. ሕፃናትን ቅባት ሃይማኖት በሚከተሉ አባቶች ማስቆረብ ይቻላል? እኛስ መሳለም እንችላለን?

መልስ፦ አይቻልም። የቅባት እምነትኮ ራሱን የቻለ ታላቅ ክሕደት ነው። ስለዚህ ከከሓድያን ማስቆረብ አይገባም። ከእነዚህ ከሓድያን መሳለምም አይገባም።

፷፩. ቡና ይጠጣል አይጣጠም?

መልስ፦ ይጠጣል። አንዳንድ ሰዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ አስተምህሮ በመቃረን አይጠጣም ሲሉ ይስተዋላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ በሐዲስ ኪዳን የከለከላቸው ምግቦች በዋናነት ሦስት ናቸው። እነዚህም ሞቶ የተገኘን መብላት እንደማይገባ፣ ደምን ወይም ጥሬ ሥጋን መብላት እንደማይገባ፣ ለጣዖት የታረደን መብላት እንደማይገባ ናቸው። "ዳዕሙ አዝዝዎሙ ይርሐቁ እምዘይዘብሐ ለአማልክት ወእማውታ ወደም" እንዲል (የሐዋ. ሥራ 15፥20)። ይህንን ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 23ም ገልጾታል። ከዚህ ውጭ

ያሉትን ግን የሚበላ አመስግኖ መብላት፣ የሚጠጣም አመስግኖ መጠጣት ይገባዋል:: የሚጠጣ የማይጠጣውን፣ የማይጠጣ የሚጠጣውን ሊነቅፈው አይገባም:: "የሚበላ የማይበላውን አይናቀው የማይበላውም በሚበላው አይፍረድ:: እግዚአብሔር ተቀብሎታልና" እንዲል (ሮሜ 14፥3)::

፷፪. ካህን ወታደር ከሆነ በኋላ ክህነቱ ምን ይሆናል?

መልስ፦ ካህን ወታደር እንዲሆን ቀኖና አይፈቅድለትም:: ወታደር ይገድላል:: ካህን ደግሞ በሥጋዊ መሣሪያ ከገደለ ከክህነቱ ይሻራል:: ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 5 ላይም "ኤጲስ ቆጶስ ራሱን ከክርስቶስ አገልጋይነት አውጥቶ በቤተ መንግሥት ከሚሠራው ሥራ በማናቸውም ሥራ መሾም አይገባውም" ተብሏል:: ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 23 ላይም እንኳንስ ወታደር መሆን ካህናት የወታደርን ልብስ እንኳ መልበስ እንደማይገባቸው ተገልጿል:: "ወኢይልበሱ ካህናት ልብሰ ሐራ" እንዲል:: ምናልባት ሰው ካልገደለ ቀኖና ተሰጥቶት ወደ ቀደመ ክህነቱ የሚመለስበት አግባብ ሊኖር ይችል ይሆናል:: ይህ ከጳጳሱ ጋር በመነጋገር ይደረጋል::

፷፫. ባልና ሚስት አብረው እየኖሩ አንደኛው ወገን መመንኮስ ቢፈልግና አንደኛው ባይፈልግ ብቻውን መመንኮስ ይችላል?

መልስ፦ አይችልም:: ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ላይ ጋብቻ ከሚፈርስበት ምክንያት አንዱ ሁለቱም ተስማምተው የሚመነኵሱ ከሆነ ነው ይላል:: ከዚህ ውጪ አንዱ ሳይፈቅድ አንዱ መመንኮስ ቢፈልግ ግን መመንኮስ አይቻልም::

፷፬. በዕለተ ሰንበት ሱቅ መሸጥ ይፈቀዳል?

መልስ፦ አይፈቀድም:: በጠቅላላው እሑድ መንፈሳዊ ሥራዎች ይሠራሉ እንጂ ሥጋዊ ሥራ አይሠራምና:: ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 33 ላይ "እሑድ እሑድ፣ በጌታችን በዓላት፣ በእመቤታችን በዓላት መሸጥ መግዛት አይገባም" ተብሏልና::

፷፭. አሁን ባለንበት ዘመን የሥራ ሁኔታ እንዴት እናድርግ? ቀዳሚት ሰንበት ግዴታ የሥራ ቀን እየሆነ ነውና::

መልስ፦ እንዲህ ያለው ጉዳይ ተቋማዊ ስለሆነ በቤተክርስቲያኒቱ ተቅዋም በቤተ ክህነት በቅዱስ ሲኖዶስ አማካኝነት ቢጠየቅና ክርስቲያኖች የጌታን በዓል ያከብሩ ዘንድና እንደ ሕጉ ይሄዱ ዘንድ ማድረግ ይገባል::

፷፮. ክልኤቱ ሊቃውንት አመሩ ፈቃደ ዮሴፍ ሠለስቱ ሊቃውንት አመሩ ፈቃደ ሥላሴ ብሎ አገባለሁ መስሎት ነበረ ሥላሴ ባወቁ አስጠበቁት የሚለው ሁለቱም የመንፈስ ቅዱስ እይታ ከሆነ እንዴት ይታረቃል?

መልስ፦ ሁለቱኮ የሚጣላ ነገር የለውም፡፡ ሁለቱ ሊቃውንት ዮሴፍ አስቦት የነበረውን ጻፉ፡፡ ሦስቱ ደግሞ በሥላሴ የታሰበውን ጻፉ፡፡

**፷፯. ከቤታችን ውሻ፥ አህያ ሲወልዱ ግቢው ወይም ቀዬው ከዚህም አልፎ ሰዎች ረክሰዋልና ጠበል መረጨት አለበት የሚሉ አሉ፡፡ ለዚህ ሃይማኖታዊው መልስ ምንድን ነው?**

መልስ፦ በሐዲስ ኪዳን ይህ ከርኵሰት አይቆጠርም፡፡ ስለዚህ እንዲሁ የኦሪቱን ልማድ መሠረት አድርጎ የሚፈጸም እንጂ አሁን ላይ ሥርዓት ሆኖ አይደለም፡፡ ጠበል መረጨት በማንኛውም ጊዜ መልካም ነው፡፡ ነገር ግን የወለደችን እናት ጠበል የምንረጫትና ከላይ የተገለጸውን ያደረጉ ሰዎችን ጠበል የምንረጫቸው ከርኵሰት እንዲነጹ ነው የሚለው አባባል ግን ስሕተት ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች ርኵሰት የነበሩት በብሉይ ኪዳን እንጂ አሁን በሐዲስ ኪዳን አይደለም፡፡

**፷፰. አሥራት በኵራትን በተመለከተ አሥራት የሚሰጠው ለንስሐ አባት ወይም ለምትኖርበት አጥቢያ ቤተክርስቲያን ብቻ ነው ሲባል እሰማለሁ፡፡ በገጠራማ አካባቢ ለተቸገሩ አድባራት መስጠት/መርዳት አይቻልም?**

መልስ፦ አሥራት በኵራት ለንስሓ አባት አይሰጥም፡፡ አሥራት በኵራት የሚሰጥ ለቤተክርስቲያን ነው፡፡ በገጠራማ አካባቢ ለሚገኙ ለተቸገሩ አድባራት ግን መስጠት ይቻላል፡፡ ቤተክርስቲያን አንዲት ናትና፡፡

**፷፱. ቅዱስ ቊርባን ከተቀበልን በኃላ መታጠብ ወይም ውሃ መንካት አይቻልም ይባላል፡፡ ይህንን በተለይ ውጭ ሀገር ለሚያድጉ ልጆች ለምን ብለው ምክንያት ሲጠይቁኝ መልስ አጣለሁ፡፡ በልተው ሲጨርሱ እንኳን እጃቸውን እንዲታጠቡ አናደርጋቸውም፡፡ ምክንያቱ ምንድን ነው?**

መልስ፦ በመጽሐፈ ቅዳሴ እንደተገለጸው ከቆረቡ በኋላ እጅን እግርን መታጠብ፣ ከልብስ መራቆት፣ መስገድ፣ ምራቅን እንትፍ ማለት፣ መበጣት መታገም፣ የእጅ እግር ጥፍርን መቁረጥ፣ ጸጉርን መላጨት፣ ሩቅ ጎዳና መሄድ፣ ፍርድ ቤት መፋረድ፣ ያለመጠን መብላት መጠጣት አይገባም፡፡ "ኢይደሉ እምድኅረ ተመጥዎ ቊርባን ተሐጽቦ እእዳው ወእእጋር ወተዓርቆ አልባስ ወሰጊድ ወወሪቀ ምራቅ ወአውፅኦ ደም ቀሪጸ አጽፋር ወተላጽዮ ጸጕር ሐዊረ ፍኖት ወተፋትሖ ምስለ ሰብእ በሊዐ ወሰትይ ዘእንበለ አቅም" እንዲል፡፡ መቊረብ የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ነው፡፡ በመንግሥተ ሰማያት ደግሞ ሰውነታችን የከበረ ስለሆነ መታጠብ አያስፈልገውም፡፡ በዚህ አንጻር የቆረበ ሰው ሰውነት እጅግ የከበረ ስለሆነ አይታጠብም፡፡

**፸. ቆራቢዎች የጠጡትን የበሉትን ትርፋቸውን ሌላ ሰው መጠጣት የለበትም ይባላል፡፡ ይህ እንዴት ይታያል?**

መልስ፦ ይህ እንኳ መጽሐፋዊ መሠረት የለውም:: ቆራቢዎች ከሌሎች ጋር መብላት፣ መጠጣት አልተከለከሉም:: የእነርሱን ትራፊም ሌላው መብላት ይችላል::

፸፩. ዲያቆን ነኝ ነገር ግን ለሥራ ያለሁበት አካባቢ ቤተክርስትያን የሌለበት ሙስሊም ማሕበረሰብ ብቻ ያለበት አካባቢ ነው:: ክህነት ይገፍ ሳላገለግል በመቀመጤ መክሊቴን በአግባቡ ሳልጠቀምበት ቀረሁ እያልኩ ክህነቴን እነጠቅ ይሆን እያልኩ ይጨንቀኛል:: ምን ትመክሩኛላችሁ?

መልስ፦ ይህ ክህነትን አያስነጥቅም አትጨነቅ:: የምታገለግላቸው ምእመናን ከሌሉ ጸሎትህን ሳታቋርጥ እየጸለይክ መኖር ነው::

፸፪. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት አስተምህሮ መሠረት አንድ ዲያቆን በሥርዓተ ተክሊል ጋብቻውን ከፈጸመ በኋላ በምን ያህል ጊዜ ቅስና መውሰድ አለበት? በአንድ ሀገረ ስብከት ሰሞኑን እሑድ ሥርዓተ ተክሊል ተፈጽሞለት ሳምንት ሳይሞላው ቅስና ተሰጠው:: ይህ አግባብ ነው?

መልስ፦ ምንም ያጠፋው ጥፋት የለም:: ነገር ግን ቅስና ሲሾም ቢያንስ ሠላሳ ዓመት ሊሆነው ይገባል::

፸፫. የመቁጠርያ ምንነት፣ አጀማመርና አገልግሎት ምንድን ነው?

መልስ፦ መቁጠሪያ ከመቼ እንደጀመረ ምንም መረጃው የለኝም:: ነገር ግን በሀገራችን ትውፊት መነኮሳት ያደርጉታል:: ለጸሎት አገልግሎትም ይውላል::

፸፬. አንድ ሰው ንስሓ አባቱን ጠይቆ ስለተፈቀደለት ነገር ከዚያ ግን ከተለያዩ መምህራን ሰምቶ ንስሓ አባቱ ካለው ጋር አልገናኝ ሲለው ምን ያድርግ?

መልስ፦ መጀመሪያ ንስሓ አባት ስንይዝ ግብረ ገብ (መልካም ጸባይ) ያለው እና የተማረ መሆኑን አረጋግጠን ልንይዝ ይገባናል:: ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 51 ትርጓሜ ላይ "ብልህ መድኀኒት ካልተገኘ ድኅነተ ሥጋ እንደማይገኝ ሁሉ የተማረ ግብረ ገብ መምህረ ንስሓ ካልተገኘ ሥርየት አይገኝም" እንዲል:: ስለዚህ ንስሓ አባትህ ያልተማረ ከሆነ የመምህራንን ቃል መቀበል ይገባል:: የቀኖና መጠንን ቀንሶ ወይም አብዝቶ ቢሰጥህ ግን ቢቀንሰውም ቢያበዛውም የንስሓ አባትን መቀበል ይገባል:: የንስሓ አባት በአስተምህሮ ዙሪያ ባለማወቅ የማይፈቀደውን ፈቅዶ ከነበረ ግን መምህራን ስሕተት መሆኑን ከተናገሩ የመምህራንን መቀበል ይገባል::

፸፭. መስቀል መሳለም መቼ ተጀመረ እንዲሁም ማማተብ?

መልስ፦ መቼ እንደተጀመረ አላውቀውም:: ማማተብ ግን ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ እንደነበረ በትርጓሜ ተገልጿል:: ቅዱስ ጴጥሮስ ሲሞን መሠርይን አማትቦ እንዳጠፋው

ተገልጿልና:: መቼም ይጀምር መቼ ግን ዙሮ ዙሮ በረከትን የምናገኝበት ስለሆነ እንሳለማለን::

**፹፯. እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ እንዲሁም በእንተ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ 12 ጊዜ በጣቶቻችን ላይ እንጸልያለን:: ከየት ወደ የት ነው ትርጉሙስ አጀማመሩስ መቼ ነው?**

መልስ፦ ይህ መቼ እንደተጀመረና ቁጥሩ ለምን 12 እንደሆነ መረጃው የለኝም:: በትውፊት እንዳየነው ግን በእንተ ክርስቶስ ስንል አውራ ጣታችንን በሌሎች ጣቶቻችን መጀመሪያ ጣታችን ላይ ወደታች ቀጥሎ ካለው ወደላይ እያልን በቅደም ተከተል እስከመጨረሻ ጣታችን እንጸልያለን:: በእንተ ማርያም ሲባል ደግሞ በሁሉም ጣቶቻችን ወደላይ ወደላይ ብቻ እንቆጥራለን:: ምሥጢሩ ግን ደጋግመን ማረን በማለታችን ምሕረትን መሻታችንን መግለጫ ነው::

**፹፯. ቅዳሴ መቼ ተጀመረ? ሥርዓቱስ ምን ይመስል ነበር?**

መልስ፦ ቅዳሴ ማለት ምስጋና ማለት ነው:: ምስጋና ደግሞ የተጀመረው መላእክት ከተፈጠሩ ጊዜ ጀምሮ ነው:: ምናልባት ጠያቂው የሐዲስ ኪዳን ሥጋውና ደሙ የሚፈተትበት ቅዳሴ የጀመረበትን ቀን ማወቅ ፈልገው ከሆነ ደግሞ በዕለተ ኀሙስ ጌታ ጀምሮታል:: ሥርዓቱ ደግሞ ቀኖና እንደመሆኑ በየጊዜው እየተሻሻለ ከአሁን ዘመን ደርሷል::

**፹፰. ዲያቆናት ካህናት የሚያደርጉት ሻሽ ትርጉሙ ምንድን ነው? ከቆብ ጋራ ያለው ልዩነትስ ምንድን ነው?**

መልስ፦ ሻሽም ቆብም ሁለቱም የአክሊለ ሦክ ምሳሌዎች ናቸው:: በተለየ ቆብ ደግሞ የመነኰሳት የራስ ልብስ ነው:: ሻሽን ያልመነኮሰ ሊቅም ሊያደርገው ይችላል:: ቆብን ግን የመነኰሱ አባቶችና እናቶች የሚያደርጉት ነው:: ሻሽ የክብር ምልክትም ነው:: ካህናት ክቡራን ናቸውና:: "ወይትዐፀፍ ደመና ውስተ ርእሱ" ያለውን መተርጉማን ደመናውን እንደሻሽ ተጠምጥሟል ብለው ሚካኤል ነው ቢሉ ክብሩን መናገር ነው እንዳሉት (ራእ.10፥1 ትርጓሜ):: በዚህ ጊዜ ምሥጢሩ ወደ አክሊል የተጠጋ ይሆናል::

**፹፱. እግዚአብሔርን ከልቤ እንድወደው ምን ላድርግ?**

መልስ፦ ለክብር እንደፈጠረን በማሰብ፣ ፍቅሩን በማሰብ (ፍጥረታትን መፍጠሩ ራሱ ሰውን የመውደዱ ምልክት ነውና)፣ ብንሞት ስለእኛ ሞቶ እንዳዳነን በማስተዋል ትእዛዙን መፈጸም እርሱን የመውደዳችን መገለጫ ስለሆነ እነዚህን ማድረግ ነው::

**፺. አንዲት እናት ጡት እያጠባች መቁረብ ትችላለች ወይ?**

መልስ፦ አዎ ትችላለች:: ልጁ ክርስትና በተነሣ ጊዜ እርሷም ቆርባ ማጥባት ትችላለች::

**፹፩. አንድ ክርስቲያን ወንድ ግርዛት መገረዝ ግዴታ ነው ወይስ አይደለም? ቤተክርስቲያን ምን ትላለች?**

መልስ፦ በሐዲስ ኪዳን መገረዝም አለመገረዝም ከሃይማኖት ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም፡፡ ከጤና አንጻርና ከሌሎች ነገሮች አንጻር ለወንድ ልጅ መገረዝ መልካም ነው፡፡ ከሃይማኖት ጋር ግን የሚያገናኘው ነገር የለም፡፡ በብሉይ ኪዳን ግዝረት የማመን ምልክት ነበር፡፡ በሐዲስ ኪዳን ግን የማመን ምልክት ጥምቀት ሆኗል፡፡ ለዚያ ነው ቅዱስ ጳውሎስ "መገረዝ ቢሆን አለመገረዝም ቢሆን ከንቱ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ ነው እንጂ" ብሎ ያስተማረው (1ኛ ቆሮ.7፥19)፡፡

**፹፪. በሕይወቴ አንድ የሚያስጨንቀኝ ነገር አለ፡፡ እሱም በአካባቢያችን ብዙም ባይሆን ግን በቅባት የሚያምኑ ቄሶች እና ማህበረሰብ ያሉበት ውስጥ ነው የተወለድኩ ነገር ግን ክርስትና በተነሣሁበት ሰዓት በቅባት ቄስ ልጠመቅ በተዋሕዶ አላውቅም ቤተሰብ ብጠይቅም ሊያውቁት አልቻሉም ምን ማድረግ አለብኝ?**

መልስ፦ በመሠረቱ የቅባት የሚባል ቤተክርስቲያን የለም፡፡ በምሥራቅ ጎጃም ያሉ ሁሉም አብያተ ክርስቲያን በጠቅላይ ቤተክህነት ተመዝግበው የሚገኙት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ስም ነው፡፡ ከዚያ ያሉ ዲያቆናት፣ ቀሳውስትም ደብረ ማርቆስ ካለው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሊቀ ጳጳስ ክህነትን ተሹመው የመጡ ናቸው፡፡ ስለዚህ እናንተ ይህንን መሠረት አድርጋችሁ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ካህን ነው ብላችሁ ተጠምቃችኋል፡፡ ቄሱ ግን እናንተ ሳታውቁ በድብቅ አረሚ፣ ሙስሊም፣ ጴንጤ፣ ተሐድሶ፣ ቅባት ሆኖ ሊገኝ ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ እናንተ ስላላወቃችሁት ችግሩ የራሱ ይሆናል እንጂ ከእናንተ የልጅነት ጸጋ አይቀርባችሁም፡፡ ስለዚህ ምንም መጨነቅ አያስፈልግም፡፡ ነገር ግን ከሓዲ መሆኑን እያወቃችሁ ከእርሱ ብትጠመቁ ልጅነትን አታገኙም፡፡ እናንተ የተዋሕዶ ነው ብላችሁ አስባችሁ ሰውየው ግን በድብቅ የሌላ እምነት ሆኖ እያጭበረበረ ቢያጠምቃችሁ እግዚአብሔር እርሱን ይጠይቀዋል፡፡ ለእናንተ ግን እግዚአብሔር ጸጋን አያስቀርባችሁም፡፡ ስለዚህ መጨነቅ አያስፈልግም፡፡ ቅባት ነን የሚሉ ካህናት ካሉ ካወቃችሁበት ጊዜ ጀምሮ በእነርሱ እጅ አትጠመቁ፣ አትቁረቡ፣ በጠቅላላው ከእነርሱ ራቁ፡፡ የቅባት ክሕደት ታላቅ ነውና፡፡

**፹፫. ትንቢት መሻር ይችላል? ከተሻረስ ከእግዚአብሔር አዋቂነት ላይ ጥያቄ አይፈጥርም? ለምሳሌ ንጉሡ ሕዝቅያስ እና የነነዌ ሕዝቦች ላይ የተነገረው ትንቢት እንዳልተፈጸመ አይተናል፡፡ ይሁዳም ስለተተነበየበት አይደለም አለመሸጥም ይችል ነበር ይባላል፡፡ እና ካልተፈጸመ ሌሎች ተፈጽመው ግን ትንቢት ከሚባሉት ጋር "ትንቢት" የሚለውን ትርጉም መያዝ ይችላል? ማለት ካልተፈጸመ ለምን ትንቢት ይባላል?**

መልስ፦ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል፡፡ ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ ዕውቀትም ቢሆን ይሻራል" ብሏል (1ኛ ቆሮ.13፥8)፡፡

ትንቢት ሁለት ዓይነት ነው:: አንደኛው ሰዎች ቢሠሩት የሚደረግ ባይሠሩት የማይደረግ ሰዎችን መሠረት ያደረገ ትንቢት ነው:: ሌላኛው እግዚአብሔርን መሠረት ያደረገ ትንቢት ነው:: እግዚአብሔርን መሠረት ያደረገ ትንቢት ሳይፈጸም አይቀርም:: ሰዎችን መሠረት ያደረገ ትንቢት ግን ሰዎች በሚሠሩት ሥራ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል:: "ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ:: ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና" የሚለው ትንቢት በአዳም ዕፀ በለስን መብላትና አለመብላት ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ሊቀርም ሊፈጸምም ይችላል (ዘፍ.2፥17):: አዳም በመብላቱም ሞቷል ተፈጽሞበታል:: በሌላ መልኩ የነነዌን ትንቢት ብንመለከት "ዮናስም የአንድ ቀን መንገድ ያህል ወደ ከተማይቱ ውስጥ ሊገባ ጀመረ ጮኽም በአርባ ቀን ውስጥ ነነዌ ትገለበጣለች" ብሎ ነበር (ትን.ዮና.3፥4):: ነገር ግን ከዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 5 ላይ ስንመለከት ንስሓ በመግባታቸው ትንቢቱ ቀርቷል:: ስለዚህ ትንቢት መባሉ ባያደርጉት ይደረግ ስለነበረ ነው:: እግዚአብሔርም ይህንን ስለሚያውቅ ነግሯቸዋል:: ይህ መባሉም እነርሱን እንዲመለሱ አድርጓቸዋል:: እና ከአዋቂነቱ ጋር አይቃረንም::

፹፬. ፍርድ ሁለት ጊዜ ነው የሚሰጠው? ማለትም አንድ ሰው ሲሞት ገነት ወይ ሲኦል ፍርድ ይሰጠዋል:: በምጽአትም ደግሞ እንደገና ለመንግሥተ ሰማያት ወይም ለገሃነም ፍርድ ይሰጣል:: ስለዚህ ሁለት ፍርድ ነው የሚሆነው ወይስ ቀድሞ የነበረውን ፍርድ ለዘለዓለም የማጽናት ጉዳይ ነው? ከዚህ ጋር ተያይዞ በሁለቱም ሀሳብ ውስጥ ቢሆን አንድ ጥያቄ አለ በጻድቃን ምልጃ ከሲኦል የወጡ ነፍሳት እንዳሉ ይነገራል:: እንዲዚህ ሲሆን የእግዚአብሔርን ፍርድ መለወጥ ይችላል? ከእግዚአብሔር ፍርድ ጋር አይጋጭም?

መልስ፦ የእግዚአብሔር የመጨረሻ ፍርድ የሚሰጠው በዕለተ ምጽአት ነው:: ነገር ግን ፈታሒነቱን እንረዳ ዘንድ በየዘመኑ ፍርድን ፈርዷል ይፈርዳልም:: ስለዚህ በዚህ ምድር ያጠፋን ሰው በልዩ ልዩ መከራ በመቅጣት ሲፈርድበት የሚታይበት ሁኔታ አለ:: በኋላም ነፍሱን ወደ ሲኦል በማግባት የሚፈርድበት ጊዜ አለ:: የመጨረሻው ፍርድ ግን በዕለተ ምጽአት የሚደረግ ነው:: ሌላው ከእግዚአብሔር ፍርድና ከጻድቃን ምልጃ ጋር ተያይዞ የተጠየቀው ነው:: እግዚአብሔር ፍጹም ቸር በመሆኑ በጻድቃን ምልጃ እንድንድንም ያደርጋል:: ምልጃ የፈታሒነቱ አንድ አካል ነው:: እርሱ ስለፈቀደ ነው በጻድቃን ምልጃም የሚድኑት:: የጻድቃን ምልጃ ከእርሱ ፍትሕ የተቃረነ ሳይሆን ሰዎች ይድኑ ዘንድ ራሱ የፈቀደው በጎ ፈቃድ ስለሆነ አይቃረንም::

፹፭. ክህነት የለኝም ዲቁና አልተቀበልኩም:: እና ዲቁና ለመቀበል ዕድሜዬ ሄዷል:: ለክብረ ክህነት የሚበቃኝን ያህል ተምሪያለሁ (ዳዊት ውዳሴ ማርያም):: ስለዚህ መምህር በደንብ ተምሬ መርጌታ መሆን እችላለሁ?

መልስ፦ መርጌታ የክህነት ስም ሳይሆን የሙያ ስም ነው። ስለዚህ ይቻላል። ሴቶች እንኳ ክህነት ባይሾሙም አቋቋም፣ ዜማ፣ ቅኔ እየተማሩ መምህራት ሆነዋል። ስለዚህ በደንብ ተምሮ መርጌታ መሆን ይቻላል።

**፹፮. በቤተክርስቲያን አስተምህሮ ንስሓ በውክልና ይቻላል ወይ? ከተቻለ እንዴት?**

መልስ፦ አዎ የሚቻልበት አግባብ አለ። የያዕቆብ መልእክት ላይ "ተአምኑ በበይናቲክሙ ኃጢአተክሙ፤ እርስ በእርሳችሁ ኃጢአታችሁን ተነጋገሩ" ካለ በኋላ ሊቃውንት በሐተታ ሲገልጹ "ኃጢአቱን ለመምህረ ንስሓው መንገር ቢያፍር ለባልንጀራው ነግሮት ይንገርለት" ብለዋል (ያዕ.5፥16 ትርጓሜ)። በሃይማኖተ አበው ላይም "ወንትአመን ኃጢአተነ በበይናቲነ፤ ኃጢአታችንን ለመምህረ ንስሓችን እንናገር" ካለ በኋላ መተርጉማን በሐተታ "አንድ ሰው ንግድ፣ ዘመቻ ሄዶ እንዲሁ እንዳይሞት ቢሞት እንኳ ለባልንጀራው ነግሮ ንስሓውን ይንገርለት" ብለዋል (ሃይ.አበ.37፥2 ትርጓሜ)። በዋናነት ግን ራሳችን ብንገባ መልካም ነው። ማፈር ያለብን ኃጢአት መሥራትን ነው እንጂ ከኃጢአት እንላቀቅ ዘንድ ከካህን መናዘዝን አይደለም።

**፹፯. በዐውደ ምሕረት ላይ ፓትርያርክ ሊቀ ጳጳስ ቆሞሳት አስተዳዳሪዎች ቢገኙ የግድ መጥራት አለብን ወይ? ቀኖና ነው ወይ?**

መልስ፦ የግድ መጥራት አለብን የሚል ነገር የለም። ነገር ግን አባቶችን ስማቸውን ጠርተን ሰላም ብለን ትምህርታችንን ብናስተምር መልካም ነው። ይህን የመሰለ አካሄድ ደግሞ ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክታትም እንረዳለን። መጀመሪያ ሰላምታ ካቀረበ በኋላ ነው ወደ ትምህርቱ ወይም መልእክቱ የሚገባው (1ኛ ቆሮ.1፥1፤ ፊልጵ.1፥1፤ 2ኛ ተሰሎ.1፥1)። ቀኖና ግን አይደለም። ብዙ ከሆኑ ጠቅልለን ብፁዓን አበው ብለን ማለፍ እንችላለን።

**፹፰. ቅዳሴ አሐዱ ከተባለ በኋላ የማይገባ ከመጀመርያው ቅጽር (ከውጨኛው) ነው ወይስ ከቤተ መቅደስ ብቻ ነው?**

መልስ፦ በሥርዓተ ቅዳሴ "ወኵሎሙ ምእመናን እለተ ጋብኡ ለነሢአ ምሥጢር ቅዱስ ይቁሙ በኀድዐት ውስተ ቤተክርስቲያን ለሰሚዐ ነገረ እግዚአብሔር፤ ሥጋውን ደሙን ለመቀበል የተሰበሰቡ ምእመናን ሁሉ ነገረ እግዚአብሔርን ለመስማት ልቡናቸውን ሳያባክኑ በእግራቸው ወዲያና ወዲህ ሳይሉ በዓይናቸው ግራ ቀኝ ሳያዩ በዝግታ በጸጥታ ሆነው ይቁሙ" ይላል። ከዚህ የምንረዳው ቅዳሴ ከተጀመረ በኋላ ወዲያ ወዲህ ማለት እንደማይገባ ነው። ነገር ግን ሊያስቀድስ መጥቶ እርሱ ሲደርስ ቅዳሴው ተጀምሮ ቢደርስ ከውጭ ሆኖ ተከታትሎ በረከትን ቢቀበል በማለት አንዳንድ አባቶች ከሕንጻው ሳይሆን ከቅጽሩ መግባትን ይፈቅዳሉ። ለዚህም "ወለዘሂ መጽአ ኀቤየ ኢይሰድዶ ወኢያውፅኦ አፍኣ" የሚለውን ይጠቅሳሉ (ዮሐ.6፥37)። መውጣትም የሚፈቀድበት እንዳለ ፃኡ ንኡስ

ክርስቲያን የሚለው ማስረጃ ይሆናል። የታመመ ሰውም ሕመሙ ቢጸናበትና አስቸኳይ ነገር ቢገጥመው የሚወጣበት ሥርዓታዊ አግባብ አለ። አስቀዳሾች ሐሳባቸው እንዳይበታተን እንደ ደብረ ሊባኖስ፣ እንደ ጎንደር ቂርቆስ ሁለት ቅጽር ካለው ቤተክርስቲያን ከውጨኛው ቅጽር ቆይተው ቅዳሴው ሲያልቅ ገብተው ይባረካሉ።

**፳፱. አንድ ዲያቆን መስፈርቱን ሳያውቅ ቢሾም ወይም በልጅነቱ ቢሾም መስፈርቱን ባወቀ ጊዜ ምን ማድረግ አለበት?**

መልስ፦ በመስፈርቱ መሠረት ተሹሞ ከነበረ በሹመቱ ይቀጥላል። ሳይገባው ባለማወቅ ተሹሞ ከነበረ ይሻራል። ለምሳሌ በፍትሐ ነገሥት በጉቦ የተሾመ ይሻር ይላል። ይህን ሥርዓት ባለማወቅ በጉቦ ከተሾመ በኋላ ቢያውቀው ያው ከመሻር አይቀርም። ዘማዊ ከነበረ ይሻራል። ክህነትን ከሚከለክሉ ነገሮች ምንም ነገር አልሠራ ከነበረና ንጹሕ ከነበረ ግን በክህነቱ ይቀጥላል። ከዚህ ያለፈውን ጉዳይ በንስሓ አባት፣ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ አማካኝነት መፍትሔ መስጠት ይገባል።

**፴. የቀኖና እና የንስሓ ልዩነት እንዴት ነው?**

መልስ፦ ንስሓ ኅሊናዊ መጸጸት ነው። ነስሐ-ተጸጸተ ከሚለው የግእዝ ግሥ ንስሓ የሚል ጥሬ ዘር ይወጣል። ትርጉሙ ከልብ መጸጸት ማለት ነው። ቀኖና ደግሞ የበደልነውን በደል ለንስሓ አባታችን ነግረነው የሚሰጠን የቅጣት ትእዛዝ ነው።

**፴፩. የቅዱስ ዳዊት መዝሙሮችን በመከፋፈል ይህ ለዚህ ጥሩ ነው ይህ ለዚህ መልካም ነው እያሉ የሚናገሩ አንዳንድ ሰዎችን እያየሁ ነው። ለየራሳቸው የተሰጠ የፈውስ አገልግሎት አላቸው ወይንስ ከምን አንጻር ነው የሚናገሩት?**

መልስ፦ የቅዱስ ዳዊት መዝሙሮች ሁሉም መልካሞች ናቸው። መልካም ያልሆነ መዝሙር የለም። ጸልየናቸው ዋጋ የሚያሰጡን ደግሞ እንደልባችን እምነት እንጂ በሌላ ቀመር (Formula) አይደለም። በእርግጥ ከምሥጢሩ ጋር ለመሄድ ለምሳሌ ጠዋት ላይ አምላኪየ አምላኪየ እገይሥ ኀቤከ፤ አቤቱ ወደ አንተ እገሰግሣለሁ የሚለው እንዲጸለይ በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 14 ላይ ተገልጿል። ሰኞ ንሴብሖን እያሉ ሊቃውንት ከቀኑ ጋር ተመሳሳይ ታሪክ ያለውን አምጥተው ነግረውናል። ይህ ጉዳዩን የበለጠ ከቀኑ ጋር አዋሕደን እንድንረዳው እንጂ ሌላ ቀመር ኖሮት አይደለም። ስለዚህ ዋናው በእምነት መጸለይ እንጂ ይህኛውን ብደግም ያድነኛል፣ ያኛውን ብደግም አይፈውሰኝም የሚባል ነገር የለም። እንዲህ የሚሉ ሰዎችም በዚህ አግባብ ከሆነ ልክ አይደሉም።

**፴፪. አንድ ሰው ሲመነኩስ እስከ ስንት ቀን መጠበቅ አለበት? ማንእዳባ ሂዶ ከመነኮሰ 10 ቀን ይጠበቃል፣ ከሌላ ቤተክርስትያን ከመነኮሰ ግን 40 ቀን ይጠበቃል ይባላል። ይህ እንዴት ይታያል?**

መልስ፦ ይህ ይህ እንኳ ዝም ብሎ በልማድ የመጣ ነገር እንጂ መጽሓፋዊ መሠረት የለውም። የመነኵሰ ሰው ይጠበቅ የሚል የለም። ማን ከምን ለምን ይጠብቀዋል? የመነኵሰም የቆረበም ሰው ራሱን ከኃጢአት መጠበቅ አለበት እንጂ ሌላ ጠባቂ አያሻውም።

፺፫. አንድ ክርስቲያን ከጌንጤ ቢወልድ እርሷ ሳትጠመቅ ልጁ ክርስትና ተነሥቶ የእናቱን ጡት ይጠባል?

መልስ፦ መጀመሪያ ኦርቶዶክስና ጌንጤ መጋባት የለባቸውም። ከተጋቡ በኋላ አንዱ ጌንጤ አንዱ ኦርቶዶክስ ከሆነና ከወለዱ ደግሞ ልጁን በሞግዚት አስጠምቆ አምጥቶ እናቱ ከቤት ጡት ብታጠባው ምንም ችግር የለውም። ጡት ለሕፃናት የምግበ ሥጋ ምንጭ እንጂ ሌላ ነገር አይደለምና።

፺፬. ለአንድ ጻድቅ ታቦት የሚቀረጽለት ማረጋገጫው ምን ሁኖ ሲገኝ ነው? በዚህ ዘመንስ ለዚህ የበቃ ቢኖር መለኪያው ምንድን ነው?

መልስ፦ ጻድቅ ሆኖ ሲገኝና የሰውየው ጽድቅ በብዙ መንገድ ሲገለጥ ነው። በሕይወት ዘመኑ የሠራው ሥራ፣ የጻፈው መጽሐፍ፣ ክርስቲያናዊ ሕይወቱና የመሳሰሉት ናቸው። እነዚህ ሥራዎቹ ለሌላው አርአያ ይሆኑ ዘንድ በገድል ተጽፈው ሌላው እያነበባቸው፣ ጽላት ተቀርጾላቸው፣ መልክእ ተደርሶላቸው ይኖራሉ። በዚህ ዘመን እንዲህ ያለ ቢኖርም ካረፈ በኋላ ጠቅላላ ሕይወቱ በቅዱስ ሲኖዶስ ተመርምሮ በቀኖና ይጸድቃል። ከሚታወቀው ሕይወት ውጭ ያለ ሌላ ሕይወት ካለ ራሱ እግዚአብሔር ይወቀው። በሚታወቀው ሕይወቱ ግን አስተማሪ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ አያስወቅስም።

፺፭. የወለደች አራስ እንድትጠበቅ ሃይማኖታዊ ሥርዓት አለ ወይ?

መልስ፦ የወለደች ሴት ብዙ ደም ስለሚፈሳት፣ ሕመም ስለሚሰማት ከአጠገቧ የሚረዷት ሰዎች ቢኖሩ መልካም ነው። ይህ እንዲሆን የሚያዝዝ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ግን የለም።

፺፮. አንድ ሰው በምንኩስና ሕይወት እየኖረ ዶክተር ኢንጂነር ሌሎችንም ተምሮ በዓለም ቢኖር ከቤተክርስቲያኗ ጋር ያለው ተጽእኖ ምንድን ነው?

መልስ፦ መነኵስ ከዓለም የተለየ ስለሆነ በገዳም ይኖራል። ከላይ የተጠቀሱት ሙያዎች ካሉትና በእነዚያ ሙያዎቹ ለገዳሙ የሚሆኑ ፕሮጀክቶችን ለመሥራት ወይም በቅዱስ ሲኖዶስ ለቤተክርስቲያን የሚሆኑ ፕሮጀክቶችን ለመሥራት ተፈቅዶለት ከሆነ ሊመጣ ይችላል። ከዚያ ውጭ የተለየ ሥርዓት ካልተሠራ በስተቀር መነኵሳት በገዳም ይኖራሉ እንጂ በዓለም አይኖሩም።

፶፯. ካህናት (ቀሳውስት እና ዲያቆናት) ሚስቶቻቸው በተለያየ ምክንያት ይሞታሉ (ልጅ ቢወልዱም ባይወልዱም)። ከዚያ በኋላ፣ በተለይ የክህነት ሕይወታቸው እንዴት ነው የሚሆነው?

መልስ፦ ሌላ ሳያገቡ ልጆቻቸውን እያሳደጉ ከኖሩ በክህነታቸው ይቀጥላሉ። እንደገና ካገቡ ደግሞ ክህነታቸው ፈርሶ ምእመን ሆነው ይኖራሉ።

፶፰. ጠበል አራት ቀን ተጠምቆ ቢቋረጥ ችግር አለው?

መልስ፦ ጠበል አንድ ቀንም፣ ሁለት ቀንም፣ ሦስት ቀንም፣ አራት ቀንም፣ ከዚያም በላይ መጠመቅ ይቻላል። የግድ የተቀመጠ ቁጥር የለም። ስለዚህ ተጠማቂው ሊጠመቅ የፈለገውን ቀን ያህል ተጠምቆ ወደ ሥራው መመለስ ይችላል።

፶፱. ኢየሱስ ክርስቶስ ከተነሣ በኋላ የተወጋ ጎኑን የተቸነከሩ እጆቹን አሳየ ይላል። እንደዕለተ አርቡ ሁኖ ከተነሣ ከትንሣኤ በኋላ የቀደመ አካላችንን ወፍራሙ ወፍራም ለምጻሙ ለምጻም ሁኖ ይነሣል እንደማለት አይሆንም? መስሎ ታያቸው ካልን ደግሞ ምትሐት አያሰኝም?

መልስ፦ አይሆንም። ክርስቶስ በእውነት ስለተነሣ መስሎ አልታየምና ምትሐት አይባልም። ሲነሣ የእርሱ በተለየ የተወጋ ጎኑን የተቸነከሩ እጆቹን ለደቀመዛሙርቱ መለያ ይሆናቸው ዘንድ ትቶታል። እኛ ግን ስንነሣ ወንዱ ሁሉ በአምጣነ አዳም ሴቱ ሁሉ በአምጣነ ሔዋን ይነሣሉ። መምሰል አንጻራዊ ነው እንጂ በሁሉ ነገር አይደለም። ለምሳሌ ክርስቶስ በራሱ ሥልጣን ነው የተነሣ። ስለዚህ በኵራችን እርሱ ስለሆነ በራሳችን ሥልጣን እንነሣለን አንልም። ከትንሣኤ በኋላ መነሣቱን ያሳያቸው ዘንድ በልቷል። ከትንሣኤ በኋላ ምግብ መመገብ ግን የለም። ስለዚህ እርሱ ያደረጋቸው ለሐዋርያት ማረጋገጫ ይሆኑ ዘንድ ስለሆነ ለእርሱ ብቻ ይነገራሉ። እኛ ስንነሣ ግን ወፍራም፣ ለምጻም፣ ቀጭን፣ ቀይ የለም። ሁላችንም ወንዶች አዳምን ሴቶች ሔዋንን መስለው እንነሣለን እንጂ።

፷. ዲያቆን ጽንሐሕ አይዝም ወይስ ይይዛል?

መልስ፦ በትውፊት የጽንሐሑን አንገት ይዘው የሚያጥኑ ቀሳውስት ናቸው። ዲያቆን ጽንሐሕ ከያዘም ከወገቡ ላይ ይይዛል እንጂ እንደ ቄሶቹ ከአንገቱ ላይ አይዝም።

፷፩. መነኰሳት በተለይ ሴቶች ልጅ ቢወልዱ የምንኵስና ቆባቸውን ማውልቅ አለባቸው? አኗኗራቸውስ ምን መምሰል አለበት?

መልስ፦ መጀመሪያ መነኰሳት ከዓለም የራቁ እንደመሆናቸው ከመነኰሱ በኋላ ግንኙነት አይፈቀድም። ነገር ግን ፀንሰው ሳለ መንኵሰው ልጅ ቢወልዱ ወይም ደግሞ ዝሙት ፈጽመው በሕገ ወጥ መልኩ ልጅ ወልደው ቢገኙ ምን ይደረጋል ለሚለው ፍትሐ ነገሥት እንደሚከተለው ይላል። "ወኵሉ እኑ ዘይትዐቀፍ በግብረ ዝሙት ይትኀደግ

ሎቱ ምዕረ ወይጹም ፵ ዕለተ እንዘ ውጉዝ ውእቱ በተሐርሞ ወንጽሕ ዓመተ ፍጹመ፤ በዝሙት የተሰነካከለ መነኵሴ ቢኖር አንድ ጊዜ ይቀርለታል ዓርባ ቀን ከሰው ተለይቶ ጥሬ እየቆረጠመ ውሃ እየጠጣ በንጽሕና ሆኖ ዓመት ይጹም" ይላል። በአጭሩ ለበደለው በደል ቀኖና ተሰጥቶት/ተሰጥቷት በምንኵስና ይቀጥላል/ትቀጥላለች። ምንኵስናን ነቅፎ የወጣ ሰውም ተጸጽቶ ከተመለሰ በምንኵስናው ጸንቶ መኖር ይችላል።

## ፻፪. በልጅነታቸው ያለተክሊል የተዳሩ ልጆች ተምረው ዲቁና ተቀብለው ከሚስታቸው ጋር ከቆረቡ በኋላ መቀደስ ይችላሉ?

መልስ፦ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 "ወማዕሠረ ተዋስቦሰ ኢይከውን ወኢይትፌጸም ዘእንበለ በሀልዎተ ካህናት ወጸሎት ዘላዕሌሆሙ ወይመጥውዎሙ ቍርባነ ዘቦቱ ይትዋሐዱ ክልኤሆሙ ወይከውኑ አሐደ ሥጋ ወዘእንበለ ዝንቱሰ ኢይትኈለቍ ሎሙ አውስቦ፤ የጋብቻ አንድነት ካህናት ቢኖሩ ጸሎት ጸልየው ሥጋውን ደሙን ቢያቀብሏቸው እንጂ አይጸናም። ያለዚህም ጋብቻቸው ከጋብቻ አይቆጠርም" ይላል። ስለዚህ በልጅነታቸው ያለተክሊል ያለ ቍርባን የተጋቡ ሰዎች ጋብቻቸው ከጋብቻ ስለማይቆጠር ግንኙነት ካደረጉ ከዝሙት ስለሚቆጠር ክህነት አይገባቸውም። በመጽሐፈ ሐዊ እንዳየነው ካህን ድንግል የሆነና ድንግል የሆነችን የሚያገባ ነውና። ከዚህ ውጭ ግን ቢያገባ ዝሙት ስለሆነ አይቆጠርም። በተክሊል ተጋብተው ያሉ ሰዎች ግን ተምረው ክህነትን የሚቀበሉበት አግባብ ነበረ (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 7)።

## ፻፫. በዕቃ የተቀዳ ጠበል ለምን ከቤት ውጪ ይቀመጣል?

መልስ፦ ይህ ልማድ ነው እንጂ ከቤት ውስጥም መቀመጥ ይችላል።

## ፻፬. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋው አልቆ አጥንቱ እስከሚቆጠር ነው የተገረፈው። ስለዚህ ሲገረፍ የፈሰሰው ደም ወደ መሬት ፈስሷል ወይስ እንዴት ነው?

መልስ፦ አዎ ክብር ይግባውና ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገረፍና በመስቀል ሲሰቀል የፈሰሰው ደሙ ወደ መሬት ፈስሶ መሬትን ቀድሷል። ያ ደም ግን መለኮትን የተዋሐደ በመሆኑ ውላጤ፣ ሙስና የለበትም። ስለሆነም ራሱ እግዚአብሔር ባወቀ ለዘለዓለም አካሉ ሆኖ ይኖራል።

## ፻፭. በዓላት ግብጾች ኢትዮጵያውያን ሥራ እንዳይሠሩ የቀመሩት ነው ብለው የሚናገሩ አሉ። ልክ ናቸው?

መልስ፦ ልክ አይደሉም። በዓላትን ማክበር በረከተ ሥጋን፣ በረከተ ነፍስን ያስገኛል ብለን የሐዋርያትን ሲኖዶስ መሠረት አድርገን እናከብራለን እንጂ ግብጾች ብለውን አይደለም። እንዲህ ያለ የጥላቻ ንግግር እንኳን ከክርስቲያን ከሰው አይጠበቅም። ሰንበትን አክብር ያለ ጌታ እንጂ ግብጻውያን አይደሉም። የጌታን በዓላት እንድናከብር የነገሩን ሐዋርያት

ናቸው። ስለዚህ እንደዚህ መሠረትና እጅ እግር የሌለው ነገር መቀበል የለብንም። ሥራ መሥራት ሌላ ነው፣ በዓል ማክበር ሌላ ነው። በዓል እያከበርን ጠንክረን ሠርተን ሀገራችንም ራሳችንንም መለወጥ እንችላለን። የድኅነታችን ምንጭ በዓል ማክበራችን እንዳልሆነ ምንም በዓል የማያከብሩ ከእኛ ሀገር በታች በድኅነት እየማቀቁ የሚኖሩ ሀገሮች መኖራቸው ማስረጃ ነው።

**፶፮. አንዲት እናት ልጅ እያጠባች መቁረብ ትችላለች?**

መልስ፦ አዎ ትችላለች። መቊረብ ልጅን ከማጥባት አይከለክልም። ከዚሁ ጋር ለመግለጽ ያህል የፀነሰች ሴትም መቊረብ ትችላለች። እርሷ ስለቆረበች ፅንሱም ቆረበ ግን አይባልም። በጥምቀት፣ በቊርባንና በመሳሰሉት ምሥጢራት እናት ከልጅ ግንኙነት የላቸውምና። "ወአልቦ ማዕከለ ወላዲት ወወልድ ተሳትፎ በጥምቀተ ክርስትና" እንዲል (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 3፤ ሲኖዶስ ዘቅርጣግና 7)።

**፶፯. አንድ ሰው ቤተሰብ ያለ ፍላጎቱ ሊድሩት ሲሉ እምቢ ብሎ ሌላ ሴት አገባ። አሁን ቄስ ሆኗል። ይህ አያስነቅፍም ወይ?**

መልስ፦ በመሠረቱ ያለሙሽሮች ፍላጎት የሚደረግ ጋብቻ መኖር የለበትም። ቤተሰብ ማስገደድ የለበትም። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 እንደተገለጸው በተጋቢዎች ፈቃድ መደረግ አለበት። ሙሽራው አልፈልግም ካለ የእርሱ ፍላጎት መከበር አለበት። ስለዚህ ይህ ምንም አያስነቅፍም።

**፶፰. በወረቀት የተሳሉ ቅዱሳት ሥዕላት ከዘመን ብዛት የተነሣ ተቀዳደው ከሚወድቁ በእሳት ተቃጥለው እምነት ቢሆኑ ይሻላል የሚሉ አሉና ልክ ነው ይላሉ?**

መልስ፦ አይ ልክ አይደለም። ቅዱሳት ሥዕላት ምንም ያህል ቢያረጁ በክብር ለብቻቸው በሳጥን ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ሊቀመጡ ይገባል። ንዋየ ቅድሳት ለአገልግሎት ባይመቹ እንኳ ከዕቃ ቤት ተቀምጠው ይኖራሉ እንጂ አይቃጠሉምና።

**፶፱. ብዙ ሰዎች ጸጉራችሁን አሳጥሩ ሲባሉ ጌታኮ ከእኔ ተማሩ ብሏል። ስለዚህ የጌታ ጸጉር ረጅም ስለሆነ በማለት ጸጉራቸውን የሚያስረዝሙ አሉ። የጌታ ጸጉር የረዘመበት ምስጢሩ ምንድን ነው?**

መልስ፦ በብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሔር የተለዩ ሰዎች ጸጉራቸውን አይላጩም ነበር። "ራሱን ለመለየት ስእለት ባደረገበት ወራት ሁሉ በራሱ ላይ ምላጭ አይደርስም። ለእግዚአብሔር የተለየበት ወራት እስኪፈጸም ድረስ የተቀደሰ ይሆናል የራሱንም ጠጕር ያሳድጋል" እንዲል (ዘኍ.6፥5)። ክርስቶስም ለናዝራውያን ምሳሌ ለመሆን በተጨማሪም የክርስቶስ ጸጉር መለኮት የተዋሐደው ስለሆነ አልተቆረጠም አይቆረጥም። እኛ ሌሎች ሰዎች ግን ዕሩቅ ብእሲ ስለሆንን በዕሩቅ ብእሲ ሕግ እንጓኛለን። ወንድ ልጅ ጸጉሩን

አያሳድግ ስለሚል ማሳደግ አይገባም (1ኛ ቆሮ.11፥14-15፤ ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 11)። ክርስቶስ ግን ዕሩቅ ብእሲ ሳይሆን ሥግው ቃል በመሆኑ ጸጕሩን አልተላጨም። ስለዚህ የራሳችንን የተሳሳተ ምኞት በጥቅስ ለማመሳሰል መሞከር የለብንም።

**፻፲. በተአምረ ማርያም የፍቅር አግልግሎት ከተፈጸመ በኋላ የራስ፣ የእጅ፣ የጣት፣ የአንገት የወርቅ ሽልማታቸውን ያውጡ ይላል። እንዲሁ እንደተባለው ወርቁ ነው ወይስ ሌላ ምስጢር አለው? የፍቅር አገልግሎት የተባለውስ የቱ አገልግሎት ነው?**

መልስ፦ በቁሙ ማንኛውም ሰው ተአምረ ማርያም ሲነበብ ጌጡን ያውልቅ ተብሏል። ይህም ከእግዚአብሔር ቃል የበለጠ ጌጥ አለመኖሩን ለመመስከር ነው። የፍቅር አገልግሎት የተባለ ለቅድመ ቅዳሴው የተደረገው ንበተ ተአምረ ማርያም ከሆነ ከዚያ በፊት የነበረው ሰዓታቱ ማኅሌቱ ነው። ለድኅረ ቅዳሴው ከሆነ ቅዳሴው ነው። እግዚአብሔርን ደስ ብሎን የምናመሰግንበት በመሆኑ ማኅሌቱ፣ ቅዳሴው፣ ሰዓታቱ የፍቅር አገልግሎት ተብሏል።

**፻፲፩. አንድ ሕፃን ተጠምቶ በጣም ቢያለቅስ ጠብቶ መቁረብ ይችላል ወይስ አይችልም?**

መልስ፦ አይችልም። ሕፃናት ቅዳሴ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ምንም ነገር መብላት ወይም መጠጣት የለባቸውም። ስለዚህ ቢያለቅስ እያባበሉ ማቆየት እንጂ ስለክብረ ሥጋ ወደሙ ሲባል እስከሚቆርብ ማጥባት የለብንም።

**፻፲፪. የአንድ ቤት አባላት ወይም ቤተሰብ የተለያየ የንስሓ አባት ቢይዙ ችግር አለው?**

መልስ፦ ምንም ችግር የለውም። እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ልዩ ልዩ የንስሓ አባቶችን መያዝ ይችላሉ። አንዱን ብቻም መያዝ ይችላሉ።

**፻፲፫. ወር በገባ በሰባት ለምንድን ነው ግዝት በዓል ያልሆነው?**

መልስ፦ በመሠረቱ በ12ም፣ በ21ም፣ በ29ም፣ በሰንበትም በሁሉም የሚከበረው እግዚአብሔር መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ሰባት የፈጣሪ በዓል ነው ብሎ ሌሎችን የፈጣሪ በዓላት እንዳልሆኑ በሚያመለክት አሻሚ ንግግር መጻፍ ተገቢ አይደለም። የፈጣሪ ያልሆነ በዓል የለም። በ7ም፣ በ12ም፣ በ21ም በማንኛውም ቀን የሚከበረው በዓል የእግዚአብሔር በዓል ነው። በፍጡራን ስም መሰየሙ የጸጋ ክብራቸውን እንድናውቅ እንጂ ዋናው የበዓሉ ባለቤት እግዚአብሔር መሆኑን ለአፍታም ቢሆን መዘንጋት የለብንም። በዓል የተፈጠረ ለሰው ማረፊያ ነው። ስለዚህ በ12፣ በ21፣ በ29 ግዝት በዓላት ተደርገው በሌሎቹ ሰው የፈለገውን እንዲሠራ ሊቃውንቱ ሥርዓት ሠርተውልናል። ሁሉም ቀናት እግዚአብሔር ታላላቅ ሥራ የሠራባቸው ቢሆኑም በእነዚህ እንድናርፍ ሥርዓት ተሠርቷል። ስለዚህ በእኛ መሰለኝ እየተነሣን ለምን 7፣ ለምን 27 እያልን ራሳችንን አርቀ አሳቢ ባናስመስል መልካም ነው። በተፈቀደው

እያከበርን ሌላውን እንደራሳችን ፈቃድ መኖር ነው። ዓመቱን ሙሉ በሚነበበው ስንክሳር ብንመለከት በሁሉም ቀናት ሥላሴ ታላላቅ ሥራ ሠርተውባቸዋል። እንዲህ ስለሆነ ዓመቱን ሙሉ ግዝት ይሁን አይባልም።

፻፲፬. ባልና ሚስት ቆርበው እየኖሩ ስለሸመገሉ ሩካቤ አይፈጽሙም። አንዱ (ዷ) መመንኮስ ይችላሉ?

መልስ፦ ከጋብቻ በኋላ መመንኰስ የፈለገ ካለ ተፈቃቅዶ መመንኰስ ይቻላል። ሚስት ሳትፈቅድ ባል መመንኰስ የለበትም፣ ባል ሳይፈቅድም ሚስት መመንኰስ የለባትም። ተፈቃቅደው ከሆነ ግን ይችላሉ (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 10)።

፻፲፭. እየተገነባ ያለ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ምን ምን ሲያሟላ ነው ሙሉ ለሙሉ ተጠናቋል ተብሎ ተመርቆ አገልግሎት መስጠት የሚችለው? ሳያልቅ ወደ ሕንፃው ገብቶ እየተቀደሰበት ሊሠራና ሊጠናቀቅ ይችላል ወይስ ሙሉ ለሙሉ የማያዳግም ሥራ ከተሠራ በኋላ አስመርቆ ወደ አገልግሎት ማስገባት ነው?

መልስ፦ ሕንጻው ሙሉ በሙሉ ከተሠራ በኋላ በሜሮን ተቀብቶ የተቀደሰ ሆኖ ይቀደስበታል። ግማሹ እየተሠራ በግማሹ መቀደስ ግን አይገባም። ሙሉ በሙሉ እስኪጠናቀቅ ድረስ ጊዜያዊ መቀደሻ ቦታ (መቃኞ) በጳጳሱ ተፈቅዶ እየተቀደሰ መቆየት ነው።

፻፲፮. አንቀጸ ብርሃን ላይ ክርስቶስ ሲወለድ መላእክት በእናቱ እቅፍ ሆኖ አዩት ወደ ላይ ከፍ ሲሉ ደግሞ በመንበሩም ተቀምጦ አዩትና አደነቁ የሚል አለ። ከትንሣኤው ፴ ቀናት በኋላ ዐረገ ሲል እንዴት ነው ከላይ ከተባለው አንጻር? አያይዘው ጌታችን በተመሳሳይ ሰዓት መስቀል ላይም የኪሩቤል ጀርባ ላይም ነበር ሲባል እንዴት ነው? በማሕፀንም በዙፋንም አለ ሲባል እንዴት ነው?

መልስ፦ መላእክት በሥጋ በእመቤታችን እቅፍ ሲያዩት በመለኮት ደግሞ በዘፈቀደ በሚገለጥላቸው መልኩ በሰማይ ተመልክተውታል። ይህንን ለመግለጽ ቅዱስ ያሬድ በእናቱ እቅፍ ሆኖ በሰማይ በመንበሩ ተቀምጦ አዩት ተብሏል። በአርባኛው ቀን ዐረገ የተባለ ቃል በሥጋ የርቀት ያይደለ የርኅቀት ዕርገትን ነው። በመስቀል ላይ ሳለ በኪሩቤል ጀርባ ነበረ ማለትም በሥጋ በመስቀል ተሰቅሎ በመለኮቱ ግን በዘፈቀደ ለእነርሱ በሚገለጥበት መንገድ በኪሩቤል ጀርባ ነበረ ማለት ነው። ከኪሩቤል ጀርባ ሳይለይ በሥጋ በድንግል ማርያም ማሕፀን መወሰኑን ያመለክታል።

፻፲፯. ስለ ቅባት አስተምህሮ ስሕተትነት የታወቀ ነው። ግን ከዚህ በፊት የዚህ እምነት ተከታይ የነበሩ (በልጅነታቸው) አሁን ግን እውነቱን አውቀው የተመለሱ ቤተሰቦቻቸው ግን በዚያው

**እምነት የቀጠሉ ቢሆን ከቤተሰቦቸው ጋር ያለው ግንኙነት በምን መልኩ መሆን አለበት? አብሮ መብላት አብሮ መጠጣት ይከለክላል?**

መልስ፡- ከሌላ እምነት ሰዎች ጋር አንድ ላይ መጸለይ አይቻልም። ስለዚህ ከቅብዐቶች ጋር አንድ ላይ መጸለይ አይገባም። ከዚህ ውጭ ባለው ግን በአንድ ቤት መኖርና ማሕበራዊ ጉዳዮችን ማከናወን ይቻላል። ሃይማኖታዊ ምሥጢራትን ማከናወን ግን አይቻልም። አብሮ መብላት አብሮ መጠጣት ግን ነውር የለውም። የራስህን ምግብ ባርከህ መብላት ነው።

**፲፲፰. የክርስቶስን ሕማም በሕክምና መነጽር ማየት ይቻላል አይቻልም በማለት በቅርብ ጊዜያት የተነሣ ክርክር አለ። ምንም እንኳን ከሕክምና አንጻር የሚያዩት ሰዎች የሕማሙን ነገር ይበልጥ በሰው ልብ ለማስገባት እና ታመመ ቈሰለ ከሚለው ገለጻ በላይ በጥልቀት ገብቶ የሥቃዩን ጥግ ለማሳየት ቢሆንም በሌላኛው ወገን ደግሞ ይህን ማድረግ ሕማማቱን ማሳነስ ወይም መቀነስ ነው የሚል ተቃውሞ ቀርቧል። እርስዎ ምን ይላሉ?**

መልስ፡- ነገረ ክርስቶስን በሳይንሳዊ ትምህርቶች አንጻር ለማየት መሞከር ፈጽሞ አይቻልም። ዕርገቱን ከስሕበት ሕግ (Gravitational law) አንጻር፣ ስቅለቱን በድንግልና መወለዱንና የመሳሰለውን ከሕክምና አንጻር፣ በተዘጋ ቤት መግባቱን ከምሕንድስና አንጻር... ወዘተ እያልን ብንናገር ወደ ስሕተት ያመራናል። ስለዚህ ነገረ ክርስቶስን መጻሕፍት ላይ በተገለጹት አንጻር ማየት፣ ማስተማር፣ መናገር ይገባናል እንጂ ከሳይንሳዊ ዕውቀቶች አንጻር ካየነው ያለአቻ ንጽጽር (False equivalence) በመሆኑ ሕፀፁ ስለሚጎላ እንዲህ ዓይነቱን መርሐ ግብር ብንተወው እላለሁ።

**፲፲፱. አንድ ዲያቆን የሌላ ሃይማኖት ተከታይ ሚስት አግብቶ መቀደስ ይችላል ወይ? ክህነቱ ተቀባይነት የሚያገኘው በምን ሁኔታ ነው። ዲያቆናትስ እስከ ስንት ዕድሜ በዲቁና ይቆያሉ?**

መልስ፦ እንኳን ዲያቆን ማንኛውም ምእመን የሌላ እምነት ሰዎችን ማግባት አይችልም። ለጋብቻ መሥፈርቱ አንዱ በሃይማኖት አንድ መሆን ነውና። የሌላ ሃይማኖት ሴት ከሆነች በምን አገባት? በቍርባን እንዳይባል የሚቀርብ ያመነ ነው። እንዲሁ ዝም ብሎ ያለቍርባን ነው ከተባለ ደግሞ ያለቍርባን የሚደረግ ጋብቻ ከጋብቻ አይቆጠርም ተብሏል። ስለዚህ ግንኙነት ካደረገ የዚህ ሰው ክህነት ተቀባይነት የለውም። ዲያቆናት በዲቁና እስከ ዕለተ ሞታቸው ሊቀጥሉ ይችላሉ።

**፲፳. ዐሥራትን ስናወጣ ለምንገለገልበት አጥቢያ ቤተክርስቲያን ብቻ ነው ገቢ መሆን ያለበት የሚሉ መምህራን አሉ። በአንጻሩ ደግሞ ዐሥራትን ከአጥቢያ ውጭ በገጠር አገልግሎት ለሚታጎልባቸው ገዳማት አድባራት መስጠት ይቻላል የሚሉ አሉ። እርስዎ ምን ይላሉ?**

መልስ፡ ቤተክርስቲያን አንዲት ስለሆነች አሥራት በሎራታችንን ለማንኛውም ቤተክርስቲያን መስጠት እንችላለን። እኛ ያለንበት አጥቢያ አገልግሎቱን ለመፈጸም የሚቸገር ከሆነ ግን ቅድሚያ ለአጥቢያችን መስጠት አለብን።

፻፳፩. የልደታ ማርያም ንፍሮ ይነፈራል። ለምንድን ነው?

መልስ፡ ይህ ትውፊታዊ ተግባር ከእመቤታችን ልደት ጋር የሚገናኝ ነው። ድንግል ማርያም የተወለደችው በሊባኖስ ተራራ ነው። ስትወለድ ደግሞ ሐናን አይሁድ አሳድደዋት ስለነበረ ድንግል ማርያም ከቤት ውጭ በተራራ ተወልዳለች። ይህንን ታሪክ መሠረት በማድረግ የነበረውን ሁኔታ ለማስታዎስ ለጊዜያዊነት በሚሠራ ቂጣና፣ ንፍሮ በመቀቀል ይከበራል።

፻፳፪. አንድ ዲያቆን በቅዳሴ ሲያገለግል ለብፁዕ ጳጳስነ ብሎ የሚጠራው የሀገረ ስብከቱን ጳጳስ ስም ወይስ ዲቁና የሰጠውን ጳጳስ ስም ነው መጠራት ያለበት?

መልስ፡ የሀገረ ስብከቱን ጳጳስ ነው። የዘመኑን፣ የቦታውን ጳጳስ ስም መጥራት ይገባል። አሁን ከምንቀድስበት ቦታ (በሀገረ ስብከቱ) ያለው የሾመን ጳጳስ ከሆነ እርሱን እንጠራለን። እርሱ ካልሆነ አሁን ተሹሞ ያለውን እንጠራለን።

፻፳፫. ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤ እስከ ዕርገት በየት ቆየ? ምን ምን ሥራዎችንስ ሠራ?

መልስ፡ ከትንሣኤ እስከ ዕርገት በሥጋ በዚሁ ምድር ሐዋርያትን ኪዳንን፣ ትምህርተ ኅቡዓትን እያስተማረ ኖሯል። የሠራቸው ሥራዎች ትንሣኤውን ማስረዳትና ትምህርተ ኅቡዓትን እንዲሁም ኪዳንን ማስተማር ነው።

፻፳፬. ባልና ሚስት ሲጋቡ ለ10 ቀናት ያህል ይጠበቃሉ። ይህ ባህላዊ ነው ሃይማኖታዊ?

መልስ፡ ይህ ባህላዊ ነው እንጂ ሃይማኖታዊ አይደለም። ብቻቸውን ቢሆኑ የሚያገኛቸው መናፍስታዊ ጥቃት ኖሮ አይደለም። እንዲያውም ከመናፍስት ጥቃት መጠበቅ ያለባቸው ያልቆረቡ ሰዎች ናቸው። የቆረቡትማ ቢያንስ ሰይፈ እሳት የክርስቶስን ሥጋና ደም ታጥቀዋል የሚያስፈራቸው የለም።

፻፳፭. አንድ ሰው ሚስቱ ምጥ ተይዛ እያለ እስክትወልድ ድረስ መታጠቂያህን (ቀበቶህን) ፍታ ይባላል። ጤና ጣቢያም ላይ ቀበቶ ሲያስፈቱ አይቻለሁ። ይህ ከየት የመጣ ነው?

መልስ፡ ይህም ከሃይማኖት ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም። ሲጀምር ይህን በባህል አንጻር እንኳ ብናየው ጥሩነቱ ያን ያህል አይደለም። ቀበቶን መፍታት ከሚስቱ መውለድ ጋር አይገናኝም። ቀበቶና ማሕፀን ምን ያገናኘዋል? መታጠቂያውን ፈቶ፣ ሱሪው ወልቆ ከመዋረድ እንዲህ ያለው ባህልስ ቢቀር ይሻላል።

**፻፳፮. አንድ ሰው ሚስቱ ላልሆነች ሴት ማጉረስ ይችላል ወይስ አይችልም?**

መልስ፦ ማጉረስኮ የፍቅር ምልክት ነው። ይህ ደግሞ ከፍትወታዊ ፍቅር ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም። ዘመድ ዘመድ የሆኑ ሰዎች መዋደዳቸውን ለመግለጽ የሚያደርጉት ነገር ነው። ይህ እንደየሰው ይለያያል። በባልና በሚስት ላይ ችግር የሚፈጥር ከሆነ አለማጉረስ ነው። ነገር ግን ይህ ክርስቲያናዊ ፍቅርን ለመግለጽ የሚደረግ ከሆነ ችግር የለውም። በዚህ ጉዳይ እንደየባህሉ ብንሄድ የተሻለ ነው። ሌላ ሴትን ማጕረስ ባልን የመናቅ ምልክት ተደርጎ የሚታሰብበት ቦታ ካለ መተው ነው።

**፻፳፯. በእስልምና እምነት ያሉ ወገኖች የብሉይ ኪዳን አይሁዶች በአንድ አምላክ ያምኑ ነበረ። የሥላሴ ትምህርት በኋላ የመጣ የስሕተት ትምህርት ነው ይላሉ። የኔታ ምን ይላሉ?**

መልስ፦ ይህ የራስን ስሕተት የሌላው አስመስሎ በማቅረብ የመጣ ስሕተት (Blame shift) ነው። በመጀመሪያ በኋላ የመጣ እምነት እስልምና መሆኑን ሙሉ ዓለሙ የሚያውቀው እውነታ ነው። እስልምና በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጣ እምነት ነው። የብሉይ ኪዳን አይሁዶች በአንድ አምላክ ያምኑ ነበረ የተባለው እውነት ነው። የብሉይ ኪዳን አይሁዶችም እኛ ክርስቲያኖችም የምናምነው በአንድ አምላክ ነው። የሥላሴ ትምህርትም አንድ አምላክ እንዳለ ያስተምራል እንጂ ሦስት አማልክት እንዳሉ አያመለክትም። ይህ አንዱ አምላክ ሦስት አካላት እንዳሉት ግን እንናገራለን። ይህንን ደግሞ ራሱ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን በአካል ሦስት መሆኑን በብዙ መልኩ ገልጿል። የመጀመሪያውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ብናየው እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ሲል በአካል ሦስት መሆኑን በሚያመለክት ቃል ኤሎሂም אלוהים ብሎ ነው። አንድ አካልን የሚያመለክት ቢሆን ኖሮ אלוה ባለ ነበርና። ስለዚህ ይህንን የቀድሞውን እውነታ ባላዩ በማለፍ በቅርብ ዘመን የተፈጠረን እምነት የተሳሳተ ትምህርት እውነት ለማስመሰል መድከም አይገባም።

**፻፳፰. የዝክር እና የጽዋዕ ማኅበር ልዩነት አለው ይሆን?**

መልስ፦ ዝክርን የሚዘክር ሰው አንድ ሰውም ሊሆን ይችላል። በባለቤቱ በእግዚአብሔር ስም ወይም በቅዱሳን ስም ነዳያንን በመጥራት፣ ካህናትን በመጥራት፣ ሌሎችንም ሰዎች በመጥራት የሚከናወን ነው። ጽዋዕም በዓላማ ደረጃ ከዝክር ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም በአፈጻጸሙ ግን ይለያል። ጽዋዕ በአንድ ቅዱስ ስም የተሰባሰቡ ሰዎች በየተራ የሚዘክሩት ነው። ዝክር ግን በቋሚነት አንድ ሰው የሚዘክረው ነው።

**፻፳፱. ኢትዮጵያ የሚያበራ ውሃን ወደ ነዳጅ የሚቀይሩ ድንጋይ ወደ ወርቅ የሚለወጡ በርካታ የጥበብ የብራና መጽሐፍት አሉ ይባላል። አሉ ከተባለ ለምን አይወጡም ስንል ተሰውረው ነው ይላሉ። እውነት ይኖር ይሆን?**

መልስ፦ እንዲህ ያለ ነገር አይቼ ስለማላውቅ መልሱን አላውቀውም፡፡ ግላዊ አስተያየቴን እንድሰጥ ግን ይፈቀድልኝ፡፡ እኔ በግሌ እንዲህ ያሉ ጉዳዮችን ከተረት ተረት ነው የምመድባቸው፡፡ ፍጥረታትን ተመራምሮ መጠቀም እንደሚገባን አእምሮንና ፍጥረትን እግዚአብሔር በአንድ ላይ ሰጥቶናል፡፡ ስለዚህ ከእንዲህ ያሉ ተረቶች ወጥተን አእምሯችንን ተጠቅመን ለመሥራት መትጋት ይገባናል ባይ ነኝ፡፡ እንዲህ ያለ መጽሐፍ በመፈለግ የምንደክምበትን ኀይል ብንሠራበት ምናልባት ከሌሎች ሀገሮች ቀዳሚ የምንሆንበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡

፻፴. ሰንበቴ የሚባለው አሁን ባለው አካሄድ ሳያስቀድሱ ጠላውን ጠጥቶ ምግቡን በልቶ መሔድ ነውን?

መልስ፦ ሰንበቴ ምእመናን በሰንበት በሰንበት ቤተክርስቲያን እየተገናኙ ነዳያንን የሚመግቡበት እነርሱም ስለክርስትና የሚነጋገሩበት ነው፡፡ ይህም ቤተክርስቲያን አስቀድሰው ከዚያ በኋላ የሚደረግ ነው፡፡ እንጂ ሳያስቀድሱ ለምግብ ብቻ የሚመጡበት መሆን የለበትም፡፡

፻፴፩. በቅዳሴ ሰዓት ከቅጥር ግቢ ውጭ የግል ጸሎት መጸለይ ይቻላል?

መልስ፦ የግል ጸሎት መጸለይ አይከለከልም፡፡ ነገር ግን የበለጠ የማኅበር ጸሎት እያለ የግል ጸሎት መጸለይ ለምን አስፈለገ? እግዚአብሔር የግልህን መሻት በማኅበሩ ጸሎት እንደሚፈጽምልህ አታምንም እንዴ? በቀን የፀሐይ ብርሃን እያለ ሻማ ማብራት ምን ያስፈልጋል? መቻሉን ይቻላል፡፡ ግን ግን የለበጠ የምትጠቀምበትን የማኅበር ጸሎት ብታስቀድም ለአንተ የተሻለ ነው፡፡

፻፴፪. ቅዳሴ እየተቀደሰ እያለ ማንም ሰው ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ አይችልም ይባላል፡፡ ወንጌል ከተነበበ በኋላ ለማሳለም የሚንቀሳቀሱት ሰዎች እንዴት ሊንቀሳቀሱ ቻሉ?

መልስ፦ ወንጌል የሚያሳልሙት ሰዎች የቅዳሴ ተልእኮው አንዱ አካል በመሆናቸው ወንጌልን ለማሳለም ከቦታ ወደ ቦታ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ማንም ሰው መንቀሳቀስ የለበትም የተባለው ቀዳሾችን፣ ወንጌል አሳላሚዎችን የሚያካትት አይደለም፡፡

፻፴፫. በዓለም ያለችው ቤተክርስቲያን አንድ ሆና ሳለ ለምንድን ነው የሀገራችን አድባራት የማይረዳዱት? ለምሳሌ የከተማው የገጠሩን፣ አቅም ያለው የሌለውን?

መልስ፦ ቤተክርስቲያን አንዲት እንደመሆኗ አንዷ እየተቸገረች አንዷ ገንዘብ የምታባክንበት ሁኔታ መኖር አልነበረበትም፡፡ ቅዱስ ሲኖዶስም ይህንን ማስተካከል ይጠበቅበታል፡፡

**፻፴፬. አንዳንድ ሰዎች ቀን ቀን ሰው ማታ ማታ ጅብ ይሆናሉ ይላሉ። በዓይናች አይተናል እንደእነዚህ ዓይነት ሰዎችንም እናውቃለን የሚሉ አሉ። ይሄ እንዴት ይታያል?**

መልስ፦ በዓይናችን አይተናል ሰዎች ጅብ ሲሆኑ ባሉ ሰዎች ሰይጣን ራሱ የሚደነቅ ይመስለኛል። ከእርሱ የሚበልጡ ውሸታሞችን ሲያይ ምን ያህል ይገረም ይሆን? ሰው ወደ ጅብነት አይለወጥም። ቀን ሰው ማታ ጅብ የሚሆን ሰው የለም። እንዲህ ያለ ምናባዊ ውሸት የሚያወሩትን ሰዎች ውሸት ጥሩ እንዳልሆነ መንገር ይገባናል። ማኅበረሰቡን ከእንደዚህ ያለ ድንቁ*ርና ማላቀቅ ይገባል።

**፻፴፭. መድረክ መሪውም፣ ሰባኪውም ጸሎት አስፈጻሚ ካህኑም ሥራቸው ልመና ሆነ። የሚሰበሰበው ብር ለፕሮጀክት ውሎ የሥራ ዕድል የሚፈጥር ነገም ከመለመን የሚታደግ ቢሆን ተስፋ ነበር ግን አይደለም። ምን ይሻላል? ብዙ ምእመናን ስንሰላች ስለበረከት ፈንታ መርገም እንዳንቀበል በማለት ከቤተክርስቲያን እንዲቀሩ እያደረገ ነው። ምን ይሻላል?**

መልስ፦ ይህ የቤተክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር ደካማ ከመሆኑ የመነጨ አስተዳደራዊ ክፍተት ነው። በተጨማሪም ሰው በፍትሐ ነገሥት በተገለጸው መሠረት አሥራቱን፣ በኵራቱን ማውጣት ባለመቻሉ ቤተክርስቲያን አገልጋዮቿን ለማኖር ስትል በዐውደ ምሕረት መለመንን እየጀመረች መጣች። ይህ እንዳይሆን ምእመናንም አሥራት በኵራታቸውን ቢያወጡ፣ የቤተክርስቲያን አስተዳደርም ይህንን ቢያስቀር መልካም ነበር።

**፻፴፮. ከእግዚአብሔር ውጭ ጸሎታችንን የሚሰማን አካል አለ ወይ ማለቴ ቅዱሳን መላእክቱንና እናታችንን ማርያምን ጨምሮ። እና ደግሞ ሁሉም ቦታ ይገኛሉ ወይ?**

መልስ፦ እግዚአብሔር በባሕርዩ ሁሉን ዐዋቂ ሁሉን ሰሚ ስለሆነ የምንጸልየውን ጸሎት ይሰማናል። ቅዱሳን መላእክት ድንግል ማርያምም በተሰጣቸው ጸጋ የሰውን ጸሎት ሰምተው ምልጃን ለእግዚአብሔር ያቀርባሉ። እግዚአብሔር በአካል የሌለበት ቦታ የለም። በሁሉ ቦታ አለ። ቅዱሳን ግን የአካል ውሱንነት ስላለባቸው በሁሉ ቦታ አይገኙም። ነገር ግን ሰው በእነርሱ ስም ቢማፀን ልመናቸውን እንደሚሰማ እግዚአብሔር ቃል ስለገባላቸው በሁሉ ቦታ ያለ እግዚአብሔር በስማቸው የተማፀነውን ይረዳዋል።

**፻፴፯. አንድ ሰው ለመዳን የግድ ኦርቶዶክስ መሆን አለበት?**

መልስ፦ አዎ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኝ ካልሆነ አንድ ሰው መዳን አይችልም። ለመዳን ማመን ያስፈልጋል። ይህ እምነት ደግሞ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አስተምህሮ መሠረት መሆን አለበት።

**፻፴፰. ጾም ባለመጾም የሚያገኘን ኃጢአት አለ ወይ?**

መልስ፦ አዎ። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 15 ላይ እንደተገለጸው ጾም ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ነው። የጾምን መልካምነት አውቆ የማይጾም ካለ ደግሞ ኃጢአት ይሆንበታል። "እንግዲህ በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው" እንዲል (ያዕ.4፥17)።

፻፴፱. አንድ ሰው ከቆረበ በኋላ ለ24 ሰዓት መታጠብና ከልብስ መራቆት የለበትም። ነገር ግን ለምሳሌ ዛሬ ጾም ሁኖ 9:00 የቆረበ ሰው ነገ መሥሪያ ቤት ለመግባት ቢፈልግና የመሥሪያ ቤቱ ሕግ ራሱን የቻለ ደንብ ልብስ ቢኖረው እንዴት አድርጎ ነው ማስታረቅ የሚቻለው?

መልስ፦ ዙሮ ዙሮ 24፡00 ሰዓት መከበር አለበት። ስለዚህ መሥሪያ ቤቱ የማይፈቅድ ከሆነ በማግሥቱ ሥራ በሌለበት ቀን መቊረብ ወይም እሑድ ጠዋት መቊረብ ነው አማራጩ።

፻፵. ቅዳሴ አቋርጦ የሚገባ ይሁዳን ይመስላል። ቅዳሴ አቋርጦ የሚወጣ አርዮስን ይመስላል። እንዲሁም ቅዳሴ አቋርጦ የሚወጣውን ሰው 30 አጋንንት በግራ 30 አጋንንት በቀኝ እየሳሙ ወደ ቤቱ ይወስዱታል የሚባል ትምህርት ሰምቼ ነበር። ይሄ እንዴት ይታያል?

መልስ፦ እንዲህ ያለ ምደባ ደስ አይልም። ለማስከበር ተብሎ የማይሆነውን ይሆናል ማለት ነውር ነው። ደግሞ የቁጥር አደፋፈራችን ያስቃል ያሳቅቃልም። ደርሰን 60 አጋንንትን ስናድል ማብሸቃችን። ከእንዲህ ያለ ቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ከማይገኝ ተረት ተረት መውጣት አስፈላጊ ነው። ለማስወደድ ብላችሁ እንዲህ ያለ ጅል ነገር ፈጥራችሁ የምታወሩ ሰዎችም ይቅርባችሁ። ቅዳሴ ማስቀደስ መልካም ነው። ፍሬ ቅዳሴ ሲጀመር ንኡሰ ክርስቲያን ይወጣሉ። አሁን እኒህን አርዮስ ልንላቸው ነው? በጭራሽ። ለታመሙት እንዲህ ያለ ሥርዓት የሠራነው መልሰን ይሁዳ ወይም አርዮስ ብለን ለመስደብ ነው እንዴ?! ቅዳሴ ማስቀደስ መልካም ነው በልዩ ልዩ ምክንያቶች የሚወጣውን ሰው አርዮስ ማለት ግን ነውር ነው። በልዩ ልዩ ምክንያት ዘግይቶ የመጣውን መስደብ ትልቅ ነውር ነው።

፻፵፩. ሕፃን ልጅ ክርስትና ሲነሣ ጸጉሩን መላጨት አለበት?

መልስ፦ ክርስትና የሚነሣ ሰው ጸጕሩን ይላጭ አልተባለም። ሳይላጭም ክርስትና መነሣት ይችላል። ለዚህ ማስረጃችን ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 3 ነው። ስለንኡሰ ክርስቲያን ጥምቀት ሲናገር ጸጕራቸውን ይፍቱ አለ እንጂ ይቆረጡ አለማለቱ ነው። ቃል በቃል ትርጓሜው "የራሳቸውን ጸጕር ፈትተው ሴቶችን ያጥምቋቸው" ይላል።

፻፵፪. ክርስቶስ ሲሞት አራቱ ባሕርያት ተለያይተዋል? ክርስቶስ ከትንሣኤ በኋላ ደመ ነፍስ አለችው?

መልስ፦ አልተለያዩም። የሰው ልጅ ሲሞት ነፍስ ከሥጋው ስትለይ እሳትነቱ ስለሚለየው ሰውነቱ ይቀዘቅዛል፣ ውሃነቱ ስለሚለየው ከሞተ በኋላ አካሉን ቢመቱት አይደማም።

ክርስቶስ ግን እንደ እኛ ዕሩቅ ብእሲ ስላልሆነና ሥግው ቃል ስለሆነ ከሞተ በኋላ ሐራዊ ጎኑን ቢወጋው ትኩስ ደም ወጥቶታል። ይህም አራት ባሕርያት እንዳልተለዩበት ያመለክታል። ክርስቶስ ሞተ ስንል ነፍስ ከሥጋው ተለየ ማለት እንጂ አራቱ ባሕርያት አልተለዩበትም። አዎ ከትንሣኤ በኋላ ለክርስቶስ ደመ ነፍስ አለችው። በትንሣኤ ከትንሣኤ በፊት የነበረውን ሁለንተና አካሉን ይዞ ተነሥቷል እንጂ ደመ ነፍሱን ትቶ አልተነሣምና።

፩፻፫. ሴት ልጅ ልማደ አንስት ላይ ስትሆን ቤተክርስቲያን መጠጋት የምትችለው ምን ያህል ነው?

መልስ፦ ከቅጽረ ቤተክርስቲያን አትገባም እንጂ ከውጭ ተሳልማ መሄድ ትችላለች። የተቀመጠ ሜትር ወይም ኪሎሜትር የለም። አንዳንዶች አርባ ክንድ ይራቁ ይላሉ። ለዚህ ግን መጽሐፋዊ መሠረት አላገኘሁለትም።

፩፻፬. መንገድ ላይ ሥዕለ አድኅኖ ይዞ መለመን የመና*ፍቃን መሳለቂያ አድርጎናል። የሚለምኑትም ለቤተክርስቲያን ብቻ ብለው ሳይሆን የሻይ የሚታሰብላቸውንም በማሰብ ነው። ይሄ በቤተክርስቲያን ስም መነገድ አይሆንም?

መልስ፦ ይህ የቤተክርስቲያኗ የአስተዳደር አካላት ድክመት መገለጫ ነው። ይህ እንዳይሆን በቅዱስ ሲኖዶስ ተወስኖ እንዲህ የሚያደርጉትን ደግሞ ተከታትሎ ቀኖናዊ እርምጃ በመውሰድ ማስተካከል ይቻል ነበር።

፩፻፭. የሰው ልጅ የክርስትና ስም ያስፈለገው ለምንድን ነው? ማለቴ እኛ ክርስትና ስንነሳም ሆነ የተለያየ ጸሎት ሲደረግልን እንዲሁም በፍትሐት ጊዜ አብርሃም፣ አበበ፣ ጫላ፣ ሐጎስ፣ ትዕግሥት፣ መቅደስ እየተባልን ብንጠራስ?

መልስ፦ የሰው ልጅ የክርስትና ስም ያስፈለገው በቤተክርስቲያን አገልግሎት ጊዜ በክርስትናው፣ በጋብቻው፣ በሞቱ ጊዜ መጠሪያ ይሆነው ዘንድ ነው። ይህም ዝም ብሎ የመጣ ነገር አይደለም። ክርስቶስም ለአንዳንድ ሐዋርያት እርሱን ሲከተሉት ስማቸውን የቀየረላቸው አሉ። "ኢየሱስም ተመልክቶ አንተ የዮና ልጅ ስምዖን ነህ አንተ ኬፋ ትባላለህ አለው ትርጓሜውም ጴጥሮስ ማለት ነው" እንዲል (ዮሐ.1፥42)። ይህንን መሠረት አድርገን ክርስትና ስም እናወጣለን።

፩፻፮. አንድ ድንግል መነኩሴ ከመነኮሰ በኋላ ቢማርና ለአገልግሎት ቢበቃ ቅስና ብቻ መቀበል ይችላል ወይስ ዲቁና የግድ ነው? ቁምስና ማለት ምንድን ነው?

መልስ፦ ክህነት የሚሾም በቅደም ተከተል ነው። ዲቁና ተሹሞ ከዚህ ቅስና ይሾማል እንጂ ቀጥታ ቅስና አይሾምም። ቁምስና የሚባለው በቁስና በኤጲስ ቆጶስ መካከል ያለ መዓርግ ነው። ኮሬ ኤጲስ ቆጶስ እየተባለም ይጠራል። የኤጲስ ቆጶሱ ረዳት ነው።

**፻፵፯. የእግዚአብሔርን ሀልዎቱን ከምናውቅባቸው አንዱ አእምሮ ጠባይዕ ነው። ነገር ግን አንድ ሰው በተለያየ ምክንያት (ወዶ ሳይሆን ለምሳሌ በአጋንንት ተንኮል በሰዎች አማካኝነት የተመረዘ ምግብ በልቶ ወዘተ) ቢያብድ (አእምሮውን ቢያጣ) ይህ ሰው በተሰጠው አእምሮ ጠባይዕ ተመራምሮ የእግዚአብሔርን ሀልዎት አያውቅ ነገር አያስተውልም። ታድያ ይህ ሰው ይፈረድበታልን? ሰው ሲያድግ ነገሮችን ሲመዝን እውነትን ከሐሰት መለየት ሲችል ሃይማኖት ሊቀይር ይችላል (ማለት ከሐሰተኛ እምነት ወደ ክርስትና)። ነገር ግን ሰውየው በአእምሮ መጎልመስ በአስተሳሰብ መብሰል ሲጀምር አበ*ደ። ሃይማኖቱን ሳይቀይር በጥንት ሃይማኖቱ እንዳለ ማለት ነው። ታዲያ ይህ ሰው እግዚአብሔር ይፈርድበት ይሆን?**

መልስ፦ የእግዚአብሔርን ፍርድ አናውቀውም። ስለዚህ ይህን ጥያቄ በትክክል መመለስ የሚችል ራሱ እግዚአብሔር ነው። እኛ ግን አእምሮ ማጣት፣ መታመምና የመሳሰሉት ነገሮች ሊገጥሙን እንደሚችሉ በማሰብ ጤነኛ እንደሆንን እግዚአብሔርን በማመለክ ጸንተን መኖር ይገባናል።

**፻፵፰. በበዓል አከባበር ዙርያ በግንቦት ልደታ ምዕመናን ለዓመቱ ካደረሰችኝ እያሉ በግ፣ ወይፈን፣ የአልኮል መጠጦችን ይሳላሉ። ይህ ስሕተት አይደለም ወይ?**

መልስ፦ አይደለም። እነዚህ ስለቶች በሰፈር አካባቢ የሚደረጉ ናቸው። ከዝክር ይቆጠራሉ። የሚሳለው ሰው በዚህ ቀን ካደረሰኝ የዛሬ ዓመት በግ፣ ወይፈን፣ ወይም የአልኮል መጠጥ አዘጋጃለሁ ቢል ይችላል። ጠላም፣ ወይንም ሌሎችም የአልኮል መጠጦች በመጠኑ ጠጥተናቸው እግዚአብሔርን ብናመሰግን አልተከለከሉምና። የተከለከለ አብዝቶ መጠጣትና መስከር እንጂ በመጠኑ መጠጣት አልተከለከለም። ቤተክርስቲያን ላይ ለሚደረጉ ስለቶች ግን ጥንቃቄ ያስፈልጋል። ለምሳሌ ቅቤ፣ ዱባ፣ ሾላና የመሳሰሉት ለቤተክርስቲያን ስለት ተብለው መግባት እንደሌለባቸው ፍትሐ ነገሥት ይገልጻልና (አንቀጽ 17)።

**፻፵፱. እጮኞች በተክሊል ወይም በቁርባን ካልተጋቡ በስተቀር ከጋብቻ አይቆጠርም ብለዋል። እንደዚያ ከሆነ ብዙዎቻችን የተወለድነው ልጆች ይህን ሥርዓት ካልፈጸሙ ቤተሰቦች ነው። ትክክል ካልሆነ የተወለድነው ልጆች የዘማውያን ልጆች ነን?**

መልስ፦ እንደ ፍትሐ ነገሥቱ ገለጻ አዎ። ይህ ነገር ከፍትሐ ነገሥቱ ገለጻ አንጻርና ከአብዛኛው አሁናዊ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋብቻ አንጻር ሲታይ የተራራቀ በመሆኑ ቅዱስ ሲኖዶስ ላለፈው ይቅርታን እንድናገኝ፣ ለሚመጣው እንድንጠበቅ ሥርዓት ቢሠራ መልካም ነው። ሥርዓትን ጠብቆ ማስጠበቅ በዋናነት የሲኖዶስ ድርሻ ነበር። ይህ ግን አልሆነም። ሲኖዶሳዊ ስብሰባ የሚያስፈልግ ለዚህ ሕዝባዊ ጥያቄ መልስ ለመስጠት ነበር። ግን የጠበቅነውን ያህል አልሆነልንም። እስኪሆን በትዕግሥት እንጠብቅ። እስከዚያው ወደፊት ለማግባት ያሰባችሁት በተባለው መልኩ በቁርባን ማግባት ነው።

ያለሥጋው ያለደሙ ተጋብታችሁ ያላችሁ ደግሞ ቅዱስ ሲኖዶስ መፍትሔ እስኪሰጥ በምክረ ካህን መኖር ነው።

፻፶. የሙስሊም ሆቴል (ቁርስ ቤት) ገብቶ አንድ ክርስቲያን እንቁላል፣ ወተትና የመሳሰለቱን መመገብ ይችላል?

መልስ፦ ይችላል። ካልተጠራጠረ የቀረበለትን ባርኮ መብላት ይችላል። ለምሳሌ የእስልምና እምነት ተከታይ ብቻ ያለባቸው ሀገሮች ብትሄዱ ይህ ይገጥማችኋል። ስለዚህ ከገበያ የሚገኘውን የቀረበላችሁን በእግዚአብሔር ስም ባርካችሁ ሳትጠራጠሩ መብላት ትችላላችሁ። "ወደምትገቡባትም ከተማ ሁሉ ቢቀበሏችሁ ያቀረቡላችሁን ብሉ" እንዲል (ሉቃ.10፥8)።

፻፶፩. በገጠሩ የሀገራችን ክፍሎች ገበሬው ሰብሉን በረዶ እንዳይመታበት ማሳው ላይ (የሆነ ነገር ያስደርግ እና ምን እንደሆን እንጃ ብቻ) ከዚያም ሰብሉ ካፈራው ላይ በረዶ እንዳይመታው ላደረገው ሰውዬ ይሠጠዋል። ጥያቄዬ የእውነት ተፈጥሮን ማዘዝ ይችላሉ ወይ?

መልስ፦ በመሠረቱ በምድራዊ ጥበብ ሰዎች ተፈጥሮን ማዘዝ አይችሉም። ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔርን ሥራ ለራሳቸው እያስመሰሉና በተፈጥሮ የሚደረገውን ነገር በእነርሱ ኀይል እንደተደረገ እያስመሰሉ የሚያጭበረብሩ ደባትር ነን የሚሉ አጭበርባሪዎች ይኖራሉ። እነዚህ አካላት በረዶ ቢመጣ በኃጢአታችሁ ምክንያት ነው ብለው ወደእኛ ኃጢአት ሲያጠጋጉት፣ በረዶው ሲቀር የእነርሱ የጸሎት ውጤት እያስመሰሉ ያወራሉ። እውነታው ይህ አይደለም። ሰብልን የሚጠብቅ እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ ማፈርም መፍራትም መገዛትም የሚገባው ለእግዚአብሔር ነው። ከዚያ ውጭ መምህራን ለሀገር ደኅንነት ለመጸለይ ክፍያ መጠየቅ የለባቸውም። ስለሀገር መጸለይ ግዴታቸው ነውና።

፻፶፪. መጽሐፈ መነኰሳት ፊልክስዩስ ላይ መቃርስ አንዱን አረሚ ከሞት ካስነሣው በኋላ ያ ያልተጠመቀ ሰውዬ ለምንድን ነው ሁለተኛ እንዲኖር ያልወደደ?

መልስ፦ ይህ ታሪክ ፊልክስዩስ ተስእሎ 148 ላይ ይገኛል። እንግዲህ ያ ሙት እንዳልተጠመቀ ተገልጿል። ተጠምቀህ መኖር ትፈልጋለህ ወይ ሲባል ግን አልፈልግም አለ። ይህ የራሱ ምርጫ ነው። ስለዚህ እንዲህ ያለው ጥያቄ ሊያስጨንቃችሁ አይገባም። ይህኮ የሰውየው ምርጫ ጉዳይ ነው። ሳጥናኤልምኮ በክርስቶስ ሠምራ አማካኝነት ና ውጣ ቢባል አልፈለገም። የሙታንን ምርጫ እናክብር።

፻፶፫. እኔ ዲያቆን ነኝ፣ ዲቁናውን ስቀበል ውዳሴ ማርያም እና ዳዊት ጨርሼ ነበር። ግን ከዚያ በኋላ ለመማር ብዙ ነገሮች አልመቻችልኝ ሲሉ አልቀጠልኩም። ጊዜ አግኝቼ ልማር ስሞክር ግን በተለይ ለዜማ ትምህርት ድምፄ እምቢ አለኝ ከዚያ ተውኩት። አሁን ላይ በዕድሜየ ትልቅ

ሁኜ እገኛለሁ። ዲቁንናየን እንደያዝኩ ነው። ስለዚህ የእኔ ጥያቄ ዲቁናዬ ይቀጥላል አይቀጥልም? ከቀጠለስ እንዴት ይቀጥል/ላገልግል?

መልስ፦ ንጽሕናህን ጠብቀህ ካለህ አዎ ዲቁናህ ይቀጥላል። እግዚአብሔር የድምፅን ማማርና አለማማር አይደለም የሚያይ። ደግ ልብን ይዞ መቀደስን እንጂ። ስለዚህ ድምፅህ ምንም ቢሆን ግብረ ዲቁናውን አጠናክረህ ተምረህ ቀድስ።

፻፶፩. እሑድ ዕለት አካላዊ እንቅስቅሴ ማድረግ ማለትም ስፖርት መሥራት ችግር አለው ይሆን?

መልስ፦ ለቆራብያን አዎ ችግር አለው። ምክንያቱም ከሰውነታቸው ብዙ ላብ ስለሚወጣቸው መሥራት የለባቸውም። ሌላው ሰው ግን ቅዳሴ አስቀድሶ፣ ቃለ እግዚአብሔርን ተምሮ ብዙ መድከም ሳይኖርበት አካላዊ እንቅስቃሴ ቢያደርግ ምንም ነውርነት የለውም። ለስፖርቱ ብሎ ከቅዳሴ ከቀረ ግን ትልቅ ነውር ይሆንበታል።

፻፶፪. ባል እና ሚስት አንዳቸው ለመቍረብ ፈልገው አንዳቸው እምቢ በማለቱ መቍረብ የፈለገው አካል በሞት ቢለይ ተጠያቂው ማን ነው?

መልስ፦ ባልና ሚስት መቍረብ በፈለጉበት ጊዜ በየሚመቻቸው ጊዜ መቍረብ ይችላሉ። አንዱ ካልፈለገ የፈለገው መቍረብ አለበት። እንጂ ሌላውን መጠበቅ አይጠበቅበትም። ባስልዮስ ጸልዮ ያዳነው ባርያ ታሪክ በጥቂቱ ይህንን ያሳውቀናል። እርሷ ትቆርብ ነበር። ባሪያው ግን በኋላ በባስልዮስ ጸሎት እስኪቆርብ ርቆ ነበር። መቍረብ የፈለገው አካል ቢሞት ተጠያቂው ማን ነው የሚለውን ጥያቄ ለእግዚአብሔር እንተውለት። ምናልባት ጠያቂው የጥፋተኝነት ስሜት ተሰምቶት ዕረፍት አጥቶ ከሆነ ንስሓ አባቱን አማክሮ ከእንዲህ ያለ የጥፋተኝነት ስሜት ነጻ መውጣት ነው። የሚያስጨንቅ ነገር የለም።

፻፶፫. ሁለት እጮኛሞች ቢኖሩ እና አንደኛው በዘመኑ ያሉትን የሐሰተኛ አጥማቅያን ደጋፊ ቢሆን አንደኛዋ ደሞ በፍጹም ሐሰተኛ ናቸው ብትልና ለወደፊት ቢጋቡ ይሻላል ወይስ ቢተውት ምን ይመክራሉ?

መልስ፦ በመሠረቱ የጋብቻ አገናኝ ኤጀንሲ አይደለሁም። ነገር ግን የሚጋቡ ሰዎች የጾታ ብቻ ሳይሆን የአመለካከት ልዩነትንም ይዘው ሊጋቡ ይችላሉ። ስለዚህ በአጥማቅያን ዙሪያ ልዩ ልዩ አመለካከት ቢኖራቸው ይህንን ልዩነት በፍቅር አጥብበው መኖር ከቻሉ መኖር ነው። በዚህ መግባባት አንችልም ካሉ እነዚህ ሰዎች እንዴት ነው አንድ ላይ መኖር የሚችሉት?!። በቃለ እግዚአብሔር መሠረት ይመሩ። የግለሰቦች ደጋፊና አንጃ በመሆን ለምን ይጣላሉ! እና ከላይ ለተጠቀሱት ሰዎች የምመክረው መጀመሪያ የግለሰብ አንጃ ከመሆን ውጡና ክርስቲያን ሁኑ የሚል ነው። ክርስቲያን ያለፉ ቅዱሳንን፣ ራሱን ክርስቶስን አርአያ ያደርጋል እንጂ ባልሞተ ሰው መከራከር የለበትም።

፻፶፯. መጀመርያ በምኖርበት አከባቢ የንስሓ አባት ነበረኝ። ከዚያ ለትምህርት ወደሌላ ቦታ ሄጄ ሌላ የንስሓ አባት አሉኝ። እና ክረምት ሲሆን ወደ ቤቴ ስመለስ ከዚያ ባሉት ካህን ንስሓ መግባት እችላለሁ?

መልስ፡- ይቻላል። ሰው ከኀጢአቱ መሞት ስለሌለበት ሌላ ሀገር ሲሄድ ከሌላ ሀገር ንስሓ አባት ይይዛል። ኀጢአታችሁን አታሳድሩ ስለተባለ በሄደበት ሀገር የንስሓ አባት አበጅቶ ለዚያ መናዘዝ ይገባዋል።

፻፶፰. አሁን ያለው ሲኖዶስ ቅዱስ ሲኖዶስ ነው ማለት እንችላለን። ከሥራው ከድርጊቱ ከወቅቱ አንጻር?

መልስ፡- አሁን ያሉትን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ጳጳሳትና ጉባኤያቸውን በእምነት ደረጃ እንደ ኬልቄዶናውያን ሌላ እምነት ስላልመሠረቱ ቅዱስ ሲኖዶስ እንላቸዋለን። በምግባር ደረጃ ብዙ ጥፋት አጥፍተዋል፣ እያጠፉም ሊገኙ ይችላሉ። ይህንን መዓርግ ይዘው ባጠፉት ጥፋት ራሱ እግዚአብሔር ይጠይቃቸዋል። በእነርሱ ኃጢአት ራሱ ይጠይቃቸው።

፻፶፱. ፍትሐ ነገሥቱ ያለ ሥርዓት በሕገ ወጥ የሾመውን ጳጳስም ይሁን ሊቀ ጳጳስ ሿሚውም ተሿሚውም ይሻር ከተመለሰም ሕዝባዊ ሆኖ ያገልግል የሚለው በሲኖዶሱ በኩል ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ ተሸሯል። ስለዚህ ማንኛውን እንከተል ሲኖዶሱን ወይስ ፍትሐ ነገሥቱን? ይህ ሲኖዶስ ከጉባኤ ኬልቄዶን የሚለይበት ምንድን ነው? መለካዊ አልሆነም ወይ?

መልስ፡- ጉባኤ ኬልቄዶን ዶግማውን በነገሥታት ጫና የቀየረ ስለሆነ ተወግዞ ተለይቷል። በሀገራችን የወሊሶውም፣ የአክሱሙም፣ የቆጋውም ሹመት ሕገ ወጥ ሹመት ነው። በመሆኑም በወቅቱ ቅዱስ ሲኖዶስ አውግዞ ለይቶታል። ሐዋርያት ደግሞ በሲኖዶሳቸው አንድ ሰው ከተሻረ በኋላ የክህነት ሥራ ከሠራ ለዘለዓለሙ ከክህነት ይሻር ብለዋል። በሐዋርያት ሲኖዶስ መሠረት ከሆነ የወሊሶውም የአክሱሙም ተሿሚዎች ሕዝባዊ ጨዋ ሆነው መኖር ይገባቸው ነበር እንጂ በክህነታቸው መቀጠል አይችሉም። ነገር ግን ቅዱስ ሲኖዶስ እንደየዘመኑ ሁኔታ ቀኖናን የማሻሻል ሥልጣን ስላለው በወቅቱ ሲኖዶሱም ቀኖናን በቀኖና አሻሽለን ነው ከወቅቱ ጋር ይህንን ያደረግነው ስላሉ ራሱ ሲኖዶስ ይጠየቅበት። ሌላው ሰው ግን በዚህ ምክንያት የሚቀርበት ነገር የለም። በእምነቱ ጸንቶ ይቀጥል።

፻፷. ንስሓ እገባለሁ ከዚያ ቀኖናዬን ስጨርስ የንስሓ አባቴ ስደውልላቸው አያነሱልኝም። ፍተሐት ዘወልድ ሳይደረግልኝ ይቀራል። አንድ ጊዜ ብቻ አይደለም ሁልጊዜ ነው። እኔ ደግሞ ተስፋ እቆርጣለው። አሁን ደግሞ ኃጢአት ስሠራ እዳልሠራሁ ሆኖ ይሰማኛል። እንዴት ነው ከልቤ መጸጸት የምችለው?

መልስ፦ በማናቸውም ጉዳይ ተስፋ መቍረጥ አይገባም። ንስሓ አባትሽ አልመቻቸው ካለ በግልጽ ተናግሮ እንዲያስናብቱሽ መንገር ነው። ከዚያ ሌላ ንስሓ አባት መያዝ ነው። ኃጢአት ስሠራ እንዳልሠራሁ ሆኖ ይሰማኛል የሚለው ኃጢአትን ደጋግመው ሲሠሩት የሚሰማ ስሜት ነው። ስለዚህ ሞት እንዳለ፣ ዘለዓለማዊ ስቃይ እንዳለ በማሰብ ከእንደዚህ ዓይነት ቸልተኝነት ነጻ መውጣት ይገባል። የሚደርስብንን ቅጣት በማሰብ፣ ለእኛ ሲል ክርስቶስ የተቀበለውን መከራ በማሰብ ለመጸጸት መሞከር ይገባል።

## ፻፷፩. አንድ ሰው ሰው ገድሎ ለቄስ ንስሓ ቢገባ ካህኑ ያንን ወንጀል ለፖሊስ የመናገር ግዴታ አለበት ወይስ ምስጢር መጠበቅ?

መልስ፦ ካህን የልጆቹን ምሥጢር ጠብቆ መኖር አለበት እንጂ የልጆቹን በደል ለሌላው መናገር የለበትም። ስለዚህ አንድ ሰው ምንም ያህል ወንጀል ቢሠራ በክፉ ሥራው ተጸጽቶ እስከመጣ ድረስ የነፍስ ድኅነትን ይሰጠው ዘንድ ቀኖና ሰጥቶ ዝም ማለት አለበት። የምእመናንን ምሥጢር እስከ መቃብር ይዞት መውረድ እንጂ ትንፍሽ ማለት የለበትም።

## ፻፷፪. ድምፅ የሌለው ሰው የድምፅ ዕፅ ቢጠቀም ኃጢአት አለው?

መልስ፦ ማንኛውም ዕፅ ለሰው አገልግሎት ይሰጥ ዘንድ ተፈጥሯል። ስለዚህ ለምግብነት፣ ለመድኀኒትነት፣ ለልብስነትና ለመሳሰሉት መጠቀም እንችላለን። ነገር ግን ስመ አጋንንትን በመጥራት ዕፀዋትን የምንጠቀማቸው ከሆነ ሥር ማሽ፣ ቅጠል በጣሽ ያሰኙናልና አልተፈቀደም። ሰው በተፈጥሮ በተሰጠው ድምፅ እግዚአብሔርን እንዲያገለግል እንጂ የሌለውን ነገር መሻት የለበትም። ነገር ግን በበሽታ ምክንያት ድምፁ ተዘግቶ የነበረ ሰው ካለ የዘጋውን ነገር የሚቀንሱ ወይም የሚያስወግዱ ዕፀዋት ካሉ በመድኀኒትነት መውሰድ ይችላል። ለድምፅ ጥራት የሚጠቅሙ እንደማርና የመሳሰሉት በሕክምናው ዘርፍም የሚታወቁ መድኀኒቶችን እንደሁኔታው ሊጠቅም ይቻላል። ብዙ ጊዜ ግን የቅኔ፣ የድምፅ ወዘተ እየተባሉ የሚሰጡት ሰይጣናዊ ድግምትን በመድገም የሚደረጉ በመሆናቸው በራሳችን ድምፅ እግዚአብሔርን ማገልገል ብንችል እላለሁ። እግዚአብሔርን ባለን ድምፅ ብናመሰግነውም ጸጋውን አትረፍርፎ ይሰጠናልና።

## ፻፷፫. ዶግማ ቀኖናዋና ሥርዓቷ ሲጣሱ የማስተካከል ኃላፊነት ያለበት አካል ማን ነው? ሲኖዶስ ወይስ የሊቃውንት ጉባኤ?

መልስ፦ ሥርዓትን ማስተካከል፣ ማሻሻል፣ መለወጥና የመሳሰሉ ነገሮችን የማድረግ ኀላፊነት የቅዱስ ሲኖዶስ ነው። የሊቃውንት ጉባኤ ለቅዱስ ሲኖዶስ ግብአት መስጠት ይችላል እንጂ ራሱ ወሳኝ አይሆንም።

## ፻፷፬. ቅዱሳት ሥዕላትን በሚመለከት የእኛ የሆነውንና ያልሆነውን መለያ ሥርዓት የለንም?

መልስ፦ በዚህ ዙሪያ የተጻፈ አላገኘሁም (በራሪ መጻሕፍትን ባገኝም ለምስክርነት የሚቀርቡ ስላልሆኑ ትቻቼው ነው)። አንዳንዶች ግን ቅዱሳት ሥዕላትን ቤተክርስቲያን ከገቡ በኋላ ልክ አይደለም እያሉ ሲተቹና ንቀው ሲያልፉት ይስተዋላል። እንደ እኔ እንደ እኔ አንድ ሥዕል ኦርቶዶክሳዊውን አስተምህሮ የማይሽር ሆኖ ከተገኘና አስተማሪነቱ የጎላ ከሆነ መናቅ አይገባም ባይ ነኝ። የኢትዮጵያ የአሳሳል ትውፊት ከግብጽ የተለየ ሊሆን ይችላል። ሁለታችንም ግን በዶግማ አንድ ነን። ስለዚህ የሁሉንም አክብረን መኖር ነው። ዙሮ ዙሮ መረዳት ያለብን ግን ቅዱሳት ሥዕላት የተሳለለትን ቅዱስ ሙሉ ቁመናና መልክ የሚገልጹ እንዳልሆኑ ነው። የቅዱሳንን ገድላቸውን በማንበብ ታሪካቸውን መሠረት አድርገን እንሥለዋለን። ሥዕሉ ከአስተማሪነቱ ይልቅ ተነቃፊነቱ ጎልቶ የሚታይ ከሆነ መተው ነው። በጠቅላላው በዚህ ዙሪያ ቀኖና ቢሠራ መልካም ይሆናል።

፻፸፫. ካህናት (ቀሳውስት እና ዲያቆናት) ሚስቶቻቸው በተለያየ ምክንያት ይሞታሉ (ልጅ ቢወልዱም ባይወልዱም)። ከዚያ በኋላ፣ የካህናቱ ሕይወት፣ በተለይ የክህነት ሕይወታቸው እንዴት ነው የሚሆነው? በአገልግሎታቸው ይቀጥላሉ ወይስ መመንኮስ ይኖርባቸዋል?

መልስ፦ የግድ ይመንኩስ የሚል አስገዳጅ ሕግ የለም። ስለዚህ ሌላ ሳያገባ ክህነቱን ጠብቆ ልጆቹን እያሳደገ መኖር ይችላል። ከመነኰሰ ወደ ገዳም ይሄዳል። ይህን ጊዜ ደግሞ ልጆቹ አሳዳጊ ያጣሉ። ስለዚህ ሌላ ሳያገባ በክህነቱ እያገለገለ ልጆቹን እያሳደገ መኖር ይችላል። ፈተናውን አልችለውም አግብቼ እኖራለሁ ካለም ክህነቱ ፈርሶ ሌላ አግብቶ ሊኖር ይችላል።

፻፸፬. ሁለት እጮኛሞች በአምስት እና በአራት ዘውግ የሥጋ ዝምድና ቢኖራቸው መጋባት ይቻላል ወይስ አይቻልም? ከመንፈሳዊ ሕይወት ላይ ምን የሚያመጣው ጉዳት ስላለ ነው ይህ ሥርዓት የወጣው?

መልስ፦ እንደፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ገለጻ በሀገራችን በሴቲቱ ስድስት ወገን፣ በወንዱ ስድስት ወገን ሆኖ በሰባተኛው መጋባት ይቻላል። በአምስትና በአራት ግን አይቻልም። ይህ ሁሉ ሰውን ለማዛመድ ነው። ይህ ግን ቀኖና ስለሆነ በቅዱስ ሲኖዶስ ሊሻሻል ይችላል። መንፈሳዊ ሕይወት ለእግዚአብሔር ሕግና ሥርዓት በመገዛት ይገለጻል። ስለዚህ እንደ ሥርዓቱ ከተመራን ዋጋ እናገኛለን። ሥርዓቱን ትተን በራሳችን ፈቃድ ከተመራን ግን ከእግዚአብሔር ሕግ ይልቅ ራስ ወዳድነት ሰልጥኖብናል ማለት ነው። ይህ ደግሞ ጉዳት ነው።

፻፸፯. አብዛኛው ትዳር የሚመሠረተው ከሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ውጭ ነው። በዚህ መንገድ ተጋብተው ልጅ ሀብት ያፈሩም አሉ። ይህን ጋብቻ ቤተ ክርስቲያን ታውቀዋለች ወይ? ካለወቀችው በምን መንገድ ነው ወደ ቤተ ክርስቲያን ዕውቅና የሚመጣው?

መልስ፦ ጋብቻ የሚከናወነው በቍርባን ስለሆነ ቅድስት ቤተክርስቲያን ታውቀዋለች። ከሥርዓተ ቤተክርስቲያን ውጭ የሚደረጉ ግን መኖር የለባቸውም። አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ግን ብዙዎች ያለ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ተጋብተው ልጆችን ወልደው ይኖራሉ። ስለዚህ ይህንንና የመሳሰለውን ጉዳይ ቅዱስ ሲኖዶስ የሚያስተካክልበት መንገድ ወይም ይሁንታ የሚሰጥበት መንገድ ቢኖር መልካም ነው።

፻፳፰. አዲስ ቆራቢ የሆኑ ምእመናንን የመቀደሻ ካባ ወይም መጎናጸፊያ ያላብሷቸዋል። እና ይህ ልክ ነው ይላሉ?

መልስ፦ ይህ እንኳ ልማድ ነው እንጂ መጽሐፋዊ መሠረት የለውም። በቍርባን ጊዜ ባልና ሚስት አንድ መጎናጸፊያ ለብሰው የሚቆርቡት የጋብቻቸው ቀን ነው። በሌላው ቀን ግን ወንዱም በወንዶች መቆሚያ ሆኖ ይቀበላል፤ ሴቲቱም በሴቶች መቆሚያ ሆና ትቆርባለች።

፻፳፱. አንዱ በቁርባን ሌላው በተክሊል መጋባት ይቻላል?

መልስ፦ አዎ ይቻላል። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ላይ ተገልጿል። ድንግልናውን ጠብቆ የኖረው ሰው በረከተ ተክሊልን ያገኝ ዘንድ ተክሊል ሲያደርግ ያልጠበቀው ደግሞ ያለተክሊል ሆኖ ይጋባሉ። ለድንግሉ መጽሐፈ ተክሊል ይደገምለታል።

፻፴. አንድ ሰው ንስሓ ሊገባ የንስሓ አባቱን አግኝቶ ግን ንስሓ ለመግባት መምጣቱን ብቻ ጠይቆ ኀጢአቱን ሳይናዘዝ ቄሱ ቀኖና ሰጠው። ሲጨርስ መጥተህ ተፈታ አለው። ይህ ሰው ምን ማድረግ አለበት?

መልስ፦ ይህ የተግባቦት ችግር ነው። የቄሱም የልጁም ችግር ነው። ቄሱም ሳይሰማ ቀኖና መስጠት የለበትም፤ ልጁም በደሉን ሳይናገር ዝም ብሎ መሄድ አልነበረበትም። በግልጽ መነጋገር ነው። ንስሓ የሚገባው ሰውም የበደልኩት በደል ይህ ይህ ነው ብሎ ገልጾ መንገር ነው። በኋላም ቢሆን መጠየቅ ነው። ሳልናዘዝ ለምንድን ነው ቀኖና የተሰጠኝ ብሎ መጠየቅ አለበት።

፻፴፩. አንድ ክርስቲያን የክርስትና ስሙን ቢረሳ (ከመጀመሪያው የማያውቅ ቢሆን) ወይም የእርሱ ለመሆኑ ቢጠረጠር ምን ማድረግ አለበት?

መልስ፦ የክርስትና አባቱ ስሙን መዝግቦ መያዝ አለበት። ነገር ግን ከተረሣና ካልታወቀ የንስሓ አባቱ እንደገና መሰየም ይችላል።

፻፴፪. ልጁ ዲያቆን ነው። ፍቅረኛ አለችው። ሁለቱም በቅርብ ጊዜ መጋባት ይፈልጋሉ። ነገር ግን የእርሷ ቤተሰቦች በሀገሩ ባህል መሠረት  ሽማግሌ መጥቶ ደጅ ጠንተው፣ ጉልበት ጫንቃ ስመው እንጂ አንቺ በፈቃድሽ የምታመጪውን ባል አንቀበልሽም አሏት። ምን ይሻላል መምህር?

መልስ፦ ልጂቱ ራሷን የቻለች ከሆነች የፈለገችውን ወንድ በፈለገችው መንገድ ማግባት ትችላለች። በቤተሰብ ሥር ካለች ግን የእርሷ መፈለግ ብቻ ሳይሆን ቤተሰብም መፍቀድ ይገባቸዋል። ከዚህ ያለውን የአመለካከት ክፍተት በካህናት፣ በሽማግሌዎች ማግባባት ቢቻልና ከተዋደዱ ቢጋቡ መልካም ነው።

፻፸፫. አንድ ነገር እውነት መሆኑን የምናውቀው በማስረጃ ነው ወይስ በእምነት?

መልስ፦ በማስረጃም በእምነትም። በማስረጃ የሚታወቅ እውነት አለ። በእምነት የሚታወቅ እውነትም አለ።

፻፸፬. የሰንበት ውሃ ወደ ቤት አይገባም የሚባል እንዴት ነው?

መልስ፦ ይህ በገጠሪቱ ቤተክርስቲያን ሰንበትን የማክበር መገለጫ ተደርጎ ይታሰባል። ሆኖም በሰንበት የሚበላ የሚጠጣ ነገርን መሥራት አልተከለከለም። እንጀራ መጋገር፣ ወጥ መሥራት፣ ሻይ ቡና ማፍላት፣ የሚጠጣ ውሃ ከሌላ የምንጠጣውን መቅዳትና ከቤት ማስቀመጥም ይቻላል።

፻፸፭. አንድ ሰው በልጅነት አእምሮው በተለያየ ምክንያት በቂ ትምህርት ሳይማር ዲቁና ይሾማል። ለምሳሌ ወደ ደቡብ ገጠራማ አከባቢ ካለው አገልጋይ እጥረት የተነሣ ትንሽ ነገር ይማርና የቀረውን ዲቁና ከተሾመ በኋላ ይማር ተብሎ ይሾማል። ይህ ነገር እንዴት ይታያል?

መልስ፦ ብዙ አገልግሎትን ይሸፍን ዘንድ አንድን ሰው ለአገልግሎት የሚሆነውን ያህል ተምሮ ሌላውን በኋላ ይማር ተብሎ መሾሙ መልካም ነው። በኋላ እያገለገለ መማርና በደንብ ማወቅ ግን ይገባዋል። ይህንን እንደሁኔታው የክፍሉ ጳጳስ ይወስነዋል።

፻፸፮. የ35 ዓመት ጎልማሳ ነኝ። በሰንበት ትምህርት ቤት እንዲሁም በግቢ ጉባኤ አልፌያለሁ። መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት በጥቂቱም ቢሆን እንዳውቅ አስችሎኛል። ነገር ግን ከግቢ ከወጣሁ በኋላ በሥራ ምክንያት ከአገልግሎትም ከማገልገሉም እየራቅሁ ነው። መርከበኛ ነኝ። ከድሮም እግዚአብሔር ቢፈቅድ በሥርዓተ ተክሊል ባይሆን እንኳ በሥጋ ወደሙ ሥነ ሥርዓት ጋብቻዬን እፈጽማለሁ ብዬ ለራሴ ቃል ገብቼ መታበይ ያይደለ እስከዛሬ ራሴን ጠብቄ ቆይቻለሁ። በቅርቡ ከአንዲት ልጅ ጋር ተዋወቅሁ። እርሷም ከእኔ በፊት ጓደኛ እንደነበራት ነግራኛለች እኔም አውቃለሁ። ነገር ግን ለእርሷ ጥሩ ስሜት ስላለኝ በሥጋ ወደሙ ጋብቻችንን እንድንፈጽም ጠይቂያት ነበር። እርሷ ግን ፈቃደኛ አልሆነችም። እርሷም ከዚህ በፊት በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የማግባት ፍላጎቱም ሐሳቡም አልነበረኝም፣ ምንም ከአንተ በፊት ከሌላ ሰው ጋር ብቆይም እስካሁን የሥጋ ድንግልናየን ጠብቂያለሁ። ነገር ግን አንዳንድ የማይደረጉ ነገሮችን ስላደረግሁ በተክሊል ማግባት አልችልም አለች። በሥጋ ወደሙ ብንጋባ ጥሩ ነበር። ግን ቤተሰቦቼ ከእኔ ይህን አይጠብቁም። እኔ እራሴን ጠብቄ እንዳለሁ ስለሚያስቡ ያ እኔን ያስጨንቀኛል። ስለዚህ በዓለማዊ ሥርዓት ከተጋባን በኋላ ሥጋ ወደሙን ብንቀበል ይሻላል ብላ

ታስባለች። ይህን ደግሞ እኔ በፍጹም መቀበል አልቻልኩም። እንደ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ሥርዓት ቀኖና ምን ባደርግ ይሻላል?

መልስ፦ የክርስቶስ ሥጋንና ደምን በመቀበል ጋብቻ መደረግ እንዳለበት ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ላይ ተገልጿል። ስለዚህ ልጂቱ ይሉኝታዋን ትታ እግዚአብሔርን አክብራ በቤተክርስቲያን ሥርዓት ብታገባ ዋጋዋ ይበዛል። የግንዛቤ እጥረት ሊሆን ስለሚችል ስለምሥጢረ ተክሊል በደንብ ብትማር። ሌላው ደግሞ ቤተሰብ ይታዘበኛል ከሚለው ይልቅ ያለ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ቢሆን እግዚአብሔር ያየኛል ብትል የተሻለ ነው። ተክሊል የሚከለክል ነገር አድርጌያለሁ ብላ ካሰበች ደግሞ በቁርባን ብታገባ መልካም ነው። ፍቅረ ቤተሰብ ይቀንስብኛል ብላ ፍቅረ እግዚአብሔርን ማፍረስ የለባትም። መዋደዱ ካለ በምክረ ካህን ተነጋግራችሁ ተማምናችሁ አድርጉት።

፻፸፯. በጥምቀት ሰዓት መጠመቂያ ባሕር ላይ እሳት አብርተው ይለቃሉ። ትርጉሙ ምንድን ነው?

መልስ፦ እሳተ መለኮት የሆነ ጌታ በውሃ መካከል ቆሞ መጠመቁን ለማመልከት ነው። "ነድ ለማየ ባሕር ከበቦ ባሕር ኀበ የሐውር ጸበቦ" እንዳለ ቅዱስ ያሬድ።

፻፸፰. አንድ ዲያቆን (ቄስ) ክህነቱን ቢያፈርስ ቤተ መቅደስ ገብቶ መቀደስ አይችልም። ይህ የታወቀ ነው። ነገር ግን ክህነቱን ማፍረሱ ከኃጢአት ይቆጠርበታል?

መልስ፦ አዎ ክህነትን ማፍረስ ራሱን የቻለ ኃጢአት ነው። ያፈረሰበት መንገድ ራሱ ኃጢአት ነው። ኃጠአት ማለትኮ ማጣት ማለት ነው። ይህም ጸጋ እግዚአብሔርን ማጣት ነው። ከጸጋ እግዚአብሔር አንዱ ደግሞ ክህነት ነው።

፻፸፱. የሰው ልጅ የራሱ የሆነ ቅሬተ አካል አለው የሚለው ሐሳብ ስሕተቱ ምንድን ነው?

መልስ፦ የሰው ልጅ የራሱ የሆነ ቅሬተ አካል አለው የሚለው ሐሳብኮ ትክክል ነው በዚህ ምንም ተቃርኖ የለም። ችግሩ የሰው ይሁን አይሁን ጥልቅ ጥናት ሳይጠና አንድን ሀገር የሰው ልጅ መገኛ ማለቱ ላይ ነው። ዓለም ሁሉ ሳይቆፈር ከአንድ ቦታ በተገኘ ዐፅም መሠረትነት ያንን ቦታ በዚያ ምክንያት የሰው መገኛ ማለት ሳይንሳዊም አይደለም ከእውነትም የተቃረነ ነው።

፻፹. ወልድ በተሰቀለ ጊዜ አብና መንፈስ ቅዱስ የት ነበሩ?

መልስ፦ አሁን ካሉበት።

፻፹፩. የሥጋ ወንድማማቾች ከአንድ ቤተሠብ የሥጋ እኅትማማቾችን ማግባት ይችላሉ?

መልስ፦ አይችሉም። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 24 ላይ እንደተገለጸው ይህ የጋብቻ ዝምድና ስለሆነ መጋባት አይገባም። የሙሽራው ዘመዶችና የሙሽሪት ዘመዶች ተዛምደዋልና መጋባት የለባቸውም።

፻፹፪. እኔ ባለሁበት አካባቢ የቤተክርስቲያን አገልጋይ አባት ከሌላ ቦታ መጥተው ተቀጥረዋል የሚናገሩት አማርኛ ነው። የአካባቢውን ቋንቋ ግን አይችሉም ሌላ ካህንም ከአጥቢያው የለም። የእኔ ጥያቄ አማርኛ የማይችሉ የንስሓ ልጆቻቸው በአስተርጓሚ ነው ንስሓ መግባት የሚችሉት ወይስ በዚያው ተናግረው ይሰጣቸዋል?

መልስ፦ በመሠረቱ ጌታ በጰራቅሊጦስ ለሐዋርያት ቋንቋ የገለጠበት ምክንያት ሁሉንም በቋንቋው ማስተማርና ማገልገል እንደሚገባ ለማስተማር ነው። ስለዚህ አገልጋዮች የሚያገለግሏቸውን ሕዝቦች ቋንቋ መቻል ይገባቸዋል። በአስተርጓሚ ንስሓ መግባት ያሳቅቃል። ነገር ግን ሌላ መንገድ ከሌለ ከሚሰበር ይሰንጠር ነውና በአስተርጓሚም ቢሆን ንስሓ ገብተው ከኃጢአት ነጻ መሆን ይገባቸዋል። ከዚህ ሁሉ ግን ቋንቋውን የተማረ ካህንን የንስሓ አባት ማድረግ ይገባል።

፻፹፫. የታሰረን የጠየቀ፤ የሚያስፈታ በእግዚአብሔር ዘንድ መልካም ነው። ማስፈታት ሲባል በምን መልኩ ነው? ትክክል ባልሆነ መንገድም ቢሆን ነው? ደግሞስ ወንጀለኛን ነው ወይስ ያለወንጀል የታሰረን?

መልስ፦ ማስፈታት የሚለው ዋስ ሆኖ በዋስ ማስፈታትን የሚመለከት ነው እንጂ ሌላ ኃጢአት ሠርቶ ማስፈታትን አይደለም። ወንጀለኛንም ቢሆን ካሣ ክሦን ማስፈታት እንችላለን። ለቀጣይ ወንጀል እንዳይሠራ ፍቅርን ማስተማር ይገባል። በእነዚህ ነገሮች መፈታት የማይችል ከሆነ እየሄዱ መጠየቅ ነው።

፻፹፬. ከባለቤቴ ጋር ተጋብተን ሦስት ልጆችን አፍርተናል። ነገር ግን ምንም ዓይነት ሰርግም ሆነ የቤተክርስቲያን ሥርዓት አላደረግንም አልቆረብንምም። አሁን ስሰማ ጋብቻ የግድ በቅዱስ ቁርባን መሆን አለበት። ስለዚህ እንደ አዲስ መጋባት ይኖርብናል ማለት ነው?

መልስ፦ እንደፍትሐ ነገሥቱ ከቁርባን ውጭ የተደረገ ጋብቻ ከጋብቻ አይቆጠርም ይላል። ነገር ግን በተግባር የሀገራችን አብዛኛው ሕዝብ አንተ እንዳልከው ነው። እንዲህ ያደረገ ሰው ምን ማድረግ እንዳለበት የሚገልጽ መፍትሔ ተገልጾ አላየሁም። ስለዚህ ቅዱስ ሲኖዶስ በዚህ ጉዳይ ቋሚ አሠራርን እስኪዘረጋ ድረስ በነበረው ሁኔታ ቀጥሉ። ንስሓ እየገባችሁ ሥጋዉን ደሙን እየተቀበላችሁ በፍቅር መኖርና ልጆችን ማሳደግ ነው።

፻፹፭. የቆረበ ሰው ምግብ ሳይበላ አይናገርም ይባላል። በመሐል ሰው ግዴታ ማናገር ቢኖርብኝስ?

መልስ፦ እውነት ነው በትውፊት የቆረበ ሰው መክለፍት ወይም ሌላ ምግብ እስኪቀምስ ድረስ አይነጋገርም። ምሥጢሩ አፍን ከመሸፈን ጋር ይያያዛል። ይኸውም ተሐዋስያን ወደ አፋችን እንዳይገቡ ነው። ቃለ እግዚአብሔርን መነጋገር፣ አስቸኳይ ጉዳይ ከገጠመም ቀስ ብሎ መነጋገር አይከለከልም። ካህናት ከቆረቡ በኋላ ቃለ እግዚአብሔርን መጮኻቸው፣ ሰባክያን መስበካቸው ለዚህ ማስረጃ ይሆናል።

፻፹፮. በአሁኑ ወቅት ራሱን መንበረ ሰላማ ብሎ የሰየመው የትግራዩ ሲኖዶስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቅዱስ ሲኖዶስ ተወግዞ መለየቱ ይታወሳል። አሁን እኔ መጠየቅ የምፈልገው ትግራይ ያሉ አብያተ ክርስቲያን ለምሳሌ አክሱም ወይም የመሳሰሉት ለመሳለም ሄደው ሥጋ ወደሙ መቀበል ይቻላል ወይ?

መልስ፦ ፍትሐ ነገሥቱ ላይ ከተወገዙ ሰዎች ጋር በአንድ ላይ መጸለይ እንደማይገባ ተገልጿል። "ወኢይደሉ ጸሎት ምስለ ካህን ውጉዝ ወኢምስለ ዘኢየአምን። ወዘጸለየ ምስለ እሉ ይትመተር" እንዲል (አንቀጽ 14)። ስለዚህ ከተወገዙት ጳጳሳት ውጪ ያሉ ካህናት ሲቀድሱ ሥጋውን ደሙን መቀበል ይገባል እንጂ የተወገዙት ካሉ ከእነርሱ ምሥጢር አለመሳተፍ ነው።

፻፹፯. ዲያቆን ሆኖ ስፖርት መሥራት ይፈቀዳል። ለምሳሌ ክብደት ማንሳት፣ ማርሻል አርት፣ ሩጫ፣ ቦክስ መጋጠም፣ ቴኳንዶ እና ሌሎችንም?

መልስ፦ ቦክስ መጋጠም አይችልም። ዱላ ገጥሞ ሌላውን ለመጉዳት ሳይሆን አስተምሮ ሊያድን ነው ክህነቱን የተቀበለውና። ሌላው የስፖርት ዓይነት ደግሞ ስፖርት የሚሠራበት ዓላማ ይወስነዋል። ቴኳንዶ የሚሰለጥን ሌላውን ሰው ገንጭሎ ለመጣል ከሆነ አይቻልም። ነገር ግን ከላይ ያሉትን የስፖርት ዓይነቶች ለራሱ ጤንነት፣ ከተፈጥሯዊ ጠላቶች ከእባብ ከአራዊትና ከመሳሰለው ለማምለጥ ወይም ሌሎችን ለማስመለጥ የሚሰለጥናቸው ከሆነ በደል አይሆኑበትም።

፻፹፰. የሰው ልደት ማክበር በቤተ ክርስቲያን ይፈቀዳል? ለምሳሌ የእኅቴን፣ የወንድሜን፣ የልጄን ወዘተ።

መልስ፦ በልደት ዙሪያ የሚፈቅድም የሚከለክልም በቅዱሳት መጻሕፍት አላገኘሁም። በትርጓሜ ግን ልማደ አሕዛብ እንደሆነ ተገልጿል። ሰው የተወለደበትን ቀን አስቦ ዓመታትን ሰጥቶ፣ ዕድሜን ጨምሮ የሰጠውን አምላክ ቢያመሰግን ግን ምንም በደል የለውም።

፻፹፱. አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር ስንል አብን ብቻ ነው የምንጠራው?

መልስ፦ አይደለም። በዚህ ጊዜ አባታችን ሆይ የምንለው ሦስቱንም በአንድ ላይ አዋሕደን ነው። እኛን በጥምቀት በጸጋ የወለዱን ሦስቱም በመሆናቸው ለእኛ አባታችን መባል ለሦስቱም ይገባል (ማቴ.28፥19)።

**፳፯. ሥላሴ ብላችሁ የሦስት ሽማግሌዎች ሥዕል ላይ ትሰግዳላችሁ። ግን መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል አብና ወልድ ደግሞ በተለያየ እይታ ነው ሦስትነታቸው የተገለጸው። ታድያ የሦስት ሽማግሌዎች ሥዕል ከየት አምጥታችሁ ነው ለሚሉን ምን እንመልስ?**

መልስ፦ በመሠረቱ ሥላሴ ረቂቃን በመሆናቸው በሥዕል መሣል አይችሉም። ወሰን የሌለባቸው በመሆናቸው ወሰን ባለበት ወረቀት ወሰን ባለው አካል መሳል አይችሉም። ነገር ግን ሥላሴ በባሕርያቸው መሳል ባይችሉም በዘፈቀደ በተገለጹባቸው ሊሣሉ ይችላሉ። በዘፈቀደ ከተገለጹበቸው ልዩ ልዩ መንገዶች አንዱ ለአብርሃም ሦስት ሰዎች መስለው የታዩበት ነው። እኛ በሦስት ሽማግሌዎች አምሳል የምንሥለው ሥዕለ ሥላሴ ይህንን መሠረት ያደረገ ነው። በጥምቀት የተገለጹበትን ለመግለጽ ደግሞ ወልድን በተዋሐደው ሥጋ በተገለጠበት በውሃ ሆኖ፣ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ሆኖ ይሳላል።

**፳፰. አንድ ዲያቆን ከተወለደ ጀምሮ ምንም ዓይነት የንስሓ አባት ሳያበጅ እና ንስሓ ሳይገባ ቆይቶ ዲቁና ሲቀበል ከጳጳሱ የሚሰጠው ንስሓ በቂ ነው ወይስ የነፍስ አባት አበጅቶ ንስሓ መግባት ይጠበቅበታል?**

መልስ፦ ማንኛውም ሰው ንስሓ አባት ሊኖረው ይገባል። ማናቸውም ምሥጢራት ማሰሪያቸው ቅዱስ ቊርባን ነው። ወደ ቅዱስ ቊርባን የምንቀርበው ደግሞ ንስሓ ገብተን ነው። ስለዚህ ዲቁና እስከሚቀበል ድረስ ንስሓ አባት ካልነበረው ዲቁና ሊቀበል ሲሔድ ጳጳሱ እንደ ንስሓ አባት ሁሉን በደሉን ሰምተው ቀኖና ከሰጡት ቀኖናውን ጨርሶ ይቆርባል። ይህ ግን ብዙ ጊዜ በአተገባበር የማይቻልና የሚከብድ ስለሆነ ንስሓ አባት ይዞ ከዚያ ንስሓውን ጨርሶ መቀበል የተሻለ ነው።

**፳፱. በሀገራችን በብዛት ሰዎች ከወለዱ ካረጁ በኋላ የንስሓ አባቶች ምዕመናንን ካልመነኮሳችሁ እያሉ ሲያመነኵሱ እናያለን። ይህ ነገር እንዴት ነው?**

መልስ፦ በግድ መንኵሱ የሚባል ሥርዓት የለም። ይህ የአለማወቅ ውጤት ነው። የንስሓ አባቶች መማር ማወቅ አለባቸው። በትዳር የነበሩ ሰዎች እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ እንደማንኛውም ሰው ንስሓ እየገቡ እየቆረቡ ይኖራሉ እንጂ ካልመነኮሱ የሚል ሥርዓት የለም።

**፻፺፫. መስቀል ስንሳለም ግንባራችንን ሲነካው ያሰብነው ኃጢአት ይቅር እንባላለን:: ስንስመው ደግሞ በአፋችን ያወራነው ኃጢአት ይቅር እንባላለን የሚባለው እውነት ነው? እና ንስሐ ስንገባ እነዚህ ይቅር የተባልንባቸውን ኃጢአት ድጋሚ እንገባለን?**

መልስ፦ እንዲህ ያሉ መጻሕፍት ላይ የሌሉ አገላለጾችን ባንጠቀም መልካም ነው:: ሰው ሲሳለም የሚሻሩ ኃጢአቶች ይኖራሉ:: የትኞቹ እንደሆኑ ግን እኛ አናውቅም:: ግንባር ሲነካ፣ ስንስም የሚባል ነገር የለም:: ስለዚህ እኛ አምነን እንሳለማለን:: ስንሳለም እኩይ ፍልስጣ የተባለ ጋኔን የጻፋቸው ኃጢአቶች እንደሚጠፉ ተገልጿል:: የትኞቹ እንደሆኑ አናውቅም:: ስለዚህ ንስሓ ስንገባ የምናስታውሰውን የበደልነውን በደል ሁሉ መናዘዝ እንጂ እያወቅነው ሳንናገር የምንተወው ኃጢአት መኖር የለበትም::

**፻፺፬. እኅተ ሥላሴ፣ እኅተ ገብርኤል፣ ክንፈ ገብርኤል፣ ወልደ ማርያም ወዘተርፈ ዓይነት የክርስትና ስሞች ተገቢ ናቸው?**

መልስ፦ ወልደ ማርያም የሚለው ችግር የለውም:: ምክንያቱም ድንግል ማርያም በቅዱስ ዮሐንስ አማካኝነት እናታችን ሆና ተሰጥታናለችና ነው:: የጸጋ ልጆቿ ስለሆን በዚህ ያስተረጉማል:: ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ወንድሜ እኅቴም እናቴም ነውና" ይላል (ማቴ.12፥50):: በዚህ መሠረት እኅተ ኢየሱስ፣ እኅተ እግዚአብሔር፣ እኅተ ሥላሴ ቢባል ይቻላል:: ምሥጢሩ ግን አንድ ሴት እኅተ ሥላሴ ስትባል የሥለሴን ፈቃድ የምትፈጽም ሴት መሆኗን ያመለክታል:: "የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ወንድሜ ነው እኅቴም እናቴም" እንዳለ ጌታ (ማር.3፥35):: እኅተ ገብርኤል ክንፈ ገብርኤል መባልም በጥምቀት እንደ መላእክት የከበርን እንደምንሆን መግለጫ ስለሆነ ይቻላል::

**፻፺፭. አንድ የመንግሥት ሠራተኛ የመጀመሪያ ሙሉ ደሞዙን ሙሉውን፣ ነጋዴ የመጀመሪያ ሙሉ ትርፉን፣ አርብቶ አደር መጀመሪያ የተወለዱትን ነው መስጠት ያለባቸው? ይህስ ትንሽ ለሰዎች ፈተና አይሆንም ወይ ማለትም ለምሳሌ ደመወዝተኛ ሙሉ ደመወዙን ከሰጠ እንዴት ነው የሚሆነው? ለገበሬ ሲሆንስ እንዴት ይታያል? አፈጻጸሙን በደንብ ቢያስረዱኝ?**

መልስ፦ ቀዳምያት የሚባለው ከእህሉ መጀመሪያ የደረሰውን መስጠት ነው፣ ከእንስሳት መጀመሪያ የተወለደውን መስጠት ደግሞ በኵራት ይባላል:: ደመወዝተኛ የመጀመሪያ ደመወዙን መስጠት ነው:: ሌላውም መጀመሪያ ያገኘውን ነገር ለእግዚአብሔር መስጠት ነው:: ይህ ደግሞ በእምነት ካየነው የራሱ በረከት አለው:: በሥጋ ዓይን ካየነው ግን ኪሣራ ይመስላል:: ገበሬ ከመጀመሪያው አዝመራ ይስጥ የተባለ ሙሉ አዝመራውን ሳይሆን መጀመሪያ የተሰፈረውን ነው (ዘፀ.23፥19 ትርጓሜ)::

**፻፺፮. አንድ ሰው በቆረበበት ቀን ሌሊት በቆረበበት ልብስ ሕልመ ሌሊት ቢገጥመው በዚያ ልብስ ከዚያ በኋላ መቁረብ ይችላል?**

መልስ፦ እንዲህ ያለ ገጠመኝ ሊያጋጥም ይችላል:: ቢያጋጥምም ግን በዕለቱ ሳይሆን በሌላ ቀን ንጹሕ አድርጎ (አጥቦ) ሊቆርብበት ይችላል::

**፻፺፯. ሁለት ተጋቢዎች ሌላ ደብር (ከተማ) ሥርዓተ ተክሊል ፈጽመው ከጨረሱ በኋላ በትራንስፖርት ወደ ሌላ ደብር (ድግስ ወደሚደረግበት) መሄድ ይችላሉ?**

መልስ፦ የቆረቡ ሰዎች ሩቅ መንገድ አይሂዱ የተባለው እንዳይደክሙ ነው:: በትራንስፖርት መሄድ ግን የማያደክም ስለሆነ አይከለከልም:: የትራንስፖርት መንገዱ የማይመችና የሚያደክም ከሆነ ግን አይቻልም::

**፻፺፰. ምጽዋት ድኅነትን ያበረታታል የሚሉ አሉ:: እርስዎ ምን ይላሉ?**

መልስ፦ ይህ እንኳ የምቀኞች አስተያየት ነው:: ምጽዋት ሰው እግዚአብሔርን የሚመስልባት ግብር እንደሆነች ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 16 ይገልጻል:: ምጽዋት የምንሰጥ ሠርተን፣ ለፍተን ካገኘነው ነው:: ምጽዋት የሚሰጠው ሰው ደግሞ ተቸግሮ ለሚኖር ሰው ነው:: ሰው ሳይቸግረው ምጽዋት መቀበል እንደሌለበት ግን ተጽፏል:: ይህ የነዳያንን ምግብ መቀማት ነውና:: ስለዚህ መሥራት የሚችል ሰው በደንብ ሠርቶ ራሱን ረድቶ ሌላውን ይረዳል:: "ብፁዕ ዘበአማን ዘይክል ተራድኦተ ርእሱ" እንዲል (ዲድስቅልያ 19):: የተቸገረን መርዳት ድኅነትን አያስፋፋም:: ታዲያ የተቸገረው ሰው ሳንረዳው ቀርተን ይሙት!? ይህ ርኅራኄ የማጣት፣ የሰይጣን አረመኔያዊ እሳቤ ነው:: የዕድገት ፀር ጠንክሮ አለመሥራት፣ ምቀኝነት ነው እንጂ ሰውን መርዳት የዕድገት ፀር አይሆንም::

**፻፺፱. አንድ ካህን ሚስቱ ብትሞትበት ሳይመነኩስ መቀደስ ይችላል?**

መልስ፦ አዎ ይችላል:: ሚስቱ ስለሞተች ተብሎ ከቅዳሴ መከልከል አይገባም:: ሳይመነኩስ ክህነቱን እንደያዘ ልጆቹን እያሳደገ እየቀደሰ መኖር ይችላል::

**፪፻. ሥዕለ አድኅኖ ከባልና ሚስት መኝታ ቤት ማስቀመጥ ይቻላል ወይ?**

መልስ፦ ሥዕለ አድኅኖ የከበረ ስለሆነ ከቤት የሚቀመጥ ከሆነ ጸሎት ከምትጸልዩበት የጸሎት ቤት (ቦታ) ማስቀመጥ ነው:: ስለዚህ ከመኝታ ቤት መቀመጥ የለበትም:: ምንም እንኳ በጋብቻ የሚደረግ ግንኙነት ክቡር ቢሆንም ክቡር ነው ብለን ከቤተክርስቲያን እንደማንፈጽመው ሁሉ በቅዱሳት ሥዕላት አጠገብም መደረግ የለበትምና::

**፪፻፩. አንድ ቤተሰብ አለ:: በፊት ቅድመ አያት ላይ የአወልያ መንፈስ ነበረ:: እና ሰዎች እየሄዱ የሚደረገውን ነገር ያደርጉ ነበር:: ከዚያ እሳቸው ከሞቱ በኋላ አሁን ላይ በልጅ ልጅ ልጅ ልጅ ላይ ያ መንፈስ መጣ እና ቤተሰቦቹ የሚያምኑት የቤተሰብ ጠባቂ ነው ሰይጣን አይደለም ይላሉ:: ጠበል ሄዶ ነበረ ግን አይጮህም አሉ:: አሁን ልጁ ያንን መንፈስ ተቀብሎ**

የሚያደርጉትን እያደረጉ አሉ። ያ ቤተሰብ ኦርቶዶክስ ነው። ጥያቄዬ መንፈስ ከዘር ወደ ዘር ይተላለፋል ወይ? ያንን ቤተሰብ በምን ማገዝ ይቻላል? በአሁኑ ሰዓት እነርሱን ማሳመን ከባድ ነው። መዓት ወይ ቁጣ ይመጣል ብለው ያምናሉና። ምን እናድርግ?

መልስ፦ ሰው ባለማወቅ የዛር፣ የአወልያ፣ የአቴቴ፣ የቤት አምላክ፣ የቆሌ ወዘተ እያለ የመናፍስት አምልኮ ውስጥ ይገኛል። ከዚህ ነገር እንዲላቀቅ ስናስተምረውም ከዚህ በፊት ባገለበተው እምነት ምክንያት መከራ የሚደርስበት እየመሰለው የሚጎዱትን መናፍስት ተሸክሞ ይኖራል። ስለዚህ መፍትሔው መጀመሪያ ሰዎችን ከተሳሳተ አመለካከት ማዳን ነው። የሚያመልኳቸው መናፍስት የእነርሱ ዋና ጎጂዎች እንጂ በምንም መልኩ እንደማይጠቅሟቸው መንገር ነው። እግዚአብሔር ቸር ስለሆነ ታግሿችሁ እንጂ የምታመልኳቸው መናፍስት ዓላማቸው እስካሁን ድረስ እናንተን ማጥፋት እንደሆነ ማወቅ አለባችሁ። ሳያጠፏችሁ ፈጥናችሁ ተዋቸው። ሁልጊዜ የሚጠብቃችሁ እግዚአብሔርን ብቻ አምልኩ እንጂ በታቦት ላይ ጣዖት ደርባችሁ አታምልኩ። በዘር የሚተላለፍ መንፈስ የለም። ነገር ግን ልጆችም የመናፍስትን አሠራር አምነው የሚፈጽሙ ከሆነ ሊተላለፍባቸው ይችላል። የዚህ ተጠቂ ካሉም ንስሓ ገብተው ሥጋውን ደሙን በመቀበል መላቀቅ ይችላሉ።

፩፻፪. ሕፃናት ክርስትና ሲነሡ በጎን ቅዳሴ ይገባል በጎን ይነሣሉ እና አግባብ ነው ወይ?

መልስ፦ ሁለቱም የተልዕኮው አንድ አካል ስለሆኑ ምንም ችግር የለውም። ይህንን የመሰለ በጎን ማሕሌት፣ በጎን ሰዓታት የሚቆምበት አግባብ አለ። ሁለቱም የአንድ ተልዕኮ አካል ስለሆነ ምንም ችግር የለውም።

፩፻፫. የጣትና የጆሮ ቀለበት በተአምረ ማርያም ብቻ የሚወልቅ ተአምሯ ከቅዳሴውና ከሰዓታቱ ይበልጣል?

መልስ፦ ስለመበላለጥ የተጻፈ ነገር በሌለበት ከመሬት ተነሥቶ ይበልጣል ወይ? ብሎ መጠየቅ ተገቢ አይደለም። ለሁሉም የየራሳቸው ሥርዓት አላቸው። አባቶች ለተአምረ ማርያም ይህንን ሥርዓት ሠርተዋል። ለቅዳሴው ደግሞ ልዩ ልዩ ሥርዓቶችን ሠርተዋል። ለወንጌልም ልዩ ሥርዓት አለ። ይህ በየራሱ የምንመለከተው እንጂ ከሌላው ጋር በማመዛዘን የምናነጻጽረው አይደለም። ከላይ የተጠቀሱት ሁሉ ጠቃሚ እንደሆኑ አምነን እንደየሥርዓታቸው እንተገብራቸዋለን እንጂ ይህ ይበልጣል ይህ ያንሣል እያልን የሥራ ፈት ምደባ አንመድብም።

፩፻፬. ጊዜ ምንድን ነው? ቀጥ ያለ? እየዞረ የሚመለስ? ህልውና ያለው ነገር ነው?

መልስ፦ ጊዜ የሚባለው በድርጊትና በድርጊት መካከል የተፈጸመውን ቅደም ተከተል ለመግለጽ የሚያገለግል ነው እንጂ በራሱ አካላዊ ህልውና ያለው ነገር አይደለም። ጊዜ

የድርጊቶች ወይም የሁኔታዎች ጥገኛ ወይም ከእነርሱ አንጻር የሚተረጎም እንጂ ራሱ ህልውና የለውም። ስለዚህ ቀጥ ያለ፣ የሚመለስ፣ ህልውና ያለው ነገር አይደለም። ለምሳሌ የአንድ ሰው ዕድሜ 20 ዓመት ነው ስንል ይህ 20 ዓመት ከሰውየው መኖር አንጻር የሚገለጽ ነው። አንድ ቀን ስንል ከጨለማና ከብርሃን አንጻር የሚተረጎም እንጂ ጨለማና ብርሃን እንዲፈራረቁ ያደረገ ማንነት ወይም ምንነት ያለው ነገር አይደለም። ጊዜ የተፈጠረ ነው እያልን ስንናገርም ፍጥረታት ተግባራቸውን ሲያከናውኑ የሚቆጠረው ጊዜ ከፍጥረታት ተግባር ጋር የጀመረ መሆኑን ለመግለጽ ነው እንጂ ራሱን የቻለ ህልውና ያለው ነገር ነው ማለታችን አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ "በመጀመሪያ" ተብሎ የተገለጸው ጊዜ ከሰማይና ምድር መፈጠር አንጻር የሚነገር እንጂ ራሱ ህልውና ያለው ነገር አይደለም።

**፪፻፮. እግዚአብሔር በነቢብ ፈጠረ ስንል ይህ ነቢብ እኛ የምናውቀው ከአየር ሞገድ ጋር ተጋጭቶ የሚሰማ ነቢብ አይደለም ይባላል። ታዲያ ይህ ነቢብ ምንድን ነው?**

መልስ፡- በትርጓሜ እንደተገለጸው ይህ ነቢብ የልቡና ነቢብ ነው። ንባብ ወይም ንግግር ብዙ ጊዜ ሁለት ደረጃዎችን ያልፋል። አንደኛው በልቡና ሲታሰብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በአንደበት ሲገለጽ ነው። እግዚአብሔር ለይኩን ብርሃን ሲል ለመላእክት በነቢብ አሳወቀ መባሉ ሐሳቡን እንዲያውቁት ማድረጉን ያመለክታል።

**፪፻፯. ጨለማ ፍጡር ነው? አካልስ አለው?**

መልስ፡- አዎ ጨለማ በዕለተ እሑድ ከተፈጠሩ ሰባት ፍጥረታት አንዱ ነው። አካልም አለው። አካሉ ረቂቅ በመሆኑ ባንዳስሰውም አለው።

**፪፻፰. እግዚአብሔር ቅድመ ሥጋዌ ከአካላዊ ቃሉ ውጭ ዝርው ቃልን ተናግሯል?**

መልስ፡- ስለቃል ስንነጋገር መለየት ያሉብን ጉዳዮች አሉ። ክርስቶስን ቃለ እግዚአብሔር ስንለው አካላዊ ቃል መሆኑን በመገንዘብ ነው። ነገር ግን ይህ እግዚአብሔር ምሥጢሩን ለነቢያት ሲገልጽ የተናገረውና ለነቢያት የተሰማው ድምፁ ዝርው ነው። ስሙም ቦርፎሪኮን ይባላል። ስለዚህ ቅድመ ሥጋዌም እግዚአብሔር ወልድ ራሱ አካላዊ ቃለ እግዚአብሔር ቢሆንም ለነቢያት፣ ለመላእክት ሲናገር የተሰማው ድምፁ ዝርው ነው።

**፪፻፱. ሕማማተ መስቀል የሚል መጽሐፍ ላይ የባሕርይ አምላክ ነው ያሉ ክርስቲያን ተባሉ አምላክ አይደለም የአምላክ ወዳጅ ደግ ነቢይ ነው ያሉ ሙስሊሞች ተባሉ የሚል አለ። ይህ እንዴት ነው? ሙስሊሞች ክርስቶስ ከመሰቀሉ በፊት ነበሩ?**

መልስ፡- የእስልምና እምነት የተመሠረተው በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በመሐመድ አማካኝነት ነው። ስለዚህ ከስቅለት በፊትም ከስቅለት በኋላም እስከ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስልምና አልነበረም። ሕማማተ መስቀል ግን ከእስልምና መነሣት በኋላ

የተጻፈ መጽሐፍ በመሆኑ በነገረ ክርስቶስ ዙሪያ ሙስሊሞች ምን እንደሚሉና ክርስቲያኖች ምን እንደሚሉ ለይቶ ገልጾልናል። ሙስሊሞቹ ክብር ይግባውና ክርስቶስን ሰው ብቻ ነው ብለው አምላክነቱን ሳይቀበሉ ይኖራሉ። ክርስቲያኖች ግን ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው መሆኑን ያምናሉ ማለት ነው።

፪፻፱. YouTube ለመሥራት ከሚሞሉ ነገሮች መካከል ሀገር (location) አንዱ ነው። እና ኢትዮጵያ partnership ስላልሆነች ኢትዮጵያ ብሎ መሙላት ክፍያ አይኖረውም። ስለዚህ location USA ወይም UK በማለት ሌላ ሀገር ሞልቶ YOUTUBE መሥራት ውሸት በመዋሸት ሥራ ላይ መሰማራት አይሆንም ወይ?

መልስ፦ ይህቺ ጥያቄ የዩንቨርሲቲ ተማሪ ድጌ ኃጢአት ነወይ ከሚላት ጥያቄ ጋር ትመሳሰላለች። በመሠረቱ ድጌ ኃጢአት ነው (የስርቆት የስለላ ስም ናት😁)። የዩቲዩቡ ጉዳይ ግን ከዚህ ጋር የሚገናኝ አይመስለኝም። ሀገራቸው ዜግነታቸው ኢትዮጵያዊ ሆነው አሜሪካ ሀገር እንደሚሠሩ ሰዎች የሚታይ ነው የሚል ግላዊ ምልከታ አለኝ።

፪፻፲. በግንቦት ወር ቃልኪዳን፤ ሰርግ አይደረግም ይባላል። ከምን የተገኘ ነው?

መልስ፦ እንደዚህ የሚባል የቤተክርስቲያን አስተምህሮ የለም። ስለዚህ ሰው ከአጽዋማት ውጭ በማናቸውም ቀናት ጋብቻን መፈጸም ይችላል።

፪፻፲፩. የንሰሐ አባት ነበሩኝ። ነገር ግን እኔ ብቻ ስፈልጋቸው ነው የምሄደው እርሳቸው እኖር አልኖር እምነት ልቀር አልቀይር ምንም የሚያውቁት ነገር የለም። ባለሁበት አካባቢ የንስሓ አባት ልይዝ ፈልጌ ሳናገራቸው የመጀመሪያ የንሰሐ አባት ነበረኝ ነገር ግን አልተሰናበትኩም ስላቸው ሰበካ ጉባኤ ትከፍል ነበር ወይ አሉኝ። አይ አልከፍልም ነበር ስላቸው ግዴታ መሰናበት የለብህም አሉኝ። እርሶ ምን ይላሉ በዚህ ጉዳይ?

መልስ፦ ንስሓ መግባት አለመግባት ከሰበካ ጉባኤ ክፍያ ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም። ሌላ ንስሓ አባት ለመያዝ ደግሞ የነበርንባቸውን ማስፈቀድ ለእርሳቸው ኅሊናም ለአንተም ይጠቅምሀል። ንስሓ አባት ደግሞ ልጆቹ ምን ላይ እንዳሉ መከታተል ይገባዋል። ይህንን ካላደረገና ካልተቆጣጠረ እርሱን ተሰናብቶ ሌላ የተማረ አባት መያዝ ነው።

፪፻፲፪. የጅራፍ ማጮህ ከእመቤታችን ልደት ጋር ያለው ምሳሌነት ምንድን ነው?

መልስ፦ አላውቀውም። በግንቦት ልደታ ጅራፍ እንደሚጮህም አላውቅም። ጅራፍ ማጮህ በደብረ ታቦር ነሐሴ 13 መደረጉ በተራራ በክብር የተገለጠው ጌታ በአይሁድ እንደሚገረፍ ያመለክታል የሚሉ ሰዎች አሉ። በሌላ መልኩ ጅራፍ ሲጮህ ከሩቅ እንዲሰማ አብ ለወልድ የሰጠው ምስክርነት ለትውልድ ሲነገር የመኖሩ ምሳሌ ነው

የሚሉ አሉ። ምናልባት የድንግል ማርያም በሊባኖስ መወለድም ለትውልድ እየተነገረ ለመሄዱ በዚህኛው አንጻር ለመግለጽ ታስቦ ይሆንን?? እኔ እንጃ አላውቀውም።

**፪፻፲፫. አንድ ካህን የንስሓ ልጁ ሴት ናት። በመድፈርም ይሁን በስሕተት ሌላ ካህን ከእርሷ ከተኛ ወይም ዝሙት ከፈጸመ ለአበ ነፍሷ ትነግረዋለች። ይህ የንስሓ አባት ዝሙት የፈጸመውን ካህን ከቤተ መቅደስ ያግደው ወይስ እንደ ምስጢረ ንስሓ ዝም ማለት አለበት?**

መልስ፦ ልጂቱ ይህ ስለተፈጸመባት ንስሓ ትገባለች። ካህኑም ለጥፋቷ ቀኖናን ሰጥቷት ቀኖናዋን ጨርሳ ሥጋውን ደሙን ትቀበላለች። ያ ደፈረኝ ያለችው ካህን ግን እርሷ ደፈረኝ ብትልም የእርሱን ቃል ደግሞ መስማት ስለሚገባና የከሳሽን ብቻ ሳይሆን የተከሳሽንም ሐሳብ መስማት ስለሚገባ ሰበካ ጉባኤው የማጣራት ሥራ ሠርቶ እንደደፈረ ከተረጋገጠ ክህነቱ በጳጳሱ እንዲያዝ ደብዳቤ ይልካል። ጳጳሱም ይወስናል። ለካህን ክህነትን የሚሰጥ ጳጳስ እንደሆነ ሁሉ ካህንን ከክህነቱ የሚሽርም ጳጳስ እንጂ ካህን ስላልሆነ ሌላው ካህን ከማመልከት ውጭ የመከልከል ሥልጣን የለውም። ጉዳዩ ቤተክርስቲያንን የሚያስነቅፍ በመሆኑ ካህኑ ይህንን ነገር ሰምቶ ቸል ብሎ በዝምታ ሊያልፈው አይገባም። የልጅቱን ስም ሳይጠቅስ በሥውር ያ ሰው እንዲመረመር በየደረጃው ላሉ የአስተዳደር አካላት ማሳወቅ ይገባዋል እንጂ።

**፪፻፲፬. እኔ አሁን ወጣት ነኝ። ትምህርት እማራለሁ። ግን የምማረው ትምህርት አያስደስተኝም። እና ገዳም ለመመነን አሰብኩኝ። ምን ያስፈልገኛል? አሁን ገዳም ውስጥ መንኖ ለመኖር የሚያስፈልገው ምንድን ነው?**

መልስ፦ ወደ ገዳም መመነን ያለብን የዓለምን ምቾት ንቀን እንጂ በዓለም አልሳካልን ሲል አይደለም። ስለዚህ ምንኩስና ወይመ ምናኔ ዝም ብሎ በስሜት የሚገባበት አይደለም። ስለዚህ ወጣት ከሆንክ መጀመሪያ ዓለምን በዓለም ሆነህ አሸንፋትና ናቃት። ሳትመነኩስ እንደመነኮሰ ሰው በቀን አንድ ጊዜ እየበላህ፣ በቀን 252 ስግደት እየሰገድክ ሞክረው። በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዘመን ከቆየህ በኋላ ራስህ አመዛዝነህ ግባበት።

**፪፻፲፭. ካህን /ቄስ/ ምእመኑን ወይም ሥልጣን የሌለውን ገፍቶ ሲጣላ መጣለት ይቻላል ወይስ ሁልጊዜ ተገፍተን ሸሽተን መኖር ብቻ ነው? ከቄስ ጋር የተጣላ ንስሓም የለው ሲሉ እሰማለሁ። ልክ ነው?**

መልስ፦ በእርግጥ ከማንኛውም ሰው ጋር መጣላት አይገባም። ከቄስም ይሁን ከሌላ ጋር በተለያዩ ምክንያቶች ተጣልተን ከነበረ ግን ንስሓ ብንገባ ይቅር እንባላለን። ንስሓ የሌለው ኃጢአት የለምና። ቄስ ገፍቶ ሲጣላህ በተቻለ መጠን ሽሸው። ሽሽተህ የማታመልጠው ከሆነ ግን ለሕግ አካላት አሳውቆ ፍትሕ ማግኘት ይገባል። መንፈሳዊ ፍርድ ቤት ቢኖር በዚያ መዳኘት ይገባል። ከሌለ ደግሞ ሰበካ ጉባኤው አስተዳደራዊ እርምጃ እንዲወስድ በሰበካ ጉባኤ ጉዳዩን መፍታት ነው።

**፪፻፲፮. ክርስቶስ ልብሱን አይሁድ በዕለተ ዓርብ ቀደውታል:: በትንሣኤ የለበሰው ልብስ ከየት የመጣ ነው?**

መልስ፦ ጌታ በትንሣኤ የለበሰው ልብስ ከትንሣኤ በኋላ እኛም የምንለብሰው ዓይነት የብርሃን ልብስ እንጂ ምድራዊ ልብስ አይደለም:: ራሱ እግዚአብሔር ለጻድቃን በኵር ይሆን ዘንድ ለብሶት የታየው አዳም በገነት ሳለ ይለብሰው እንደነበረው ያለ ልብሰ ብርሃን ነው::

**፪፻፲፯. ዲያቆናት ለካህናት መታዘዝ አለብን:: ነገር ግን ካህናት ሥርዓት አፍርሰው ቢያዝዙን መታዘዝ አለብን?**

መልስ፦ ፍቅረ ቢጽ ከፍቅረ እግዚአብሔር ቀጥሎ የሚመጣ ነው:: ስለዚህ ከእግዚአብሔር ሕግና ሥርዓት ውጪ ካህናትም፣ ቤተሰቦቻችንም ቢያዝዙን መቀበል አይገባንም:: ሕገ እግዚአብሔርን የማይቃወም ነገር ቢያዝዙን ግን መታዘዝ የፍቅረ ቢጽ መገለጫ ነው::

**፪፻፲፰. በሃይማኖት ምክንያት አንድ ዲያቆን መሣሪያ መታጠቅ ይችላል?**

መልስ፦ አይችልም:: ዲያቆናት፣ ካህናት ሌላውን ሰው መሣሪያ ታጥቀው ይገድሉ ዘንድ አልተፈቀደም:: ክህነት የሌላቸው ምእመናን ግን ታጥቀው ቤተክርስቲያንን፣ ሀገርን መጠበቅ ይችላሉ:: "ኢይደልዎሙ ቀቲል ለካህናት ከመ ኢይሰዐሩ እምክህነቶሙ ወሕጎሙ:: ወለሕዝባውያንሰ ብውሕ ሎሙ እምኀበ ልዑል ከመ ይቅትሉ በፍትሕ እለ ይደልዎሙ ሞት" እንዲል (ድርሳነ ሚካኤል)::